የሥርአተ-ትምህርት ማስማማትና የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር መመሪያ

ፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር

2004 ዓ. ም

ማውጫ

ገጽ

መቅድም 1

1. የመመሪያው አስፈላጊነት 2

2. ትርጉም 4

2.1 ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች 4

2.2 ሱካቶ ትምህርትና አካታች ት/ቤቶች 4

2.3 መቀላቀል (Integration) 5

2.4 ልዩ ትምህርት 5

2.5 ልዩ ፍላጎት ትምህርት 5

2.6 የድጋፍ መስጫ ማዕከል 6

2.7 ተዘዋዋሪ ተንቀሳቃሽ መምህር 6

2.8 ሜታ ኮግኒቲቭ ክሂሎች (Metacognitive Skills) 6

3. ሥርዓተ ትምህርት ማስማማት 7

3.1 ስርዓተ ትምህርት 7

3.2 አካታች ሥርዓተ ትምህርት 10

3.3 አካታች የመማሪያ ክፍሎችን ስለማደራጀት 11

3.3.1 የመማሪያ አካባቢ 12

3.3.2 በራስ መተማመን /Self-esteem/ 12

3.3.3 ተስማሚ የማስተማሪያ አካባቢን ማደራጀት 12

3.3.4 የትምህርቱን ስራ ማቀድና መተግበር 13

3.3.5 ተገቢ የሆኑ የሙከራ ስራዎች (optimal assignments) 13

3.3.6 የመሸጋገሪያና የጊዜ አጠቃቀምን ከተማሪው ፍላጎት ጋር ስለማጣጣም፤ 14

3.3.7 ድግግሞሽ፣ 15

3.3.8 ድጋፍ፣ 15

3.3.9 የመማሪያ፣ አካባቢን ማመቻቸት (Managing behavior in the classroom) 15

3.4 ስርዓተ ትምህርቱን ስለማስማማት 16

3.4.1 ይዘትን ስለማስማማት 17

3.4.2 የማስተማር ዘዴን ተስማሚ ስለማድረግ 19

3.4.2.1 በህብረት የማስተማር ዘዴ 19

3.4.2.2 በህብረት መማር (አቻ ለአቻ ትምህርት) Peer tutoring 21

3.4.2.3 ራስን በመምራት የመማር ዘዴ /Self - regulated–learning/ 22
3.4.2.4 በህብረት ማስተማር 22
3.4.2.5 የጣምራ ማስተማር ዘዴ (Co teaching) 23
3.4.3 የማስተማር ዘዴና መሣሪያዎችን ተስማሚ ስለማድረግ 24
3.4.4 የትምህርት ቅስሞሽ ምዘናን ስለማስማማት 25
3.4.4.1 የትምህርት ቅስሞች ውጤቶች 26
3.4.4.2 ግብረ-መልስ 27
3.4.4.3 ተከታታይነት ያለው ምዘና 27
3.4.4.4 ምልከታ 28
3.4.4.5 የማህደር ምዘና 28
3.4.4.6 ሙከራዎች (tests) 29
3.4.4.7 ራስን መመዘን 29
4. የግል የትምህርት መርሀ ግብር 29
4.1 የግል የትምህርት መርሀ-ግብር ለምን አስፈለገ? 30
4.2 የግል የትምህርት መርሃ-ግብር አዘገጃጀት 31
4.3 የግል የትምህርት መርሀ-ግብር ሂደት 32
4.4 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን 34
4.4.1 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን ዓላማ 34
4.4.2 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን አባላት ስብጥር 35
4.4.3 የነስፍ ወከፍ የትምህርት መርሃ -ግብር ቡድን አባላት ሚናና ኃላፊነት 35
4.4.3.1 ተማሪዋ/ው 35
4.4.3.2 ወላጅ/አሳዳጊ 36
4.4.3.3 የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር 36
4.4.3.4 የክፍል ወይም የትምህርት ዓይነቱ መምህር 36
4.4.3.5 ልዩ መምህር/ተዘዋዋሪ መምህር 37
4.4.3.6 ሌሎች 38
4.5 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን ስብሰባ 38
4.6 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ማዘጋጀት 39
4.6.1 የተማሪዋ/ው ብቃት 39
4.6.2 በትምህርት ቤት የተማሪዋ/ው ሁኔታና የመማር ችግሮች መግለጫ 40
4.6.3 ግቦች 40

4.6.4 ዘዴዎች 41
4.6.5 የቁሳቁሶች አቅርቦት 41
4.6.6 አደረጃጀትና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢ 41
4.6.7 በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጭ የሚደረግ ድጋፍ 42
4.6.8 ምዘና 42
4.6.9 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ምሣሌ 42
4.7 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን መተግበር 47
4.8 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን መመዘን 49
4.9 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቅፅን መፈራረም 50
ተቀፅላ 1፡ የትምህርት ቅስሞች መንገዶች (learning Styles) 51
ተቀፅላ 2፡ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቅፅ 55
ተቀፅላ 3፡ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ናሙና 1 58
ተቀጽላ 4፡ የነፍ ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር ናሙና 2 62
ተቀጺላ 5፡ የግለ ግምገማ ቅፅ 66
ተቀጺላ 6 ፡ የትምህርት ፅንሰ-ሃሳቦች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች 67

መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር በ1994 ዓ.ም በትምህርት ስልጠና ፖሊሲው ላይ የተመሰረተ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂ ቀርፆ ሲንቀሳቀስ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ይህንኑ ስትራቴጂ ይበልጥ ለማጠናከር ታስቦም የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ በአዲስ መልክ ተቀርጿል። የስርዓተ ትምህርት ማስማማት ጉዳይም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን ተከትሎ በስትራቴጂው ላይ አፅንኦት የተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ይህ የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል።

በትምህርትና ሥልጠና (1994) ፖሊሲ ላይ በግልፅ እንደሠፈረው ሁሉም ተማሪዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ጨምሮ እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው መማር እንደሚገባቸው ተደንግጓል። ትምህርት የዜጎችን ዲሞክራሲያዊ እሴቶችንና እኩልነትን ከሰብዓዊ መብት ጋር አጣምሮ ሊያስገኝ የሚችል መሣሪያ ከመሆኑም ባሻገር ድህነትን በመቀነስ ዜጎች ሁሉ በአገሪቱ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል መሣሪያም ነው። (ትምህርት ሚኒስቴር 1994) ።

ይሁን እንጂ አገራችን የትምህርት ለሁሉም ግቦችን ለማሳካት ከምታደርገው ጥረት አኳያ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ አሁንም ክፍተት መኖሩ ይስተዋላል። እነዚህን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ የሚያስችል የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ አለመደራጀት፣ የተመቻቸ የመማሪያ አካባቢ አለመኖር፣ የመማር ችግራቸውን ለይቶ እገዛ ለመስጠት የሚያስችል የመለያና የዳሰሳ ሥርዓት አለመጠናከር ዋና ዋናዎቹ ተግዳሮቶች እንደሆኑም ይታመናል። ከዚህ ባሻገር ተለማጭ የሆነ ስርዓት ትምህርት ያለመኖር ዓይነተኛው እንቅፋት ሲሆን መምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ የሚያስችል የስርዓተ ትምህርት ማስማማት ክሂልን አለመታጠቅም ችግሩን ይበልጥ እንዲባባስ አድርጎታል።

በመሆኑም፣ ትምህርት ቤቶች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ተቀብለው እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው ለማስተናገድ ያላቸውን ፈቃደኝነት ሲገዳደራቸው ይስተዋላል። ይህ መመሪያም በአንድ በኩል ስርዓተ ትምህርትን በማስማማት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የሚደርስባቸውን ተግዳሮት መስበር የሚቻልበትን መንገድ የሚያመላክት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መምህራን እያንዳንዱን ተማሪ ለማገዝ የሚያስችል የትምህርት አቀራረብ በመጠቀም ካላስፈላጊ ድካም ራሳቸውን ሊጠብቁ የሚችሉበት መሣሪያ ይሆናል ተብሎም ይታመናል።

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ አጠቃላይ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ተጠቃሚ ካለመሆናቸው በተጨማሪ ያለምንም ተጨማሪ ድጋፍ በትምህርት ገበታ ላይ ስለሚገኙ የመጨረሻው ዕጣ ፈንታቸው ትምህርት ማቋረጥ ወይም መድገም ይሆናል። በትምህርት ሚኒስቴር (1994) መግለጫ መሠረትም የትምህርት ዘርፉ-ኃላፊዎች መጠነ ማቋረጥንና መድገምን በመቀነስ ረገድ የሚጠበቅባቸውን

ኃላፊነት በተገቢው መንገድ እንዲወጡ ማስገንዘቡ የጉዳዩን አሳሳቢነት ይበልጥ የሚያመላክት ይሆናል፡፡

ተማሪዎች ከአካባቢያቸውና ከቀያቸው ሳይርቁ ባሉበት አካባቢና በአጎራባች ትምህርት ቤቶች ሁሉ እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው በእኩልነት እንዲሳተፉና ብሎም መጠነ መድገምንና ማቋረጥን ለመቀነስ ካስፈለገ የስርዓተ ትምህርት ማስማማትና የግል የትምህርት መርሀ ግብር መተግበር ሊታለፍ የማይገባው የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡ የስርዓተ ትምህርት ማስማማት ሥራ በተማሪው የመማር ችግር፣ ዝንባሌና የግል ችሎታ ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ የግል የትምህርት መርሀ ግብር ተነድፎለት በተግባር ላይ የሚውል ነው፡፡

የግል የትምህርት መርሀ ግብሩም በዓላማ ላይ ያተኮረና አስፈላጊውን የድጋፍ ዓይነትና ስርዓት አካቶ የሚይዝ ሲሆን ዘለቄታዊ ግቡም ትምህርት ቤቶችና ብሎም በመማር-ማስተማሩ ተግባር የተሰማሩ መምህራንንና ብዝሀ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ፍላጎት የሚያረካ መሣሪያ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ በጋራ የመስራት ተነሳሽነትን ልናዳብር ይገባል፡፡

3. የመመሪያው አስፈላጊነት

ይህ መመሪያ በዋናነት የሚያተኩረው ስርዓተ ትምህርትን በማስማማትና የግል የትምህርት መርሀ ግብር አጠቃቀምን በአገራችን የትምህርት ሥርዓት ውስጥ በማስተዋወቅ ላይ ነው፡፡ ከላይ በመቅድሙ ላይ ለማስቀመጥ እንደተሞከረው የግል የትምህርት መርሀ ግብርም ሆነ ሥርዓተ ትምህርቱን የማስፋፋት ክንዋኔዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናትና ወጣቶችን በትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ዓይነተኛ መንገድ ነው፡፡

በትምህርት ዘርፉ የ2006 የልማት ፕሮግራም (ESDPIII) በግልፅ እንደተስተዋለው አካቶ ትምህርትን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል እንቅፋት ይሆናሉ ተብለው ከሚታሰቡት ተግዳሮቶች መካከል የሥርዓተ ትምህርቱ ተለማጭ አለመሆንና መምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ የሚያስችል በዘርፉ በቂ የሆነ ስልጠና አለማግኘት ዋነኞቹ ናቸው፡፡

እንደ ትምህርት ዘርፉ የልማት ፕሮግራም(ESDPIV) መግለጫም መምህራን ሥርዓተ ትምህርቱን የማስማማት ክሂል እንዲላበሱ ለማድረግና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ድጋፍ እንዲያደርጉ ለማስቻል፣ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

ይሁን እንጂ፣ በት/ቤት ደረጃ ሥርዓተ ትምህርቱን ለማስማማትም ሆነ የግል የትምህርት መርሀ ግብርን ለመቅረፅ የሚያስችል መመሪያ እስከአሁን ድረስ አልተዘጋጀም፤ በመሆኑም ይህ መመሪያ ትምህርት ቤቶቻችን የአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ስርዓተ ትምህርት የማስማማት ሥራ በማከናወን የትምህርት ስራቸውን ቀላልና ግልፅ በሆነ መንገድ እንዲተገብሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ይህ መመሪያ ሥርዓተ ትምህርቱን በማስማማትም ሆነ የግል የትምህርት መርሀ ግብር በመንደፍ፣ በመተግበርና ክትትል በማድረግ ሂደት መከተል የሚገባቸውን ተግባራትን በዝርዝር አስቀምጧል።

መመሪያው የመምህራንን የመማር ማስተማር ሥራ ቀልጣፋና ስኬታማ ከማድረጉም ባሻገር በመመሪያው ዕጦት የተነሳ ልዩ ፍላጎታቸው በውል ሳይታወቅ ከትምህርት ገበታ ውጭ እንዲሆኑ የሚገደዱ ተማሪዎችን በትምህርት ቤት ህይወት ለማቆየት የሚያበረክተው ድርሻም ከፍተኛ ነው። የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራንም በዓመቱ መጀመሪያ ላይ የተቀበሏቸውን ተማሪዎች እስከመጨረሻው አዝልቆ ለማስቀጠል የሚያስችል ተግባር በማከናወን ሂደት መምህራንን ማገዝና ማበረታታት ይጠበቅባቸዋል።

ይህ የስርዓተ ትምህርት ማስማማትና የግል የትምህርት መርሀ ግብር መመሪያ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች በማገዝ በኩል በልዩ ፍላጎት ትምህርት ዙሪያ ለሚሠሩ መምህራንና ሌሎች ባለሙያዎችም ጭምር አጋዥ መሣሪያ ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን፤ መመሪያው በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሎ ቀርቧል።

1. የስርዓተ ትምህርት ማስማማት ተግባራትን ያካተተ ሲሆን ዋና ዋና ትኩረቶቹም፣
   - በስርዓተ ትምህርት ማስማማቱ ሂደት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች ለማገዝ ለሚፈልጉ መምህራንና ሌሎች ባለሙያዎች የቴክኒክ ድጋፍ ያበረክታል፣
   - ስርዓተ ትምህርት ማስማማትን በአገሪቱ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሁሉ እንዲተገብሩት እገዛ ያደርጋል፣
   - ስርዓተ ትምህርቱ ለምንና ለማን ተስማሚ ሆኖ መዘጋጀት እንዳለበት ያብራራል፣
   - ስርዓተ ትምህርት የማስማማቱ ሥራ በተግባር እንዴት እንደሚከናወን ይገልፃል፣

2. በግል የትምህርት መርሀ-ግብር አተገባበር ዙሪያ፤
   - መርሀ ግብሩን፣ መርሀ ግብሩን የሚተገብሩ ቡድኖችንና የመርሀ ግብሩን አፈፃፀም ሂደት ያብራራል፣

- የግል የትምህርት መርሀ ግብር አዘጋጅ ኮሚቴዎችን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በውል ያስገነዝባል፣
- መርሀ ግብሩ እንዴት እንደሚዘጋጅ፣ እንዴት በተግባር ላይ እንደሚውልና የክትትል ሂደቱን በተመለከተ በቂ ማብራሪያ ይሰጣል።

4. ትርጉም

2.1. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የምንላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ የመማር ችግሮች የሚያጋጥማቸውንና በዚህም ሳቢያ የአጭርና የረዥም ጊዜ ተጨማሪ ድጋፍን የሚሹ ተማሪዎችን በሙሉ ሲሆን፣ በሌላ አባባል እነዚህ ተማሪዎች የመማርና የዕድገት እንቅፋቶች የተጋረጡባቸው ልጆች ናቸው። እነዚህን ተማሪዎች የጥቅም ተጋሪ እንዳይሆኑና ከትምህርቱ እንዲገለሉ የሚያደርጉ በርካታ ምክንያቶች ሲኖሩ በጥቂቱ ለመጥቀስም፤

- አካል ጉዳተኝነትና ማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች
- ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ
- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዝቅተኝነትና ተያይዞ የሚመጡ የተመጣጠኑ ምግብ እጥረቶች
- ኤችአይቪ ኤድስ
- አናሳ ብሄርተኝነትና ባህላዊ ተፅዕኖ
- ብቸኝነትን የተላበሰ ገጠራማ ኑሮ
- የተለያዩ ጦርነቶችና ግጭቶችን የመሳሰሉት ናቸው

2.2. አካቶ ትምህርትና አካታች ት/ቤቶች

አካቶ ትምህርት ስንል ሁሉም ተማሪዎች ምንም ዓይነት የፆታ፣ የድህነት፣ የብሄር፣ የቋንቋ፣ የአካል ጉዳት መድልዎ ሳይታከልበት በእኩልነት የሚሳተፉበትን መንገድ የሚያመቻች ሲሆን ሁሉም ተማሪዎች መማር እንደሚችሉም የሚያምን ስርዓት ነው። አካቶ ትምህርትን ዕውን ለማድረግም በትምህርት ቤቶች፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማትና በትምህርት አስተዳደር ዘርፍ የሚስተዋሉ የመማር ማስተማር ተግዳሮቶችን ለይቶ ማስወገድና ምቹ የመማሪያ አካባቢን መፍጠር ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ይሆናል። እንደ

(UNESCO 2000; 2001 እና MoE 2006) አገላለፅም የትምህርት ቤት አካባቢዎች የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ለማሟላት በተገቢው መንገድ መደራጀት እንዳለባቸው ያስገነዝባል፡፡

ለዚህም ዕውን መሆን በአካታች ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የማወቅ፣ አካታች ስርዓተ ትምህርትን የመተግበርና ተገቢ የሆነውን ድጋፍ እንደፍላጎታቸው የመስጠት ክህሎትን መላበስ ይጠበቅባቸዋል፣

2.3. መቀላቀል (Integration)

በአካቶ ትምህርት አቀራረብ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ድጋፍ እየተደረገላቸው ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በመደበኛው ክፍል ውስጥ ሲሆን በመቀላቀል አቀራረብ ግን እነዚህ ተማሪዎች ለመሉ ቀን ወይም ለግማሽ ቀን (ለተወሰነ ጊዜ) በመደበኛው ክፍሎች ውስጥ እንዲማሩ ሲደረግ በቀሪው የትምህርት ጊዜያቸው ግን በልዩ ክፍል ወይም ዩኒት ሊመደቡ ይችላሉ፣ አንዳንድ አገሮች መቀላቀልን የአካቶ ትምህርት ሙሉ ትግባራ ከመካሄዱ በፊት እንደ ሽግግር ወቅት ይጠቀሙበታል፡፡

2.4. ልዩ ትምህርት

ልዩ ትምህርት አካል ጉዳተኞችንና የማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች ወዘተ ያሉባቸውን ተማሪዎች በልዩ የመማሪያ ክፍሎች፤ በዩኒቶችና በልዩ ትምህርት ቤቶች በተለየ መልኩ ለማገዝ የሚደረግ የትምህርት አደረጃጀትን ያጠቃልላል፡፡ በነዚህ ትምህርት ቤቶችም ሆነ የመማሪያ ክፍሎች የሚያስተምሩ መምህራንም እነዚህን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ለመርዳት የተለየ ስልጠና የወሰዱ ሲሆን ተማሪዎችም የተለያዩ ባለሙያዎችን እንደ ቴራፒስቶች የመሳሰሉትን የመጎብኘት ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ የተማሪ መምህር ጥምርታውም ከመደበኛው ትምህርት ያነሰ ነው፡፡

2.5. ልዩ ፍላጎት ትምህርት

ልዩ ፍላጎት በመሰረቱ ልዩ ትምህርትን ተክቶ የመጣ አደረጃጀት እንጂ ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው ፅንሰ-ሀሳቦች አይደሉም፡፡ ይልቁንም ለአካል ጉዳተኞችም ሆነ የማህበራዊና ስሜታዊ ችግር ያሉባቸውን ጨምሮ የመማር ችግሮች ያሉባቸውን ተማሪዎች ለማገዝ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ሁሉ ያካትታል፡፡ ይህም በልዩ ትምህርት ቤቶችና በልዩ የመማሪያ ክፍሎች ከሚሰጡ የትምህርት ድጋፎች ጀምሮ በማካተት የሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፡፡

2.6. የድጋፍ መስጫ ማዕከል

የድጋፍ መስጫ ማዕከል የምንለው ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች መገልገያ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን፣ የአካል ድጋፍ መስጫ መሳሪያዎችንና ለሁሉም ተማሪዎች የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን የያዘ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከልን ነው። ከዚህም በተጨማሪ ይህ ማዕከል ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች፣ ለመደበኛ መምህራንና ለጎረቤት ትም/ቤቶች ድጋፍና የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ይይዛል።

2.7. ተዘዋዋሪ ተንቀሳቃሽ መምህር

ተዘዋዋሪ መምህር በልዩ ፍላጎት ትምህርት የተመረቀ ባለሙያ ሲሆን ለመደበኛ መምህራን፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችና ለወላጆች የምክር አገልግሎት ይሰጣል። የሚሰጠውም አገልግሎት፣ የተማሪውን የነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር ትግበራን፣ የልጁን የትምህርት ፍላጎት ዳሰሳን፣ ከሳተላይትና ከጎረቤት ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ-መምህራንና መምህራን ጋር ትብብር መፍጠርን፣ የልጁን የትምህርት ግቦች ለመምታት ሌሎች ባለሙዎችንና ወጌሻዎችን ማስተባበር፣ በተማከለ ቡድን (core team) ተግባራት ውስጥ መሳተፍና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

2.8. ሜታ ኮግኒቲቭ ክሂሎች (Metacognitive Skills)

ሜታኮግኒቲቭ ስንል ስለመማር መማር ማለት ሲሆን ይህም ማለት ስለምንማረው ነገር በይበልጥ የመረዳት ክሂልን ያመለክታል። ይበልጥ ዘርዘር አድርገን ስናየውም ተማሪዎች የመረዳት ክሂሎታቸውን በመጠቀም አዳዲስ ሀሳብን፣

- የመረዳት
- የመቆጣጠር
- የመተግበር
- የሚተላለፍላቸውን መረጃ በአግባቡ የመተርጎም
- ደካማ ጎኖችን ለይቶ የማወቅ
- ድክመቶችን በአፋጣኝ የማረም
- ከአዳዲስ ሃሳቦች ጋር ራስን የማጣጣም ግንዛቤው እውቀትና ችሎታው እንዳላቸው አስቀድሞ መገንዘብን ይመለከታል፤

5. ሥርዓተ ትምህርት ማስማማት

ስርዓተ ትምህርትን ማስማማት ስንል መደበኛውን የስርዓተ ትምህርት በማያዛባ መልኩ በአንድ ክፍል ውስጥ ለሚገኙና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች በሚመች መልክ ስርዓተ ትምህርትን የማጣጣም ተግባር ማከናወን ማለት ነው። ስርዓተ ትምህርቱን ለሁሉም ተማሪዎች በሚመች መልክ ማጣጣም ለመምህራን ሊገዳደር የሚችል ተግባር ቢመስልም አካታች ስርዓትን ለማራመድ ግን ቁልፉና መሠረታዊው ተግባር መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ዓላማውም የትምህርት አቀራረቡ ከሁሉም ተማሪዎች የግንዛቤ፣ የስሜት፣ የመግባባትና የአካላዊ ፍላጎት ጋር ተጣጥሞ እንዲከናወን ማገዝ ነው።

መምህራንም ተገቢውን ስርዓተ ትምህርት የማስማማትና አካታች የመማሪያ ክፍሎችን በማስፋፋት ሂደት የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ስርዓተ ትምህርት ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ አካታች የመማሪያ አካባቢ እንዴት እንደሚፈጠርና የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ባሟላ መልኩ ሊደራጅ የሚችል አካታች ስርዓተ ትምህርት እንዴት እንደሚዘጋጅ ጠንቅቀው ሊረዱ ይገባል።

3.1. ስርዓተ ትምህርት

ስርዓተ ትምህርት ሲባል የትምህርት ቅስሞሽ፡

- በትምህርት ቤት አካባቢዎች
- በመኖሪያ ቤት አካባቢዎችና
- በማህበረሰቡ መናኸሪያዎች ሁሉ ሊከናወን የሚችል ስፋት ያለው ሀሳብ እንደሆነ

የሚያስገነዝብ ነው። ስለሆነም፣ በትምህርት ቤት ቆይታ ወቅትና በሂደትም በህይወት ጉዞ ውስጥ ተማሪዎች ስኬታማ መሆን የሚችሉት ዕውቀትና ችሎታቸውን ማለትም የግንዛቤ፣ የስሜት፣ የመግባባትና የአካላዊ መስተጋብሮችን በሁሉም አካባቢዎች የመጠቀም ዕድል ሲያገኙ ብቻ ነው። ስርዓተ ትምህርትን በጠባቡ ካየነው ተማሪዎች ከአንዱ የትምህርት እርከን ወይም መሰላል ወደሌለኛው ከመሸጋገራቸው በፊት ሊወስዷቸው የሚገቡ የኮርስ ዝርዝሮችን ያካተተ ሂደት ይሆናል። ለዚህም በታቀደው የትምህርት ዓላማ ላይ መመስረትንና ይዘትን፣ የትምህርት ልምዶችን፣ ሪሶርስንና መመዘኛዎችን ያካትታል። ከዚህም ባለፈ ምን እንዳስተማርንና ምን እንደተማርን (Context) ትምህርቱን እንዴት እንዳስተላለፍን፣(የመማር ማስተማር ዘዴዎች) እንዴት እንደሚመዘንና፣ (ፈተናዎች) መገልገያ መሣሪያዎችን (መፃህፍትን) ያጠቃልላል።

የተለያዩ የስርዓተ ትምህርት ዓይነቶች እንዳሉ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል፣

- **በመደበኛ ስርዓተ ትምህርት የተደራጀ** የኮርስ ይዘትን ያካተተና በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ላሉ ተማሪዎች የሚያገለግል፣
- **መደበኛ ያልሆነና** በመደበኛው የመማር ማስተማር ፕሮግራም ለመታቀፍ ዕድሉን ያላገኙ ህፃናት ተማሪዎችንና ጎልማሶችን የሚያሳትፍ ሆኖ አትኩሮቱ በማንበብ፣ በመፃፍና በስሌቶች ላይ የሚያተኩር፣
- **ክፍት** (open) የሆነ ስርዓተ ትምህርት ማለትም ልጆች ያለምንም ከልካይ ሊሳተፉበት የሚችሉ ሲሆን ተለማጭ በመሆኑ ይዘቱ፣ ቆይታው፣ መገልገያ መሣሪያዎቹ ሁሉም ተማሪዎች አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ በሚያሳትፍ መልኩ የተደራጀ፣
- **ድብቅ** (hidden) ስርዓት ትምህርት የተጠበቀ ውጤት የማያሳይና የመደበኛው ስርዓተ ትምህርት ዘርፍ አካል ሲሆን መገለጫዎቹም የማህበራዊ ክሂሎት፣ ተራ የመጠበቅ ክሂል፣ ወቅታዊ ጉዳዮችና ባህላዊ ዕሴቶችን የሚያካትት ሲሆን፣
- **ውርስ** (adopted) ስርዓተ ትምህርት የምንለው ደግሞ በመደበኛው የመማሪያ ክፍል ውስጥ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች ለማገዝ መጠነኛ ማስተካከያ እየተደረገበት የሚ ከናወን የትምህርት አቀራረብ ዓይነትን ነው፣

ከማስተካከያዎቹ መካከል ጥቂቶቹም፣

- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማስተናገድ የሚያስችል የማስማማት ስራ መከናወን እንዳለበት መምህራንን የማንቂያ አስተያየት የታከለበት መግቢያ፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ዓላማውን ለዚሁ በሚመች መልክ የመቅረፅ፣
- የመግባቢያ ስልቶችን የመጠቀም (ምልክት ቋንቋ-መስማት ለተሳናቸውና ብሬል ማየት ለተሳናቸው)፣
- የስሜት ህዋሳት ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች ለማገዝ (በመነካካት፣ በማሽተትና ወዘተ) የሚሰጡ ተጨማሪ የማስተማር ስልቶችን የማስተዋወቅና
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የሚመዘኑበት ተስማሚ የምዘና ስርዓትን የሚያመላክትይሆናል።

❖ **ተስማሚ** (adapted) ስርዓተ ትምህርት የምንለው ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማስተናገድ የሚያስችል መሰረታዊ የሆኑ የስርዓተ ትምህርት ማስማማት ተግባራት የሚከናወንበት ሲሆን መለያ ባህርያቱም፣

- ማስማማት ያስፈለገበትን ምክንያት የሚያመላክት፣
- የአቀራረብ ስልቶችንና ቁሳቁሶችን ዓይነት የሚገልፅ፣

- ተማሪዎች ሊማሩዋቸው የሚገባቸውንና መዘለል ያለባቸውን የትምህርት ይዘቶች የሚያመላክት (ለምሳሌ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ድምፅን እንዲከታተሉ አለማስገደድን፣ ማየት የተሳናቸው ተማሪዎች ስለቀለማት ዓይነት በሚገልፁ የትምህርት ይዘቶች አለመጨናነቃቸውን፤ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ተማሪዎች የተለያዩ ቅመራዎችን ተጠቅመው ሂሳባዊ ስሌቶችን እንዲያከናውኑ አለመገደዳቸውንና የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ህፃናት የግድ በጥንቃቄና በንፅህና እንዲፅፉ እንደማይገደዱ) የሚያመላክት፣
- ልዩ የትምህርት መሣሪያዎችን ማለትም የብሬል መሣሪያዎች፣ የጽህፈት መሣሪያዎችና ኮምፒዩተሮችን አስፈላጊነት የሚያመላክትና
- እንደ አካል ጉዳቱ ዓይነት ተስማሚ የሆነ የምዘና ስርዓት የማደራጀት ሂደትን ያጠቃልላል፡፡

❖ **የተለየ** (Specialized) ስርዓተ ትምህርት የምንለው የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሊያግዝ የሚችል የትምህርት ስርዓት አደረጃጀትን ነው፡፡ የማስማማት ደረጃው ከመደበኛው የስርዓተ ትምህርት ከ60 በመቶ በላይ ያለውን የሚሸፍን ሲሆን ይህም በጉዳቱ አስከፊነት ላይ የተመረኮዘ ይሆናል፡፡ ይህ ዓይነቱ ስርዓተ ትምህርትን የማስማማት ተግባር በተለይ ተደራራቢ የአካል ጉዳትና የአዕምሮ ዕድገት ውሱንነት የሚታይባቸውን ተማሪዎች ሊያገለግል እንደሚችል ይታመናል፡፡

❖ **ልዩ** (Specialized) ስርዓተ ትምህርት የምንለው በቅድሚያ በልጁ ላይ ያለውን የመማር ችግር በማወቅ ላይ የሚያተኩርና በችግሩ ዙሪያ ተገቢውን እገዛ የመትለም ሂደትን ያመላክታል፡፡ ለምሳሌ ልጁ (ልጅቷ) የንግግር፣ የመግባባት ወይም የእንቅስቃሴ ችግር ሊኖርበት(ሊኖርባት) ይችላል፡፡ በመሆኑም የተወሰነውን የትምህርት ቤት ቆይታ ከላይ በተጠቀሱት ችግሮች መፍታት ዙሪያ ላይ ያተኮረ ስልት ይቀየሳል ማለት ነው፡፡ ለዚህም የአሠልጣኝና የስልጠና መርሀ ግብር ይነደፍለታል፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በየትምህርት ቤቱ የሚገኙ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራንና ተዘዋዋሪ መምህራን (itinerant teachers) ተገቢውን አገልግሎት ሊሰጡ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

❖ **ተስማሚ** (differentiated) ስርዓተ ትምህርት የምንለው ከተማሪው ችሎታ ጋር ተስማሚና የተጣጣመ ስርዓተ ትምህርት ሲሆን ከተማሪው የአዕምሮታዊ፣ ስሜታዊ፣ የመግባባትና አካላዊ ፍላጎቶች ጋር እንዲዋሃድ ተደርጎ የሚዘጋጅ ነው፡፡ የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎትና ችሎታ ያገናዘበ የትምህርት አቀራረብ አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ረገድ መምህራን የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ይህ መመሪያ የበኩሉን ድርሻ ይወጣል ተብሎም ይታሰባል፡፡ ስለሆነም መምህራን ተስማሚ ስርዓተ ትምህርት በመንደፍ የኮርስ ይዘቶችን ማስተናገድ በሚቻልበት መልኩ የማሳነስ፣

የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችን በተደራጀ መልኩ የመንደፍ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይጠበቃል፡፡

- **ለተመሳሳይ** (homogenous group) አካል የሚዘጋጅ ስርዓተ ትምህርት የምንለው ደግሞ ተመሳሳይ ባህርያት፣ ችሎታና ዝንባሌ ያላቸውን ልጆች ለማገዝ የሚያገለግል ሲሆን እነዚህ ህፃናት ተመሳሳይ አትኩሮትና ፍላጎት እንዳላቸው አስቀድሞ መረዳትን የግድ ይላል፡፡

- **ለተለያየ** (heterogeneous group) አካል የሚዘጋጅ ስርዓተ ትምህርት ደግሞ የተለያየ ፍላጎት፣ ባህርይና ዝንባሌ ላላቸው ተማሪዎች የሚደራጅ ሲሆን በአንድ ክፍል ውስጥ ተመሳሳይና ልዩ የሆነ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች (ለምሳሌ ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ልጆች) እንዳሉ ሁሉ በአማካይ የትምህርት ደረጃና በዝቅተኛ የትምህርት አቀባበል ላይ የሚገኙ ተማሪዎችም ይኖራሉ፡፡ ይህ የማስማማት ተግባር እነዚህን ተማሪዎች እንደየፈርጃቸው ሊያስተናግድ የሚችል ሆኖ የሚዘጋጅ ነው ማለት ነው፡፡

- **የተፋጠነ** (accelerated) ስርዓተ ትምህርት የምንለው የትምህርቱ አሰጣጡ ሂደት በተፋጠነ መልኩ እንዲካሄድ የሚታቀድና በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ተደርጎ የሚተለምን የስርዓተ ትምህርት ማስማማት ተግባርን ነው፡፡ ይህ አደረጃጀት በዋናነት ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማስተናገድ የሚያገለግል ከመሆኑም በላይ በጦርነት በታወኩ አካባቢዎች ለሚገኙ ህፃናትም በጦርነቱ ሳቢያ ያባከኑትን የትምህርት ጊዜያት ለመሸፈን በሚያስችል መልኩ የሚዘጋጅ ስርዓተ ትምህርት ነው፣ በአንፃሩም ያለ ዕድሜያቸው የልጅ እናት የሆኑ ወጣት እናቶችንና ትምህርት አቋራጮችን ከሌሎች ጋር ለማስተካከል ሲያስፈልግ የሚደራጅ የስርዓተ ትምህርት ዓይነት ነው፡፡ ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን በአገራችን እየተተገበረ ያለው የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት ስርዓተ ትምህርት ነው፡፡

3.2. <u>አካታች ሥርዓተ ትምህርት</u>

በአካታች የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በስርዓተ ትምህርቱ አቀባበል ደረጃ በሁለት ወይም በሶስት ደረጃዎች ላይ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ በዕድሜ ደረጃቸው የሚማሩ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከዕድሜ ዕኩዮቻቸው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ዓመት ቀድመው የሚማሩ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከዕድሜ ዕኩዮቻቸው የትምህርት አቀባበል ደረጃ በታች ዝቅ ብለው የሚማሩ ናቸው፡፡

ይህም፣መምህራን በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎችን ለማስተማር የሚያስችሉ ዘርፈ-ብዙ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው፣ ወይም ቢያንስ በክፍል ውስጥ በተማሪዎች መካከል የትምህርት አቀባበል ልዩነቶች መኖራቸውን አውቀው ትምህርቱን ማስማማት እንደሚገባቸው በግልፅ ያስገነዝበናል። የማስማማቱ ስራ ከዕድሜ ዕኩዮቻቸው ፈጥነው የሚማሩትንና በተለይም ልዩ ተሰጥዖና ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎችንም ተጠቃሚ ሊያደርግ እንደሚችል ይታመናል።

በአካታች የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚተገበረው ተስማሚ ስርዓተ ትምህርት አንድ ዓይነት ሲሆን በተቻለ መጠን ግን ለሁሉም ተማሪዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ጨምሮ ተደራሽ ሊያደርግ የሚችል መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፣ በዚህም ረገድ ዝግጅቱ የሚከተሉት ባህርያት እንዳሉት መገንዘብ ያሻል፣

- ያልተጨናነቀና አካዳሚያዊ ይዘቶቹ የተመጠኑ መሆን እንዳለባቸው፣
- በታጋሽነትና በመቻቻል ላይ ተመስርቶ ሰብዓዊ መብትን የተላበሰ መሆኑ የጎላበት፣
- ዕድሜንና ችሎታን ያገናዘበ ለመሆኑ የተረጋገጠና፣
- የአቀራረብ ዘዴዎችንና ስልቶችን በውል ያስቀመጠ መሆን ይጠበቅበታል።

አካታች ስርዓተ ትምህርትን አዘጋጅቶ በተግባር ለመተርጎም በዓለም አቀፍ ሰነዶች ተለይተው የተቀመጡትን የአካታች ስርዓተ ትምህርት ባህርያትን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። እነዚህም ባህርያት፣ ስርዓተ ትምህርቱን ተለማጭ፣ ተገቢና፣ ከዕድሜ ልክ ትምህርት ተከታታዮች ብዝሀ-ፍላጎቶችና ባህርያት ጋር ማጣጣምን (adjustability) ያካትታል።

የአካታች ስርዓተ ትምህርትን ዕውን በማድረግ ሂደት መምህራን ተለማጭ አስተሳሰብ እንዲያዳብሩና የፈጠራ ችሎታቸውንም ከፍ በማድረግ ብዝሀ ፍላጎትን የማስተናገድ ባህርይ የተላበሱ ሊሆኑ ይገባል፤ የሚያስተምሩት ትምህርት ከሚያስተምሩት ተማሪ ጋር ተዛማጅ መሆኑን በውል መገንዘብም ያሻል፣ ለዚህም የማስተማር ደረጃዎችንና ዘዴዎችን በሚገባ በተግባር ማዋል ተገቢ ይሆናል።

3.3. <u>አካታች የመማሪያ ክፍሎችን ስለማደራጀት</u>

የአካታች መማሪያ ክፍሎች አደረጃጀትንና ባህርያቱ ላይ ያተኮረ አተገባበርን በማከናወን ሂደት መምህሩ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ለውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊ ግብዓቶች አዎንታዊ የመማሪያ አካባቢና አዎንታዊ በራስ የመተማመን ባህርያትን መላበስ አስፈላጊ ሁኖ ይገኛል። ስለሆነም ተማሪዎች እያንዳንዳቸው በግለሰብ ደረጃ ሊስተናገዱ እንደሚገባና የእያንዳንዳቸውንም ችሎታ በአክብሮትና አድናቆት ማስተናገድ ተገቢ እንደሆነ ሊሠመርበት ይገባል።

3.3.1 የመማሪያ አካባቢ

ተስማሚ የመማሪያ አካባቢ/ክፍልን/የማደራጀት ተግባር በዋነኛነት የመምህሩ ኃላፊነት ይሆናል። ተማሪዎች እያንዳንዳቸው በግለሰብ ደረጃ እንደሚከበሩ ካወቁ በመካከላቸውም የመከባበር ስሜትን እያዳበሩ ሊያድጉ ይችላሉ፣ በዚህም ሂደት ማንኛውም ሰው ምሉዕ እንዳልሆነና ሁሉም ሰው መሳሳት እንደሚችል ተገንዝበው ያድጋሉ፣ ስለሆነም በትምህርት አቀባበላቸው የመውደቅ ዕጣ-ፈንታ ቢያጋጥማቸውም እንደ ዜጋ ግን ተፈላጊ መሆናቸውን ማሳወቅና ማስገንዘብ ተገቢ ይሆናል፣ በመቻቻልና በመከባበር ላይ ያተኮረ አካባቢን መፍጠር የትምህርቱን ስራ የተሳለጠ እንዲሆን ያደርገዋል፤ በመሆኑም በተማሪዎች መካከል በተለይም በአካል ጉዳተኛና በጉዳት አልባ ተማሪዎች መካከል ያለውን ማህበራዊ መስተጋብር ጤናማ በማድረግ ሂደት መምህራን የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ መገንዘብ ያሻል። ምክንያቱም ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች "አልችልም" የሚለውን አባባል ከህብረተሰቡ እየሰሙ ስላደጉ ተፎካካሪ ዜጎች ሆነው ማደግ እንደሚችሉ በተግባር ማሳየት ይጠበቅብናል። ስለሆነም መምህራንና ወላጆች እንዲሁም ህብረተሰቡ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆች በትምህርቱ ዘርፍ ስኬታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከፍተኛ የሆነ አመኔታና ግምት ሊያሳድሩ ይገባል።

3.3.2 በራስ መተማመን /Self-esteem/

እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ የሚሆንበትን መንገድ በማመላከት ሂደት መምህራን የሚጫወቱት ሚና የሚናቅ አይሆንም፣ ባመዛኙ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ከሌሎች አቻዎቻቸው በተወሰነ መልኩም ቢሆን የተለዩ መስሎ የሚሰማቸው ስሜት እንዳለ ይታወቃል ማለትም እንደሌሎች አቻዎቻቸው ትምህርቱን ፈጥነው ያለመረዳት፣ራሳቸውን እንደሌሎች ተማሪዎች ጠንካራና ጎበዝ ተማሪዎች እንዳልሆኑ አድርጎ የማሰብ ወዘተ.. ናቸው። ይህ አዝማሚያ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው እንዲመለከቱ ይገፋፋቸዋል፣ ስለሆነም አመርቂ የሆነ ውጤት ባያስመዘግቡም ለሚያሳዩት ጥረት ሁሉ አስፈላጊውን ማበረታቻና ድጋፍ ማድረግ እጅግ ጠቃሚ ነው ተብሎ ይታሰባል።

3.3.3 ተስማሚ የማስተማሪያ አካባቢን ማደራጀት

የመማሪያ ክፍሎች ለመማር ማስተማሩ ተግባር አመቺና ለትምህርቱ ስራ አነሳሽ ሆነው መደራጀት ይኖርባቸዋል፣ ይህን ባግባቡ የማደራጀት ተግባር የመምህሩ ሲሆን አደረጃጀቶቹ ከሚያካትቱዋቸው መካከልም፤

- የማጥኚያ ጥግ የማዘጋጀት/Study Corner/፣
- መማሪያ ክፍሉ ካላስፈላጊ እንቅፋቶች/distractions/ የፀዳ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በጥቅም ላይ የማይውሉ ቁሳቁሶችን ከተማሪው ዴስክ ላይ የማራቅ ፣
- ተማሪዎችን ባግባቡ ለማደራጀት የሚያስችሉ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን (Check lists) ማዘጋጀት፣

- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ትርፍ እርሳስ፣ መጽሐፍ፣ ወረቀት ወዘተ በክፍሉ ውስጥ እንዲኖር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- እንዳስፈላጊነቱ ለተማሪው በትምህርቱ መሀል ዕረፍት መፍቀድ፣
- ተማሪው ወደ ውጭ ለመውጣት ሲፈልግ ሊያሳያቸው የሚችሉ ምልክቶችን አስቀድሞ የማወቅ፣
- አደናቃፊ የሆኑና ዕይታን የሚስቡ (አትኩሮትን የሚሹ) እንቅስቃሴዎችን ማስወገድና
- ተማሪው አስፈላጊ የሆነ የእገዛ መሣሪያ ካስፈለገው እንዲጠቀም መፍቀድ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

3.3.4 የትምህርቱን ስራ ማቀድና መተግበር

- ከትምህርት እንቅስቃሴው በፊት በትምህርቱ መጨረሻ ወቅት የሚጠበቀውን ውጤት በግልፅ የማስቀመጥ፣
- ሁሉም ተማሪዎች ለመማር ማስተማሩ ሂደት ራሳቸውን በንቃት ማዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣
- በትምህርት አቀራረቡ ውስጥ የተማሪዎችን ልምድና ፍላጎት ለማካተት ጥረት ማድረግ፣
- በአንድ ጊዜ ሊቀርቡ የሚገባቸውን የይዘት ብዛት የተመጠነ ማድረግ፣
- አስፈላጊና ተጨማሪ የማስተማሪያ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አቅርቦትን ማደራጀት/ማጎልበት፣
- አዳዲስ ክሂሎችን ለማለማመድ የሚያስችል ዕድል መዘጋጀቱን መከታተል፣
- የተማሩትን ክሂል ለማጠቃለል የሚያስችል የተግባር ሥራ መደራጀቱን ማረጋገጥና
- ከተማሪዎች የሚጠበቀው ውጤት በችሎታቸውና በፍላጎታቸው ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ ናቸው፣

3.3.5 ተገቢ የሆኑ የሙከራ ስራዎች (optimal assignments)

ለተማሪዎች የሚሰጡ ተግባራትና የሙከራ ስራዎች ለተማሪው የሚመጥኑና በተገቢው መንገድ አሳታፊ ሊያደርጉ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ተማሪዎች ሳይረበሹና ሳይጨናነቁ እንዲሳተፉበት ካስፈለገ በጣምም የከበደ አብዝቶም የቀለለ አለመሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፣ የሙከራ ስራዎችን ለመስጠት ሲታቀድ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል፣

- የሚሰጡ የሙከራ ስራዎች አጫጭርና ግልፅነትን የተላበሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

- ረዣዥም የፅሕፈት ሥራዎችን ከመስጠት ይልቅ ይህንን ሊተኩ የሚችሉ ሥራዎች ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ፣
- የሚሠሩ ሥራዎችን በርዝመት፣ በይዘትና በጊዜ ወስኖ መስጠት ፣
- በፅሁፍም ሆነ በቃል የሚሠጡ መመሪያዎች በሚታይ ነገሮች መደገፋቸውንም ማረጋገጥ፣
- በፅሁፍ በሚሠጡ መመሪያዎች ዙሪያ ትኩረት የሚደረግባቸውን ጉዳዮች በተለየ መልኩ ማሳወቅ፣
- የሚሠጡ ሙከራዎች በሙሉ ተመዝግበው የሚያዙበት ማስታወሻ /ማህደር/ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣ ይህንንም በፊርማ ማረጋገጥ፣
- ለሙከራዎች በመግለጫነት የሚያገለግል የመግቢያ ሀሳብ፣ የጥናት መመሪያና ማስታወሻ ማዘጋጀት፣
- በሙከራ ስራዎች አጀማመር ሂደትና በኋላም አፈፃፀም ዙሪያ አስፈላጊውን ማበረታቻ መስጠት ናቸው፡፡

3.3.6 የመሸጋገሪያና የጊዜ አጠቃቀምን ከተማሪው ፍላጎት ጋር ስለማጣጣም፤

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የተሰጣቸውን የተግባር ስራ ለማከናወን ከሌሎች አቻዎቻቸው የበለጠ ጊዜን ይፈልጋሉ፤ ለምሳሌ ማየት የተሳነው ተማሪ ለማንበብ የሚፈጀው ጊዜ ማየት ከሚችለው የበለጠ እንደሆን ይታመናል፣ ስለሆነም በምናቅድበት ወቅት ልናስተውላቸው የሚገቡ ነጥቦች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ያካትታሉ፣

- የተሰጣቸውን ሙከራ በሚገባ እንዲተዋወቁትና ከማቴሪያሎችም ጋር እንዲግባቡ የሚያስችል በቂ ጊዜ መሰጠቱን ማረጋገጥ፣
- የተሰጠውን ሙከራ የሚጨርሱበት በቂ ጊዜ መስጠት፣
- የተሰጠውን የሙከራ ስራ በግልፅ ማስረዳት የሚቻልበትን አማራጮች ማስፋት (ምሳሌ በፅሁፍ፣ በንግግር፣ በእንቅስቃሴና በሥዕላዊ መገለጫ)
- የተሰጣቸውን የሙከራ ስራ እያከናወኑ በየመሀሉ የሚያርፉበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- የቤት ሥራ ሠርተው የሚመጡበት ጊዜ በቂ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- ከአንድ ተግባር ወደሌላው በሚደረግ የሽግግር ወቅት በቂ ማስታወሻና ማጠቃለያ ሀሳብ በማቅረብ መረዳታቸውን ማረጋገጥ፣
- የሚሰጡ ተግባራት አሠልቺ እንዳይሆኑና ከተማሪዎች ችሎታ ጋር ተመጣጣኝ ለመሆናቸው አስቀድሞ ጥንቃቄ ማድረግን ያጠቃልላል፣

3.3.7 ድግግሞሽ፣

አብዛኞቹ የልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳብን በቶሎ የመረዳትና የመገንዘብ ችግር ስላለባቸው አዳዲስ መረጃዎች በሚቀርቡበት ወቅት ደጋግሞ ማስገንዘብ የግድ ይላል፣ በመማር ማስተማር ወቅትም መምህራን ይህንን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ በዝግታ የማስገንዘብና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደጋግሞ የማሰረዳት ትዕግስትን ሊላበሱ ይገባል፣

3.3.8 ድጋፍ፣

ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ልጆች በተጨማሪ ድጋፍ ለማበረታታት ጊዜ መውሰድ ያስፈልጋል፤ ይህንን ለማድረግ መምህራን የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎች የሚያከናውኑበትን መንገድ በአግባቡ ማደራጀትና በግል ሊታገዙ የሚገባቸው ልጆች ካሉም አትኩሮት ማድረግ እንደሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፣ በተጨማሪም የቀደመውን (ያለፈውን ክፍለ ጊዜ) ትምህርት የመከለስ፣ ደጋግሞ የማስገንዘብና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተማሪዎቹን የሚገዳደሩ ተግባራት ሲያጋጥሙ በድጋሚ ማስተማር ተገቢ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በተለይ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስልጠና የወሰዱ መምህራንና ተዘዋዋሪ መምህራን በዚህ ረገድ ሊያበረክቱት የሚችሉት አስተዋፅኦ ቀላል አይሆንም፤ ከመደበኛው ትምህርት መምህር ጋር በጣምራ የማስተማር ተግባርን ማለማመድ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ተገቢ ነው፤ በልጁ የመቀበል ክሂል ላይ በመንተራስም ተጨማሪ እገዛ በትምህርት ቤቱ የተጓዳኝ ትምህርት ማዕከል ውስጥ ማደራጀት ተገቢ ይሆናል፣ ከዚህም ባሻገር በቡድን የመማር-ማስተማር ስልት የልጁን ተሳተፎ ከፍ ማድረግ ይጠበቃል፣ ባጠቃላይ አነጋገር ተማሪው በአስተማማኝ መልኩ ከመምህራን ድጋፍ ሊያገኝ እንደሚችል ሙሉ እምነት ሊያሳድር የሚችልበት መንፈስ ማጎልበት ያስፈልጋል፣ ለበለጠ ተሳትፎም ወላጆችን፣ የተማሪውን ወንድምና እህት እንዲሁም ሌሎች በጎ አድራጊዎችን በመጋበዝ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

3.3.9 የመማሪያ፣ አካባቢን ማመቻቸት (Managing behavior in the classroom)

ሁሉም ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ አካባቢ ሊከተሉዋቸው ስለሚገቧቸው ህጎችና ወሰኖች በግልፅ እንዲያውቁና እንዲተገብሩት ማድረግ ተገቢ ነው። የክፍል ውስጥ ጤናማ መንፈስ በማስፈን ሂደት መምህራን የሚጫወቱት ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፤ የተማሪዎቻችንን ባህርይ አስቀድመን ካላወቅንና ለመቆጣጠር ዝግጁነት ከጎደለን አላስፈላጊ በሆኑ ባህርያት ሳቢያ ሊከሰት የሚችለውን ተግዳሮት መቋቋም ሊያዳግት ይችላል።

በመሆኑም የተማሪውን ህልውና በማይጋፋ መልኩ አላስፈላጊ ባህርይን ከልጁ ላይ ለማስወገድ መጣር እጅግ ጠቃሚ ነው ተብሎ ይታሰባል። ይህም ማለት ተማሪውንና ባህርዩን ለያይቶ ማስተዋል ተገቢ ነው ማለት ነው፣ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ነጥቦች ለመምህራን በመነሻነት ሊጠቅሙ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል፡

- በመከባበር ላይ ያተኮረ የክፍል ውስጥ ህጎችን ማውጣት፣
- ከተማሪው ጋር እስጥ-አገባ ውስጥ አለመግባት፣
- በተምሳሌነት ሊያስጠቅስ የሚቻል ተግባርን ካላስፈላጊ ተግባራት ለይቶ ማሳወቅ ፣
- አላስፈላጊ የምንላቸው ባህርያት ምን እንደሆኑ ተማሪዎቹ የሚረዱበትን ዘዴ ወይም መለያ ማደራጀት፣
- አላስፈላጊ ትኩረትን ለመሳብ ለሚሹ ባህርያትና ግለሰቦች ቦታ አለመስጠት፣
- የሥነምግባር መርሆዎችን ሁሉም ተማሪዎች ሊያዩትና ሊተገብሩት በሚችሉበት መልኩ ማስቀመጥ/መለጠፍ/እንዲረዱዋቸውም ደጋግሞ ማስገንዘብ፣
- በቀላሉ ሊተገበሩ የሚችሉና ከአቅም በላይ ያልሆኑ የባህርይ ማስወገጃ ዘዴዎችን አስቀድሞ ማዘጋጀት፣
- አላስፈላጊ ባህርያትን በማስወገድ ሂደት መሻሻል ለሚያሳዩ ተማሪዎች አፋጣኝ ግብረ-መልስና ማበረታቻ ማድረግ፣
- የትምህርት ስርዓታችን (Curriculum) ሁሉንም ተማሪዎች የሚስብና ላላስፈላጊ ባህርያት የሚጋብዝ አለመሆኑን ማረጋገጥ፣
- አላስፈላጊ ናቸው ተብሎ የሚታሰቡ ባህርያት እነማን እንደሆኑና መነሻ ምክንያታቸውንም የመከታተያ ፎርም ማዘጋጀት፣ በምልከታ አማካይነትም የመከታተል ሂደትን ማጎልበት የመሳሰሉት ናቸው።

3.4 <u>ስርዓተ ትምህርቱን ስለማስማማት</u>

በመማር-ማስተማሩ ሂደትና ብሎም ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማገዝ በሚደረግ እንቅስቃሴ ዙሪያ ስርዓተ ትምህርት የማስማማት ተግባር የሚጫወተው ሚና ቀላል አይደለም፣ የማስማማቱ ሥራ በብዙ መንገዶች፣ በብዙ ምክንያቶች ሳቢያና ለበርካታ ተፈላጊ ውጤቶች የሚተገበር ሲሆን እንደሁኔታዎች፣ የትምህርት ዓይነቶችና ተግባራትም የሚለያይ ነው። እያንዳንዱ መምህር፣ ተማሪና መማሪያ ክፍል የተለየ እንደመሆኑ የማስማማቱም ሥራ እንደዚሁ በነባራዊውና ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል።

የማስማማት ሥራ፣ ከተማሪው ምን እንደሚጠበቅና አዳዲስ ክሂልና ዕውቀትን ከማስጨበጥ አንፃርም ለውጥ ማስፈለጉ ላይ ያመዝናል። ከተማሪዎች ወቅታዊ ችሎታ ጋር በማገናዘብ መምህራን ተማሪዎቻቸው ምን መማር እንደሚፈልጉ፣ እንዴት መማር እንደሚፈልጉና የተማሩትን በምን መልክ ማሳየት እንደሚችሉ ማቀድም ይጠበቅባቸዋል፣ በተጨማሪም የትምህርት አቀራረቡ በምን መልክ መስማማት እንዳለበትና እያንዳንዱን ተማሪ ሊደርስ በሚችል መልኩ ለማዘጋጀት እርግጠኛ መሆን

ይገባቸዋል፣ በዚህ ረገድ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራንና ተዘዋዋሪ መምህራን ሚና የማይናቅ ነው፡፡

ስርዓተ ትምህርት 4 ክፍሎች ሲኖሩት እነዚህም ይዘት፣ የማስተማር ዘዴ፣ የትምህርት መሣሪያዎችና ምዘናን ያካትታል፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለመድረስም ከእነዚህ በላይ በተዘረዘሩት ክፍሎች ዙሪያም የማስማማት ተግባር መከናወን ይኖርበታል፡፡

3.4.1 ይዘትን ስለማስማማት

በአካታች ስርዓተ ትምህርት ተማሪዎች በስርዓተ ትምህርቱ ይዘት ሥር የተካተቱትን ፅንሰ ሀሳቦች በሚገባ እንዲከታተሉ መምህሩ ራሱን ከሁኔታዎች ጋር ማጣጣም ይጠበቅበታል፣ ይዘት ስንል እውነታዎችን፣ ፅንሰ ሀሳቦችን፣ የተለያዩ መርሆዎችን ወይም ማጠቃለያዎችን፣ አመለካከቶችንና ከሚቀርበው ትምህርት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ክሂሎት ያካትታል፣

በአካቶ ትምህርት ስርዓት ዋነኛው ትኩረት ተማሪዎችን ከመሠረታዊ ትምህርት አቅርቦት ጋር እንዲገናኙ ተደራሽነትን ማስፋት ነው፡፡ ለዚህም ትምህርቱን ተስማሚ አድርጎ ማቅረብ የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የተጨናነቀ ይዘትን ለማስወገድ በማስማማት ተደራሽነትን ማመቻቸት ይገባል፡፡ ይዘት መምህሩ ለተማሪዎች ለማቅረብ የሚያቅደውን፣ ተማሪዎች ትምህርቱን እንዴት እንደሚቀበሉት መረዳትንና የትምህርት ቅስሞሽን ያጠቃልላል፡፡ ተስማሚ በሆነ የክፍል ውስጥ አደረጃጀት የምንመራ ከሆነ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች፣ ለማስረዳት የሚቀርቡ የትምህርት መሣሪያዎችና ክሂሎች ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፉ ይሆናሉ፡፡ ይዘቶችን ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ በማድረግ ሂደት ከመምህሩ ከሚጠበቁ ተግባራት መካከል ጥቂቶቹ፤

- ተማሪዎች አዳዲስ ፅንሰ ሀሳብን በተገቢው መንገድ እንዲገነዘቡ ተጨማሪ መሣሪያዎች ማቅረብ፣
- በተለያዩ መንገዶች ሊገለፁ የሚችሉ ትምህርቶችን የማዘጋጀት፣
- ተጨማሪ ገለፃና መረጃ ለሚፈልጉ ተማሪዎች የሚሆን ዝግጅት የማሰናዳት ፣
- የመማሪያ መፃህፍትን፣ ቴፕሪኮርደር፣ ፓስተርስና ቪዲዮ ለመጠቀም የሚያስችል ዝግጅት ማከናወን ናቸው፡፡

አንዳንድ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ዙሪያ የማስማማት ሥራን የሚፈልጉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በአንድ ወይም በተወሰነ የትምህርት ዓይነት ብቻ የማስማማት ተግባርን የሚፈልጉ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም የማስማማት ሥራ በተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች ላይ ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ መምህራንም በይዘቱ ዋና ዓለማ ላይ በማተኮር ብቻ ትምህርቱን የማስማማት ሥራ መሥራትም ይጠበቅባቸዋል፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ፍጆታ ሲባል በርካታ መረጃዎችን በአንድ ጊዜ

ለመስጠት ከማሰብ በተወሰኑ መረጃዎች ላይ ያተኮረ መረጃ ለመስጠት መዘጋጀት ተገቢ ይሆናል። ይህም ከመረጃዎች መብዛት የተነሳ በልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን መጨናነቅ ይቆጥባል ወይም ይቀንሳል፣

የተማሪዎችን የመገንዘብ ክሂል ግምት ውስጥ በማስገባት የአትኩሮት፣ የማስተዋልና የማስታወስ ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል የማስማማት ተግባር ማከናወን ጠቃሚ ነው። በሌላ በኩል ስርዓተ ትምህርቱን የማስማማት ሥራ በተማሪው የህይወት ክሂል ላይ አትኩሮት ማድረግ እንዳለበትም ይታመናል፣ ይህም ማለት አንዳንድ ተማሪዎች አካዳሚክ የሆነውን የትምህርት ይዘት ለመከታተል ስለሚያዳግታቸው ቀሪ ህይወታቸውን በተሻለ መንገድ መምራት የሚችሉበትን የህይወት ክሂሎት ማስጨበጥ ይገባል።

የህይወት ክሂሎችን ለማስጨበጥ የሚያግዙ ነጥቦችም፤

- ከተማሪው የህይወት ገጠመኝ ጋር ተዛማጅነት ያለው ይዘት ላይ የማተኮር ፣
- ክሂሎች ያልተጨናነቁና በቀላል ዘዴ መቅረባቸውን ማረጋገጥ፣
- የሚቀርቡ ይዘቶች መጠንና ስፋት ውስን መሆኑን ማረጋገጥ ፣
  (ለምሳሌ የአምስት አገራትን ሁለት ሁለት መረጃ አቅርብ ከማለት የአንድ አገር ሦስት መረጃ እንዲያቀርብ መጠየቅ፣) ወዘተ...
- የሚፈለጉ ውጤቶችን መጠን መቀነስ (ለምሳሌ ልጁ ሊገነዘብ የሚገባውን የቃላት መጠን አለማብዛት)፣
- ሁለት ተቀራራቢነት ያላቸውን መረጃዎች በተለያዩ ጊዜ ከማቅረብ አዋህዶ ባንድ ላይ የማቅረብ፣
- አቀራረቦች ሁሉ በተማሪው ምርጫ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ የመሳሰሉት ናቸው።

3.4.2 የማስተማር ዘዴን ተስማሚ ስለማድረግ

የማስተማሪያ ስልትን ማስማማት የመምህሩን የአቀራረብ ዘዴም እንዲለወጥ ያግዛል። መምህራን እያንዳንዳቸው ተማሪዎች የተለየ የትምህርት አቀባበል ዘዴ፣ (ተቀፅላ 1) የመጡበት አካባቢ፣ ልምድና የመማር ፍላጎት እንዳላቸው በመገንዘብ ሁሉንም ሊያካትት የሚችል የማስተማር ዕቅድ መንደፍ እንደሚገባቸው መረዳት ይገባል። ውጤታማ የማስተማር ስልት የምንለውም የተለያዩ የመማር ማስተማር ስልቶችን በማቀናጀት የማቅረብን ሂደት ነው። በዚህ ረገድ ከተመራን ስርዓተ ትምህርታችን

ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች ተዛማጅና አካታች ይሆናል ማለት ነው። እንደሚታወቀው ልዩ ፍላጎት የሚፈጠረው ስርዓተ ትምህርቱ ሁሉንም ተማሪዎች አካቶ የማስተናገድ አቅም ሲያንሰው ነው።
የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችንና የቡድን አደረጃጀትን አትኩሮት ሰጥተን የምንጠቀም ከሆነ የማስተማር ስልታችንን ከመምህር-ተኮር ወደ ተማሪ ተኮር አሸጋገርነው ማለት ይቻላል። ይህ ሂደትም ለተማሪው በራሱ ተመራምሮ የመማር ነፃነትን ከማጎናፀፉ ባሻገር መምህሩ ልዩ እገዛ የሚፈልጉ ተማሪዎችንና ቡድኖችን ለማገዝ አመቺ ጊዜና ሁኔታን ያመቻችለታል። በርካታ የመማር ማስተማር ስልቶችን (በህብረት የማስተማር፣ በህብረት የመማር፣ በራስ አቅዶ የመማር ..ወዘተ) የሚጠቀሙ መምህራን የመማሪያ ክፍሉን ህይወት ያለውና ቤተሰባዊ ስሜትን የሚላበስ ሊያደርጉት ይችላሉ።

3.4.2.1 በህብረት የማስተማር ዘዴ

በህብረት የማስተማር ዘዴ ዕውን የሚሆነው ተማሪዎች በትናንሽ ቡድኖች ተደራጅተው በግልም ሆነ በቡድን የሚሰጣቸውን ሥራ በመረዳዳት እንዲያከናውኑ ሲደረግ ነው። ይህ አደረጃጀት በሁለት መልኩ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል።

1. በህብረት በመሥራት የሚያስመዘግቡት ውጤት እያንዳንዳቸው በተናጠል ሊያስመዘግቡት ከሚችሉት ውጤት እጅግ የላቀ እንደሆነና፣
2. የትምህርት ቅስሞች በባህርይው ማህበራዊ በመሆኑ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ሳይቀር በርካታ ቁም ነገሮችን ሊጨብጡ እንደሚችሉ ያስገነዝባል።

በህብረት የማስተማር ዘዴን ውጤታማ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ዋነኛው በርካታ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ትናንሽ የመማሪያ ክፍሎችን እንደመፍጠር ስለሚቆጠር ጭምርም ነው። ይህም መምህሩ ቡድኖችንም ሆነ እያንዳንዱን ተማሪ የማገዝ በቂ ጊዜ ይኖረዋል ማለት ነው።

ተማሪዎች በተለያዩ ቡድኖች በመደራጀት በሠሩ መጠን የልምድ መቅሰም አድማሳቸው የዚያኑ ያህል እየሠፋ ይሄዳል። ለዚህም ሲባል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተዘረዘረው መልክ ሊደራጁ ይችላሉ።

- አጠቃላይ ቡድናዊ አደረጃጀት ማለትም መላውን የክፍል ተማሪ በሚያስችል መልኩ የማስተማር ስልት ሲሆን ይዘቱ ሁሉንም ተማሪዎች እንዲያሳትፍ የማስማማት ተግባር አስቀድሞ ሊከናወን ይገባል። ይህ ዓይነቱ የማስተማር ዘዴ በተለይ መምህሩ ተማሪዎችን በጥያቄና መልስ መልክ ለማወያየትና የትምህርቱን ርዕስም በተገቢው መልክ ለማስተዋወቅ የሚያስችል ዘዴ እንደሆነ ይታመናል።
- አንድ-ለአንድ የማስተማር ዘዴ የሚባለው ደግሞ የተለየ እገዛ የሚያስፈልገው ልጅ ቢኖር (ትምህርት በማቋረጡ ሳቢያ ያባከነው ክፍለ ጊዜ ካለ፣ የመማር ችግር ካለበት፣ ወይም

ለትምህርት ቤቱ አዲስ ከሆነና ልዩ ተሰጥዖ ካለው) ተጨማሪ ተግባራት እንዲያከናውኑ ሲታሰብ የሚታቀድ ነው፡፡

- በአናሳ (ትንሽ) ቡድን የማደራጀት የምንለው ደግሞ መላውን የክፍል ተማሪ በበርካታ ትናንሽ ቡድኖች በማደራጀት የማስተማር ዘዴን ሲሆን መምህሩ አንደኛው ቡድን ጋር እገዛ ሲያደርግ የተቀሩት በራሳቸው መሪነት እየሠሩ ይቆያሉ፡፡ በዚህም ሳቢያ እያንዳንዳቸው የመረዳዳትና የመተጋገዝ ባህርይን እያዳበሩ ስለሚሄዱ በተለይ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ከዚህ አደረጃጀት በሚገባ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ በትክክል እንዲተገበርም መምህሩ አጠቃቀሙ ላይ በቂ የማስተዋወቂያ ስልጠና መስጠት ይኖርበታል፣ በተግባር ልምምድም እያዳበሩት ይሄዳሉ፡፡ የመምህሩ ክትትልና አመራር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነም ይታመናል፡፡ የልጆቹ አደረጃጀትም ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸውን በአንድ ላይ በማድረግ፣ የተለያየ ችሎታ ያላቸውን ልጆች አንድ ላይ በማድረግና ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸውን በአንድ ላይ በማድረግ ጭምር ማደራጀት ይቻላል፡፡
- ዝቅተኛ ችሎታ ያላቸው ቡድኖች አደረጃጀት የሚባለው ደግሞ በትምህርት ቅስሞች ተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያሉና ትምህርት የመቀበል አቅማቸው ከሌሎቹ የተለዩትን ተማሪዎች ለመርዳት ታስቦ የሚደራጅበትን ዓይነት ያመለክታል፡፡ ይህ ባብዛኛው የሚመቸው ተጨማሪ እገዛና ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን በመለየት አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ ሲያስፈልግ ነው፡፡
- የተለያየ ችሎታ ያላቸውን በጋራ የማደራጀት ዘዴ ደግሞ የተለያየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ያላቸውን ዕምቅ ችሎታ ለሌሎች ለማካፈል እንዲችሉ ታስቦ የሚዘጋጅ ሲሆን ችግሮችን ለመፍታት፣ የቤት ሥራዎችን በጋራ ለመሥራትና እያንዳንዱ ተማሪ ችሎታው ላይ ባተኮረ መንገድ ሌሎችን ለማገዝ ዕድል የሚያገኝበት መድረክን ማመቻቸት ማለት ነው፡፡ ዘዴው ባመዛኙ ተማሪዎች የፕሮጀክት ሥራ ሲሰጣቸውና ተዘጋጅተውበት ክፍል ውስጥ የሚያቀርቡት ሥራ ሲሰጣቸው የሚጠቅም ይሆናል፡፡
- ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸውን በአንድ ላይ የማደራጀት ዘዴ ደግሞ በፍላጎታቸው ከተመደቡ ለመማር ማስተማሩ ተግባር መነቃቃትን ይፈጥርላቸዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም ርዕሱ እንደተጠበቀ ሁኖ ለልጆቹ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በመስጠት የኮርስ ይዘቱን እንዲሸፍኑ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አንድን ተመሳሳይ ተግባር ብንወስድ፣ አንደኛው ክፍል ታሪኩን ይፅፋል፣ ሁለተኛው ደግሞ የተስተካከሉ ዓረፍተ ነገሮችን ብዛት ይመዘግባል፣ ሦስተኛው ወገን ደግሞ የታሪኩን ምስል በፎቶግራፍ (ፖስተር)መልኩ እንዲቀርፅ በማድረግ የተሰጠውን ተግባር እንዲረዱት ማድረግ ይቻላል፡፡

በህብረት የማስተማር ዘዴ 4 ዋና ዋና ክፍሎች አሉት

- የመረዳዳት ባህርይንና መንፈስን የማላበስ፣ የቡድኑ አባላት በተናጠልና በጋራ የቡድኑን ዓላማ ለማሳካት እንዲጥሩ ይረዳል፣
- እያንዳንዱ አባል በግል ተጠያቂነትን የማሳደር፣ ለመማር ማስተማሩ ስኬት በግልም ሆነ በቡድን እያንዳንዱ አባል ተጠያቂ እንደሆነ ያስገነዝባል፣
- የመተጋገዝ ባህርይን የማጎልበት፣ ችግሮችን ማቃለልን፣ መወያየትንና መተባበርን ያሰፍናል፣
- በመጨረሻም የግምገማን አስፈላጊነት የማስገንዘብ፣ ቡድኑ ሥራውን በመገምገም በቀጣይነት በድክመት የተመዘገቡትን በጠንካራ ጎን ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት የሚያመለክቱ ክፍሎች ይኖሩታል፣

በህብረት የማስተማር ዘዴን ለማጎልበት ጊዜ፣ ልምምድና ተፈላጊ ባህርያትን የማበረታታት ክሂል መላበስ የግድ ይላል። ከዚህ ዘዴ ተጠቃሚ ለመሆን እያንዳንዱ የቡድኑ አባል የመደማመጥ ባህርይን መላበስ፣ የእያንዳንዱ ሃሳብ ተከባሪ መሆኑን ማረጋገጥና አዎንታዊ አስተሳሰብን ማራመድ ተፈላጊ ሁኖ ይገኛል። በመሆኑም ተማሪዎች ሃላፊነትን የመወጣትና የመተጋገዝ ባህርይ ተላብሰው እንዲያድጉ በማድረግ ሂደት መምህራን የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም።

3.4.2.2 በህብረት መማር (አቻ ለአቻ ትምህርት) Peer tutoring

በህብረት መማር የሚያተኩረው ህፃናት ባብዛኛው ከአቻ ጓደኞቻቸው ጋር የተሻለ ቀረቤታ ስላላቸው ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ለትምህርት ስራ ማዋል ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ ነው። ይህም ማለት በመምህሩ ተከታታይነት አንደኛው ተማሪ እንደ አስረጅ ሁኖ ለሌላኛው ገጠመኙን የሚያካፍልበት መድረክ ማመቻቸት ማለት ነው። በራስ የመተማመን ስሜትን ለማላበስና በትምህርት ተሳትፎ ረገድ ያላቸውን ሚና ለማሳደግ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችም ገጠመኛቸውንና የትምህርቱን ይዘት በአስረጅነት መልክ እንዲያቀርቡ ዕድል መስጠት ተገቢ ይሆናል። ዘዴውን በማንኛውም የትምህርት ዓይነት ዙሪያ መጠቀም የሚቻል ሲሆን ሌሎች የማስተማር ዘዴዎችን ለማገዝ የሚረዳ ተጨማሪ መንገድ አድርጎ መጠቀምም ይቻላል። የህብረት መማር ጥቅሙም፣

- የእያንዳንዱን ተማሪ የግል ፍላጎት ሊያሟላ ይችላል፣
- አብረው በሚሠሩ ተማሪዎች መካከል የጋራ መግባባትና መከባበርን ያዳብራል፣
- ኃላፊነትን የመወጣት ባህርይ እንዲላበሱና የተማሩትን በውል እንዲገነዘቡት ይረዳል፣
- የመደማመጥ፣ የማተኮርና የመረዳት ችሎታን ያዳብራል፣
- በመምህሩ ሊገኙ የማይችሉ ተጨማሪ ተሞክሮዎች በተማሪዎቹ አማካይነት ሊዳብሩበት ይችላል፣

- ተማሪዎች ከጎልማሶች በተለየ የመግባቢያ ስልት ማለትም በአቻነትና በጓዳዊ ስሜት ስለሚረዳዱ የመማር-ማስተማሩን ሂደት ይበልጥ ያሰልጠዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡

3.4.2.3 ራስን በመምራት የመማር ዘዴ /Self - regulated–learning/

ተማሪዎች ከአስተማሪያቸው ውጭ ነፃ ሆነው ለመማር ይፈልጋሉ፣ ምኞታቸውም ነው፡፡ ራስን በመምራት የመማር ዘዴም ተማሪዎች ራሳቸው ግብ ጥለውና የራሳቸውን ባህርይ መቆጣጠር የሚችሉበት ዘዴ በመቀበል ውሳኔ ላይ የመድረስና ለዓላማቸው መሳካት እንዲጥሩ ማበረታታትን ያካትታል፣ ይህ ዘዴ ሁሉንም ተማሪዎችና ማንኛውንም የትምህርት ዓይነት በሚገባ ለመከታተል እንደሚያመች ይታመናል፤ ለዚህም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች በመነሻነት ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

- በፍላጎታቸውና በምርጫቸው ላይ ያተኮረ ዓላማ/ግብ/ እንዲነድፉ ማድረግ፣
- የተጣሉትን ግቦች ለማስፈፀም የሚያስችል የተግባር ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ማበረታታት፣
- በግባቸው መሠረት እያከናወኑ መሆኑን የሚከታተሉበትን ዘዴ ማስገንዘብ፣
- ግባቸውን በየወቅቱ እየከለሱ የሚያሻሽሉበትን መንገድ ማሳየት ተገቢ ይሆናል፡፡

3.4.2.4 በህብረት ማስተማር

በህብረት ማስተማር የሚባለው መምህራን ከሌሎች ባለሙያዎች እንዲሁም ከወላጆች ጋር በመሆን በጋራ የሚያስተምሩበት ስልት ነው፡፡ ዘዴውም ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ አስፈላጊ ግብዓት እንደሆነ ይታመናል፤ የተለያየ ዓይነት የህብረት ማስተማር ዘዴዎች ሲኖሩ እነሱም፣ የመደበኛ ክፍል መምህራን ከልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን፣ ከተዘዋዋሪ መምህራንና ከሌሎች የተለያየ ሙያ ካላቸው ባለሙያዎች ማለትም (የጤና፣ የማህበራዊ አገልግሎትና ቴራፒስቶች) ጋር በመሆን የማስተማር ዘዴን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በህብረት የማስተማር ዘዴ አብሮ የመስራት ክሂል መላበስን ይጠይቃል፣ በተለመደው የማስተማር ዘዴ ብቻ መመራት መምህሩ ብቻውን እንዲያስተምር የሚያስገድድ ሲሆን በዚህኛው ዘዴ ግን የማስተማሪያ ክፍሉ ከግላዊነት ወደ ማህበረሰብነት ይቀየራል ማለት ነው፡፡ ለውጤታማነቱ በተገቢው መንገድ መታቀድ ሲኖርበት ተግባሪ አካላትም ኃላፊነትንና የሙያ ተዋፅኦን በተገቢው መንገድ እንዲወጡ ይጠበቃል፡፡

አጠቃላይ መርሁም፣

- በህብረት የሚሠራበት የጋራ ግብ መንደፍን፣

- የጣምራ ኃላፊነትና የስራ ድርሻን በውል የማስቀመጥን፣
- እያንዳንዱ የቡድኑ አባል የችግሩ አካል ሳይሆን የመፍትሄው አካል የመሆንን፣
- የጋራ መተማመንና መከባበርን የማስፈን፣
- የመማማር ተነሳሽነትን የማዳበር፣
- በጋራ ስምምነት ላይ በተመሠረተ አግባብ ውሳኔ ላይ መድረስን፣
- አፋጣኝ የሆነ ግብረ መልስና ማስተካከያ የመስጠትና የአባላትን ሃሳብ የማክበርን፣
- ባለመግባባት ዙሪያ ስለሚወሰድ መፍትሄ በጋራ የመምከርንና
- እንቅስቃሴዎችን ለመገምገም ሚያስችል መደበኛ ስብሰባ ማካሄድን ያካትታል፡፡
- የህብረት የማስተማር ዘዴ ዋና ዋና ጥቅሞችም
- ኃይልን/አቅምን /ይገነባል፣
- መምህራን እርስ በርስ የሚማማሩበት መድረክ ይፈጥራል፣
- ልዩ ፍላጎት ላለቸው ተማሪዎች የሚደረገው የእገዛ ስርዓት እንዲጎለብት ይረዳል፣

3.4.2.5 የጣምራ ማስተማር ዘዴ (Co teaching)

የጣምራ ማስተማር ዘዴ በህብረት የማስተማር ዘዴ አካል ሲሆን የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህሩና የመደበኛው ክፍል መምህር ልዩ ፍላጎት ያለውን ልጅ ለሙሉ ቀንም ሆነ ለተወሰነ ጊዜያት ለማገዝ የሚያስችል ዘዴን ያካተተ ስርዓት ነው፡፡

በጣምራ የማስተማር ዘዴ ጠቀሜታም፣

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በቀለም ትምህርትም ሆነ በማህበራዊ ዘርፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያግዛል፣
- መምህራን በማስተማሩ ዘርፍ ሙያቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳል፣
- ሙያዊ እርካታን ያጎናፅፋል፣
- ትምህርታዊ እገዛ ለመስጠት የሚያስችል ስሜትን ያዳብራል፣

ለጣምራ የማስተማር ዘዴ አስፈላጊ ሁኔታዎች

- ተማሪዎችን ለመርዳት በጋራ የማቀድ በጋራ የማስተማርና በጋራ የመገምገም፣
- ሁሉንም ተማሪዎች በትምህርት ለማገዝ ሙያዊ መከባበርን ማጎልበት፣

- ከትምህርት ቤቱ ከሚገኝ ገቢ ለመማር ማስተማሩ ተግባር አስፈላጊ ድጋፍ የማድረግ፣
- በቂና መደበኛ የሆነ የማቀድና ሃሳብ የመለዋወጥ ልምድ ማዳበር፣
- ተግዳሮቶችን (የትምህርት፣ የትምህርት ዓላማዎች፣ የትምህርት አወቃቀርና ምዘና ስርዓትን) ለመፍታት የጋራ ስልት መንደፍ፣
- ከወላጆች ጋር በግልፅ የመወያያ መድረክ የማዘጋጀት ናቸው።

3.4.3 የማስተማር ዘዴና መሣሪያዎችን ተስማሚ ስለማድረግ

የማስተማሪያ ዘዴንና መሣሪያዎችን ማመቻቸት ስንል ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ሊጠቀሙበት የሚገባቸውን ተገቢ የሆነ መሣሪያ የማቅረብና ለነሱ የማይመቹትን እስከ መተካት ያካትታል። የማስተማሪያ መሣሪያዎችንና ዘዴዎችን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እንዲመች አድርጎ የመምረጥና ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግ አሰፈላጊ ነው። ለምሳሌም፣

- ፅሁፎችን ተነባቢ ለማድረግ ቃላቶችን አተልቆ መፃፍ
- ተማሪዎች ምዘናን በቃልም እንዲወስዱ የመፍቀድና በክፍል ውስጥ ማስታወሻዎች ዙሪያ ልዩና አትኩሮት የሚሹ ጉዳዮችን በተለየ ቀለም ማመላከት፣
- የትምህርት ይዘቱን በይበልጥ ለማጉላት በተለየ አፃፃፍ ማስቀመጥ፣ አዳዲስ ቃላትን ከሌሎች ለየት እንዲሉ ጎላ ማድረግ፣ ምህፃረ ቃላትን በተገቢው መንገድ የመግለፅና ማጠቃለያ ሃሳቦችን መጥኖና አስማምቶ ማቅረብ፣
- በፅሁፍና በእይታ የሚቀርቡ መግለጫዎችን የሚተኩ (የምልክት ቋንቋ አገልግሎትና ወደ ብሬል የተለወጠ/የተቀየረ/) ማስታወሻ ማዘጋጀት ፣
- በንግግርና በንክኪ የሚቀርቡ ትምህርቶችን ሊተኩ የሚችሉ ተጨማሪ መግለጫዎች፣ የብሬል አግልግሎትና የመሳሰሉትን የማዘጋጀት፣
- በማስተማርም ሆነ በምዘና ወቅት ትላልቅ ፅሁፎችን የመጠቀም፣ ምዘናዎች በቃል መግለጫም መደገፋቸውን ማረጋገጥና አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ የስሌት መኪና (Calulator) እንዲጠቀሙ የመፍቀድና
- ተጨማሪ የመማር ማስተማር መሣሪያዎችን ማደራጀት ተገቢ ይሆናል።ባጠቃላይ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ተስማሚ ለማድረግ የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ነው።

- የተማሪውን ወቅታዊ የትምህርት አቀባበል ደረጃ፣ (ከትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ ዘዴ ጋር በማነፃፀር)፣
- የትምህርት መሣሪያው ከግል የትምህርት መርሀ ግብር ግብና ዓላማ ጋር አብሮ የሚሄድ መሆኑን፣
- የትምህርት መሣሪያቹ የተማሪዎችን ዕድሜ ያገናዘቡ መሆናቸውን፣
- የትምህርቱ ክብደት ከልጁ ወቅታዊ ችሎታ ጋር መጣጣሙን፣
- የሙከራ ስራዎች/ assignment/ መጠን ያልተንዛዛ መሆኑን፣
- ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ሰዓት እንደሚያስፈልግ የማመን ፣
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ የማሳተፍና
- በድጋፍ መስጫ የትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀም ዙሪያ የአጠቃቀም ስልጠና ማከናወን ተገቢ መሆኑን መገንዘብ የግድ ይላል፡፡

አማራጭ የሆኑ የማስተማር መሣሪያዎችም ለአደጋ የማያጋልጡና አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ሆነው የልጁን አካላዊ ብቃትና የማቀናጀት አቅም ባገናዘበ መልክ ተመርጠው የሚዘጋጁ ይሆናል፡፡

3.4.4 የትምህርት ቅስሞሽ ምዘናን ስለማስማማት

የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና የሚከናወነው በምልከታ፣ መረጃ በማሰባሰብና በነዚህ ዙሪያ ውሳኔ ላይ መድረስ ሲቻል ነው፡፡ የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና የመማር ማስተማሩን ሂደት በተገቢው መንገድ ለመምራት የሚያግዝ ዘዴ እንጂ ተማሪዎችን በደረጃ አስቀምጦ ከክፍል ወደ ክፍል ለማሸጋገር የሚያገለግል መሣሪያ ብቻ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ምዘናን ከላይ ለተጠቀሰው ተግባር ብቻ የምናውለው ከሆነ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ሥነልቡና መጉዳቱና የትምህርት ፍላጎታቸውንም ማቀዛቀዙ የማይቀር ነው፡፡

በመሆኑም በአካታች የመማሪያ ክፍል ውስጥ የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና፣

1. መምህሩ ትምህርቱን ለሁሉም ተማሪዎች በሚያመች መልኩ የማስማማት ሥራ እንዲሠራ ይረዳዋል፣ ይህም ማለት በምዘናው ውጤት ተማሪው የተሰጠውን ተግባር በተገቢው መንገድ አለማከናወኑን ከተረዳ ይህ ለምን እንደሆነ ይመረምራል፣ ከዚያም የማስተማር ስልቱን በአዲስ መልክ ይቀርፃል ማለት ነው፡፡
2. ለተማሪውም ሆነ ለወላጆች ግብረ-መልስ ይሆናል፣
3. ተማሪዎችን በምዘና ወቅት በተገኘ ውጤት በደረጃ ለማስቀመጥ ከሚደረግ ሙከራ (norm-referenced) ይልቅ በመማር-ማስተማሩ ወቅት ባግባቡ የተላለፉና ያልተጨበጡ ተግባራትን በመለየት (ተግባር ተኮር) እገዛ ማድረግን ያመለክታል፣

4. የተማሪዎችን ልዩ ፍላጎት ያማከለ እንዲሆን የመጣር፣ (ምሳሌ ማየት የተሳነው በብሬልና በቃል ንባብ፣ መስማት የተሳነው ደግሞ በምልክት ቋንቋ መደገፍ እንዳለበትና የአካል እንቅስቃሴ ያለባቸው ተማሪዎች በምዘና ወቅት ተጨማሪ ስዓት እንደሚያስፈልጋቸውና)
5. ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና በግል የትምህርት መርሃ-ግብር ላይ ተመስርቶ መከናወን እንደሚገባው መረዳት ያስፈልጋል።

3.4.4.1 የትምህርት ቅስሞች ውጤቶች

እያንዳንዱ የመማር ማስተማር ተግባር ሂደቱን የሚገመግምበት መንገድ እንዲኖረው ግድ ይላል። መምህራን የመማር-ማስተማሩን ውጤት መለየት ከቻሉ ባንፃሩ በማስተማርና በምዘና ተግባራትም መሻሻልን ሊያሳዩ ይችላሉ። የትምህርት ቅስሞሽ ውጤቶች ለተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች፣ ክሂሎችና የትምህርት ደረጃዎች ተለይተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል። በመሆኑም፣ አዲስ የትምህርት ቅስሞሽ ተግባር ሲታቀድ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች መምህሩ ለመመለስ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

- ተማሪዎች እንዲያውቋቸውና እንዲያዳብሩዋቸው የሚፈለጉ ክሂሎች ምንድናቸው?
- ምን አዲስ ነገር እንዲታወቅ ይፈለጋል?
- ምን ባህርያት እንዲዘወተሩ ይጠበቃል? የመሳሰሉትን ያካትታል።

የትምህርት ቅስሞሽ ውጤቶች የትምህርት ትግበራው ውጤቶች ናቸው።ይህም የሚያሳየው ተማሪው በሥርዓተ ትምህርት መካተት ተግባራት ዙሪያ ምን ያህል ክሂል እንደተላበሰ፣ ባህርይና ዕውቀቱ ምን ያህል እንደዳበረ መረጃ መሣሪያ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

3.4.4.2 ግብረ-መልስ

የትምህርት ቅስሞሽን ለመመዘን ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች ዋናው ግብረ-መልስ ነው። ተከታታይ በሆነ መልኩ የሚከናወን የተማሪዎች እንቅስቃሴ ግብረ-መልስ ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ወቅት ትምህርቱን በሚገባ መከታተል መቻላቸውንና ብሎም የተሻለ ዕድገት ለማስመዝገብ ወደፊት ሊወሰድ የሚገባውን ርምጃ ያመላክታል። ተማሪዎች መደበኛ በሆነ መልክ ከሚሰጣቸው የቡድንም ሆነ የክፍል ውስጥ ግብረ-መልስ ተጠቃሚ ይሆናሉ፣ ይህም ለወደፊት መሻሻል በሚያስፈልጋቸው ጉዳይ ዙሪያ አትኩሮት እንዲያደርጉ ከማገዙም በላይ በጉዳዩም ከመምህራን ጋር ውይይት የሚያካሂዱበት መድረክ ይፈጥርላቸዋል ተብሎ ይታሰባል።

ውጤታማ ግብረ-መልስ የምንለው፣

- በመምህሩና በተማሪው መካከል ጤናማ፣ ሰላማዊና በመተማመን ላይ ያተኮረ፣
- በተግባር ላይ ያተኮረና ተዛማጅነት ኖሮት መደበኛ ጊዜን የጠበቀ፣
- በተሰጠው ግብረ-መልስ ላይ በማተኮር ተማሪዎችን ለተሻለ እንቅስቃሴ የሚያነቃቃ፣
- የሚሰጠው አስተያየት ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ችግር የሚፈቱበት መሆኑን፣
- ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጣቸው ጠያቂና ለውይይት የተነሳሽነት መንፈስና ክህሎት እንዲላበሱና እንዲሰማቸው ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን ነው።

አዎንታዊ የሆነ ግብረ-መልስ ጥንካሬን አጠናክሮ የሚቀጥል፣ ድክመትን ለይቶ የሚያወጣና ድክመቶችንም ለማስወገድ፣ ብሎም ለማረም የሚያግዝ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። አሉታዊ የሆነ ግብረ-መልስ በአንፃሩ የተማሪውን በራስ የመተማመን ሂደት የሚሸረሽርና ተማሪውን ለመሻሻል የማያነሳሳ በመሆኑ በጥንቃቄ ሊስተናገድ ይገባል።

3.4.4.3 ተከታታይነት ያለው ምዘና

ተከታታይነት ያለው ምዘና ተማሪው ምን ያህል ትምህርቱን እንዳወቀው፣ እንደተገንዘበውና የተገነዘበውንም በተግባር የማዋል ክሂል መላበሱን የምናውቅበት መሣሪያ ነው። ምዘና ተማሪዎች የትምህርት ቅስሞሹን በትክክል መገንዘባቸውንና ወደፊት መሻሻል የሚገባቸውን ጉዳዮች ለመለየት የምንገለገልበት መሣሪያ እንጂ የትምህርት ቅስሞሽን ብቻ የምንለካበት መሣሪያ እንዳልሆነ መረዳት ይገባል። ተከታታይ ምዘና በማከናወን የትምህርት ቅስሞሽ ሂደቱን መከታተልና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተማሪውን ፍላጎት ባማከለ መልኩ የማስተማር መማር መስተካከያ ማድረግ ተገቢ ነው።

ስለሆነም ሁሉም ተማሪዎች ችሎታቸውን የማውጣት ዕድል እንዲመቻችላቸው፣ ትምህርቱን የመከታተልና በውጤታማነት እንዲያጠናቅቁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባል። ከዚህ ባሻገር፣ ተከታታይ ምዘና መምህሩ የዓመቱን የትምህርት ማጠናቀቂያ ዘመን ሳይጠብቅ ከተማሪው፣ ከወላጆችና ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር በየወቅቱ ውይይት የሚካሄድበትን ምቹ አጋጣሚን ይፈጥራል። ተከታታይ ምዘና በምልከታ፣ በተማሪው የዕለት ለዕለት ክንዋኔ ማህደር፣ (Portfolio) በክህሎት መቆጣጠሪያ መዘርዝር፣ (Checklist) በጨበጡት ዕውቀት፣ በሚያሳዩት የባህርይ ለውጥ፣ በክፍል ውስጥ ሙከራዎችና በግል ምዘና ውጤት ሊጨበጥ /ሊገኝ /ይችላል።

3.4.4.4 ምልከታ

ተማሪዎችን የተጠና ዘዴን በመጠቀም ለብቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው ጋር፣ በቡድን፣ በተለየ ቀንና ሰዓት እንዲሁም በተለያዩ ቦታዎች በሚያሳዩት እንቅስቃሴ መገምገም ይቻላል፣ ምልከታው የትምህርት ቅስሞሽ ውጤቶች፣ ተግዳሮቶችና ባህርይት ነፀብራቅ ናቸው። የሚመዘገቡ (anecdotal

records)ውጤቶች እውነትነትን የተላበሱ ከመሆናቸው ባሻገር በይሆናል ተነሳሽነትና ዓመት ተጠብቆ በሚሰጥ ውሳኔ የተማሪውን እንቅስቃሴ የሚለኩ አይደሉም፡፡

ይልቁንም በተለያዩ ጊዜያት ተማሪው የሚያሳቸውን እንቅስቃሴ ዘግበው የሚይዙና ተማሪውን የራሱን ሃሳብ እንዲገልፅ ዕድል በመስጠት ያለውን ክህሎት በቃል ጭምር እንዲሰጥ ማበረታታት የሚያስችሉ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ ይህም ተማሪው/ዋ/ አሁን ያለበትን ተጨባጭ ሁኔታ እንድንገነዘብ ይረዳናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የዳሰሳ ሙከራ /Screening test/ በማከናወን መምህሩ የተማሪውን ጠንካራ ጎንና ችሎታ በመረዳት ተገቢውን የመማር-ማስተማር ሥራ እንዲያደራጅ ይረዳዋል፡፡

3.4.4.5 የማህደር ምዘና

አንደኛው የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና ዘዴ የተማሪው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚመዘገብበት ማህደር መገምገም ይሆናል፡፡ ማህደር ስንል፣

- እያንዳንዱ ተማሪ በየዕለቱ የሚያሳየው እንቅስቃሴ ሰነድን የያዘ፣
- ተማሪዎች ትምህርቱን እንዴትና በምን መልክ እንደተማሩ የሚያሳይ፣
- ተማሪዎች የራሳቸውን ሥራ እየገመገሙ ለማሻሻል የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ የሚያስረዳና
- የተማሪዎችን የዕለት ተዕለት ጠንካራ እንቅስቃሴ በሚገባ በመከታተል ለተሻለ ተግባር የሚያደራጅ ሰነድ ነው፡፡

በማህደር ተመዝግበው ከሚያዙ ተግባራት መካከልም፣ የዕሁፍ ተግባራት፣ (ዕሁፎች፣ ታሪኮችና ሪፖርቶች) ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ የስዕል ሥራዎች፣ ካርታዎችና ቅርፆች፣ የተለያዩ የቤትና ክፍል ውስጥ የሙከራ ስራዎች ውጤቶችና ግራፎችን ያካተተ ይሆናል፡፡ በማህደር ተካተው የሚያዙ የሥራ ውጤቶች በጊዜ ቅደም ተከተል የሠፈሩ በመሆናቸው የተማሪውን ወቅታዊ ውጤት ለማወቅ መምህሩ አይቸገርም፡፡ ተገቢ የሆነ ምዘና የምንለውም የተማሪውን ያለፈ ውጤት አሁን ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ ጋር ማወዳደር የሚያስችል ሲሆን ነው፡፡

የማህደር ግምገማ ከወላጆችና ከተማሪው አሳዳጊዎች ጋር በልጁ የትምህርት እንቅስቃሴ ዙሪያ ለመወያየት የሚያስችል መድረክ ሁኖም ያገለግላል፡፡ ከዚህም ባለፈ ተማሪው ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ሲሸጋገር ለአዲስ መምህራን የልጁን ያለፈ ታሪክ (ጠንካራና ደካማ ጎን) ለማስጨበጥ የሚያገለግልም መሣሪያ ነው፡፡

3.4.4.6 ሙከራዎች (tests)

ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በሙከራዎች ለመመዘን የሚከተሉትን ማስተዋል ይገባል፡፡

- ምዘና የሚሰጥበት አካባቢ ፀጥታ የሠፈነበት መሆኑንና ምዘናዎች አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ወደ ብሬል መቀየርና በቃልም መመዘን አስፈላጊ መሆኑን፣

- ሙከራዎችን በአንድ ጊዜ አብዝቶ ከማቅረብ ይልቅ ከፋፍሎ ማቅረብን፣
- አሰፈላጊ ሆና ሲገኝ በቂ ሰዓት የመመደብን፣
- እንደ አስፈላጊነቱ ድጋሚ የፈተና ዕድል የመፍጠርንና
- በየመሀሉ የእረፍት ጊዜ የማመቻቸት የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

3.4.4.7 ራስን መመዘን

ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ የሚገመግሙበት መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል። የራስ መተማመናቸውን በማይሸረሽር መልኩ ጥፋትን የማመንና እንዲያስተካክሉ ዕድልና ጊዜ መስጠትም ተገቢ ይሆናል። ራስን የመመዘን ተግባር በማንኛውም ጊዜ የተማሪውን ችሎታና ያለበትን ሁኔታ ለመገምገም፣ የደረሰበትን የዕውቀት ደረጃና መሻሻሉን ለመከታተል የሚያስችል መንገድ ነው።

4. የግል የትምህርት መርሀ ግብር፤

- ባለሙያዎች በተለይም መምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በትምህርት ተደራሽ ለማድረግ የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነው፣
- ተማሪዎች በጅምላ ወይም በቡድን ሳይሆን በተናጠል ከመማር ማስተማሩ ተግባር ተጠቃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
- ትምህርት ቀጣይነት ያለው ተግባር መሆኑን በመገንዘብ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች መመዝገባቸውን ያረጋግጣል፣
- የተማሪው የመማር ሂደትና አተገባበር የሚገለፅበትና የሚገመገምበት ምዝገባ መካሄዱን ያካትታል፣
- ተማሪው መደበኛ የሆነውን የትምህርት ስርዓት ለመከታተል የሚችልበት የግል የትምህርት መርሀ ግብር ዓላማዎችን ያቅዳል፣
- ለመማር ማስተማሩ ተግባር የሚያግዙ ግብዓቶችንና የተማሪውን ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል ቀጣይነት ያለው የዕቅድ ቅደም ተከተልን ያካትታል፣
- የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት ማርካት ይቻል ዘንድ የተማሪውን የቅርብ ጊዜ ፍላጎትና መደረግ የሚገባውን ቅድመ ዝግጅት ይለያል፣
- የተማሪው የመሳተፍ መብት መከበሩን ለማረጋገጥ ዝግጅቶች በተገቢው መንገድ መደራጀታቸውንና የተመዘገበውን ዕድገት መከታተል የሚያስችል መግለጫ ይኖረዋል፣
- የትምህርት ግብዓቶች ለተማሪዎች ሁሉ እንደፍላጎታቸው መዳረሱንና በአገልግሎት ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣
- ተማሪዎች የተለየ የመማር ፍላጎት እንዳላቸው ይገነዘባል፣
- ግልፅና በእውነታ ላይ የተመሠረተ ከመሆኑም በላይ ሊጠቀምበት የሚፈልግ አካል ሁሉ ሊተገብረው የሚችል መሣሪያ እንደሆነ ይታመናል።

በመሆኑም የግል የትምህርት መርሀ-ግብር ለማቀድ ሲታሰብ የትምህርት ቤት ኃላፊዎች መገንዘብ የሚኖርባቸው አብይ/ዋነኛ/ጉዳይ የልጁን ፍላጎት እንጂ ጉዳተኝነቱን መሆን የለበትም። ምክንያቱም እያንዳንዱ የግል የትምህርት መርሀ ግብር እንደተማሪው ግል ፍላጎት የሚለያይ ነውና።

4.1. የግል የትምህርት መርሀ-ግብር ለምን አስፈለገ?

አንዳንድ ተማሪዎች መደበኛውን የትምህርት ሥርዓተ ትምህርት በተገቢው መንገድ መከታተል እንዲችሉ ከፍላጎታቸው ጋር የሚጣጣም የግል የትምህርት መርሃ-ግብር እንዲዘጋጅላቸው ያስፈልጋል።

የግል የትምህርት መርሃ ግብር የሚያስፈልገውም ፤

- የተማሪዎችን የመማር መብት አረጋጋጭ በመሆኑ፣
- ለመምህራንና ሌሎች ባለሙያዎች ደግሞ ትምህርቱን በተገቢ መንገድ ለማከናወን የሚያግዛቸው መሣሪያ በመሆኑ፣
- በመደበኛ የመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚከናወን የጅምላ የማስተማር ዘዴ ሁሉንም ተማሪ ማርካት ባለመቻሉ፣
- የተማሪዎችን መጠነ-ማቋረጥና መጠነ-መድገምን የሚቀንስ በመሆኑ፣
- የትምህርት ቤት አመራሮች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል እንቅስቃሴ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ በመከናወን ላይ መሆኑን ማረጋገጫ መሣሪያ በመሆኑ ፣
- ወላጆችና አሳዳጊዎችም በትምህርቱ ሥራ ላይ ተሳታፊ መሆናቸው የሚረጋገጥበትና ለአፈፃፀሙም ግበረ መልስ የሚያገኙበት ዕድል ስለሚፈጥር፣
- በትምህርቱ ሥራ አግባብነት ያላቸው አካላት በሙሉ መረጃን እንዲለዋወጡ፣ ውጤቶችን እንዲለዩ፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት እንዲመርጡ፣እንዲያቅዱ፣ በሃላፊነት ደረጃ ላይ ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ፣ የመማር ማስተማሩን ስልትና ድጋፍ እንዲተልሙና ግብዓቶችን/የቁሳቁስና የሰው ሃይል/ እንዲወስኑ የሚያስችል መሣሪያ በመሆኑ ነው።

4.2. የግል የትምህርት መርሃ-ግብር አዘገጃጀት

በግል የትምህርት መርሀ-ግብር አዘገጃጀት ወቅት መወሰድ የሚገባቸው ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ደረጃም የእያንዳንዱን ፈፃሚ አካል ጥረትና መተጋገዝ የግድ ይፈልጋል።

ደረጃ 1 - ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልገውን ተማሪ የመለየት

የእያንዳንዱን ተማሪ ባህርይ በመረዳት ሂደት ቅርበት ያለው መምህሩ ሲሆን ወላጆችም የማይናቅ ሚና ይጫወታሉ። የእያንዳንዱ ተማሪ ተግዳሮት ግልፅና ቀላል በሆነ መንገድ ሊታወቅ የሚችለው በሁለቱም የጋራ ትብብር መሆን ይኖርበታል። ስለዚህም የልጃቸውን የፍላጎት ተግዳሮቶች አስመልክቶ ወላጆችና

አሳዳጊዎች ከመምህራን ጋር በቅርበት ሊወያዩ ያስፈልጋል። ይህ መረጃ በበኩሉ ተማሪው ክፍል ውስጥ ከሚያደርገው ተጨማሪ እንቅስቃሴ ጋር ተዳምሮ አጋዥ መረጃ ሊሆን ይችላል። የልጁን ችሎታና ፍላጎት የመለየት ተግባር የሚመሰረተውም ከመምህራን ከሚገኝ መረጃ፣ ከልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን (ካሉ)፣ ከትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራንና ከወላጆች ወይም ከአሳዳጊዎች ይሆናል።

ደረጃ 2 - ቡድንን ስለማደራጀት

የግል የትምህርት መርሀ-ግብርን ለመተግበር የተውጣጣ ቡድን መመስረትና አቅዶ እንዲመራ ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል። የባለሙያዎች ስብስብ ጠቃሚ በመሆኑም አገልግሎትና እገዛ ለማበርከት እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። በቅድሚያ ተማሪው፣ ወላጅ/አሳዳጊ/፣ መምህሩንና የትምህርት ቤቱን ርዕሰ መምህራን በማስቀደም ሌሎች ባለሙያዎች በተጨማሪነት እንዲያገለግሉ መጋበዝ ይገባል።

ይህን ቡድን በማቋቋም ሂደት የመደበኛው ክፍል መምህር ወይም የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህሩ ተነሳሽነትን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። የቡድኑ አወቃቀር በተማሪው ልዩ ፍላጎት ዙሪያ የሚያጠነጥንና ባካባቢው ሊገኙ የሚችሉ ተጨማሪ ባለሙያዎች (ቴራፒስቶች፣ ረዳቶች፣ አማካሪዎች ወዘተ) ላይ የሚያተኩር ይሆናል። ከዚህ በኋላ ቡድኑ ተሰባስቦ ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚያገለግል የግል የትምህርት መርሀ ግብር ይነድፋል። በአንድ ትምህርት ቤት እንዳስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ የግል የትምህርት መርሀ-ግብር ቡድን የሚዋቀርበት ሁኔታም ሊፈጠር ይችላል። ይህም ብዝሀ-ግልጋሎቶችን ያካተተ ዘዴን እንደመጠቀም ይቆጠራል።

ደረጃ 3 - ግብን መትለምና መተግበር

የግል የትምህርት መርሀ-ግብር ዓይነተኛና ዋነኛው ዓላማ፣

1. በተወሰነ ትምህርት ዙሪያ መከናወን የሚገባውን የግብ ትኩረት መንደፍ፣
2. በልጁ ስሜታዊና ማህበራዊ ክህሎት ዙሪያ ግብ ማውጣት፣
3. አመቺ የሆነ የመማር ስልትን መፈለግ ነው።

የልጁ ማዕከላዊ ችግር የሚያጠነጥነው በአንዱ ወይም በሌላኛው ዙሪያ ሊሆን ቢችልም ከላይ የተጠቀሱት ዓላማዎች ተያያዥነት ያላቸው እንደመሆኑ አንዱን ከሌላው ማበላለጥ ወይም አንዱን መርጦ ሌላኛውን መተው አይመረጥም።

የግል የትምህርት መርሀ ግብር ቡድንም ግብን በግልፅ አስቀምጦ ተግባራዊ መፍትሄዎችን ማመላከትና በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በተግባር የሚውሉበትን መንገድ መቀየስ/መከታተል/ተገቢ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ የምዘና ስርዓቶችንና መረጃ መለዋወጥ የሚያስችልበትን ስልት በግልፅ ማመላከት ይጠበቅበታል።

4.3 የግል የትምህርት መርሀ-ግብር ሂደት

- የተማሪውን የትምህርት ተደራሽነት በማስፋት ተሳትፎን ከማሳደጉም ባሻገር በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖር ያግዛል፣
- ተጋጋዥ የሆነ የትምህርት ቤት ማህበረሰብን በመፍጠር ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎችና የወላጆችን እሴትና መከባበር ያጎላል፣
- ወላጆች በውሳኔ ሰጭነት እንዲሳተፉ ጭምር ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፣
- በጎ የሆነ የመማር-ማስተማር አካባቢን ለመፍጠር አስተዋፅኦ ያበረክታል፣
- የተማሪውን ልዩ እገዛና ዕምቅ ችሎታ በተገቢው መንገድ ለማስተናገድ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣
- ከትምህርት ቤት ህይወት በፊትም ሆነ ትምህርታቸውን ጨርሰው እስኪወጡ ድረስ ያለውን ህይወታቸውን ሁኔታ መገምገም የሚያስችል ዑደት (Cyclic Process) በመሆኑ በውስጡ ምዘናን፣ ግብ ማስቀመጥን፣ ክለሳንና ሪፖርት የማቅረብን እንቅስቃሴዎች አካቶ ይይዛል፣
- ለሁሉም የቡድኑ ተሳታፊ አባላት የትምህርቱ ይዘት ከተማሪው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተዛመደ ግብ ላይ አትኩሮት መደረጉን የማረጋገጥ ዕድል ይሰጣል።



አተገባበር

- ግብዓቶችን በአግባቡ ስለመጠቀም
- ተማሪውን በታቀዱ ተግባራት ስለማሳተፍ
- ድጋፍ አሰጣጥ
- ፕሮግራሙን መከታተልና መገምገም

ቀስቶቹ የሚያመለክቱት የእያንዳንዱ ሣጥን ተግባራት በተከታታይነት ስለሚከናወኑበት ሁኔታ ሲሆን፣ እያንዳንዱ እንቅስቃሴም ከቀድሞው ልምድ በመነሳት የሚታቀድ ይሆናል። ዕቅድ እንቅስቃሴ ላይ በመመርኮዝ የሚታቀድ ሲሆን ትግበራ ደግሞ በዕቅድ ይመራል ማለት ነው።

ምዘና የትግበራ ሥራዎች በመካሄድ ላይ እንዳሉ የሚከናወን ሲሆን ይህም መሠረት የሚያደርገው በዕቅድ ወቅት በተጣለው ግብ ላይ ይሆናል ማለት ነው። የግል የትምህርት መርሀ-ግብር በምክክር ላይ የሚያተኩር ሲሆን የተማሪውን ፣ የወላጆችን፣ የትምህርት ባለሙያዎችንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሰዎች ተዋፅኦ አንድ ላይ ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

የግል የትምህርት መርሀ-ግበር የሚከተሉትን ዑደቶች (Cyclic) ሊያካትትም ይቻላል፣

1) የችግሩን አካባቢ የማወቅ
2) ችግሩን ለመቅረፍ ማቀድ
3) ዕቅዱን መተግበር
4) ዕቅዱን መገምገምና
5) በቀጣይነት እገዛ መስጠት የሚያስችል የማስማማት ተግባር ማከናወን ናቸው።

4.4 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን

4.4.1 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን ዓላማ

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን አላማ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የተለየ ፍላጎት እርካታን በማግኘት ግቡን እንዲመታ አስተማማኝ ለማድረግ ነው። የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አባላት የተለዋወጧቸውን ልምዶችና እውቀታቸውን እንዲሁም ቁርጠኝነታቸውን በትምህርት

መርሃ ግብሩ ውስጥ ያካትታሉ፣ ይህም ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በአጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተደራሽ እንዲሆኑ ያግዛል።

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን የሚከተሉት ተግባራት አሉት

- የረጅምና የአጭር ጊዜ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብሩን ግቦች ያሻሽላል፣
- የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ቁሳቁሶችን ይመርጣል፣
- የተማሪውን የትምህርት ለውጥ ሂደት መከታተያ ሥርዓት ያዘጋጃል
- የተማሪውን የጊዜ ሠሌዳና የእቅድ ተግባራት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ከተጣሉት ግቦች ጋር እንዲጣጣሙ ያደርጋል፣
- የተማሪው የነፍስወከፍ የትምህርት መርሃግብር በሚተገበርበት ወቅት የበኩሉን ኃላፊነት ይወጣል፣
- የድጋፍ አገልግሎቶች ቀጣይነትን ያረጋግጣል፣
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ግምገማ የሚካሄድበትን ጊዜ ይወስናል።

4.4.2 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን አባላት ስብጥር

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን አባላት ስብጥር እንደየተማሪው ፍላጎት ይለያያል። በአጠቃላይ የቡድኑ አባላት ስብጥር የሚከተለውን ይመስላል፣

- ተማሪው/አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ/
- ወላጅ /አሳዳጊ
- የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር
- መምህር/የክፍሉ ወይም የትምህርቱ/
- የልዩ ትምህርት መምህር/ተዘዋዋሪ መምህር እና
- ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ

4.4.3 የነስፍ ወከፍ የትምህርት መርሃ -ግብር ቡድን አባላት ሚናና ኃላፊነት

እያንዳንዱ የቡድን አባል ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ወደ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ስብሰባ ይዞ ይመጣል። የቡድኑ አባላት መረጃዎችን ከመለዋወጥ ባሻገር የተማሪውን የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር በጋራ ይፅፋሉ። እያንዳንዱ አባል ስለተማሪው ያለውን መረጃ ያቀርባል። ይህንንም መሠረት በማድረግ ለተማሪው ፍላጎት ምን ምን አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት ይገልፃሉ።

4.4.3.1 ተማሪዋ/ው

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድኑ እንደየአስፈላጊነቱ አመቺ ነው ብሎ በወሰነ ጊዜ ተማሪዋ/ውን የቡድኑ አባል ማድረግ ይችላል፣

የተማሪው ሚናም፤

- ስለራሷ/ራሱ የትምህርት ሁኔታ መረጃ/ግብዓት ትሰጣለች/ይሰጣል፣
- ስለራሷ/ራሱ ፍላጎትና ምርጫ መረጃ ትሰጣለች/ይሰጣል፣
- ስለወደፊት እቅድ አወጣጥ የራሷን/የራሱን ሃሳብ ትሰጣለች/ይሰጣል፣
- ውሳኔ ሲሰጥና ግብ ሲጣል ትሳተፋለች/ይሳተፋል፣

በተለይም የስብሰባው ዓላማ እንደሚከተለው ሲሆን ተማሪዋ/ው በስብሰባው ላይ እንድትገኝ/ እንዲገኝ ትጋበዛለች/ይጋበዛል።

- ተማሪዋ/ው በሽግግር ወቅት የሚያስፈልጋትን/የሚያስፈልገውን አገልግሎቶች የሚገልፅ ፅሁፍ ሲዘጋጅ፣
- ለተማሪዋ/ው ከ2ኛ ደረጃ በኋላ ምን ሊደረግላት/ሊደረግለት እንደሚገባ ግብ ለመጣልና እንዲሁም ተማሪዋ/ው እነዚህን ግቦች እንድትመታ/እንዲመታ የሚያስፈልጉ እገዛዎችና የሽግግር ወቅት አገልግሎቶች ሲዘጋጁ ይሆናል።

ተማሪዋ/ው በቡድን ውስጥ መሳተፏ/መሳተፉና ተማሪዋ/ው ስለምትማረው/ስለሚማረው ትምህርት እንድታውቅና/እንዲያውቅና በደንብ ሃሳቧን/ሃሳቡን እንድትገልፅ/እንዲገልፅ ከማድረጉም ባሻገር ለተማሪዋ/ው ስለራሷ/ራሱ ተሟጋችና በራሷ/ሱ ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠትን ያስተምራታል/ያስተምረዋል።

4.4.3.2 ወላጅ/አሳዳጊ

ወላጆች /አሳዳጊዎች ስለልጃቸው የጠለቀ እውቀት ስላላቸው የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን ቁልፍ አባላት ናቸው።

በመሆኑም፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚከተለውን ሚና ይጫወታሉ

- ስለልጃቸው የቀድሞ ባህርይ፣ ጥንካሬና ፍላጎት ያላቸውን እውቀት ያካፍላሉ፣
- ስለልጃቸው ያላቸውን ምኞትና ፍርሃት እንዲሁም ልጃቸው የተሻለ ትምህርት የምታገኝበትን/ የሚያገኝበትን መንገድ ይጠቁማሉ፣
- ልጃቸው እንዴት ልትማር/ሊማር እንደምትችል/እንደሚችል ሃሳብ ይሰጣሉ፤ የልጃቸው ፍላጎት ምን እንደሆነና እንዲሁም ሌሎች የሚያውቋቸውን ሁኔታዎች ይገልፃሉ፣
- የልጃቸውን የትምህርት ሁኔታ ለማሻሻል ከሌሎች የቡድኑ አባላት ጋር ሃሳብ ይለዋወጣሉ፤ ይወያያሉ፣

- ተማሪዋ/ው በትምህርት ቤት የምትማራቸውን/የሚማራቸውን ክሂሎት በቤት ውስጥ ስለመጠቀሟ/ሙ ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡

4.4.3.3 የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ሚና

- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን ሂደት ይደግፋል ያስተባብራል፣
- ትምህርት ቤቱን ይወክላል፣
- ስለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶችና ስላለው ሃብት (የሰውና የማቴሪያል) እንዲሁም እንዴት እየተዳደሩ እንደሆነ ለስብሰባው ይገልፃል፡፡
- አስፈላጊውን ሃብት ሥራ ላይ ያውላል፤ ከዚህም በተጨማሪ በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር እንዲተገበሩ የተቀመጡ አገልግሎቶች መሰጠታቸውን ያረጋግጣል፡፡

4.4.3.4 የክፍል ወይም የትምህርት ዓይነቱ መምህር

ከተማሪዋ/ው መደበኛ ትምህርት መምህር መካከል አንዱ (የክፍል ወይም የትምህርት ዓይነት) የግድ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን አባል ይሆናል፡፡

የመምህሩ ሚና በሚከተሉት ጉዳዩች ዙሪያ መረጃና ልምዱን ማካፈል ይሆናል፤

- መደበኛ ክፍል ውስጥ ስለሚሰጠው አጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርት ፣
- ሥርዓተ ትምህርቱን በተማሪው ፍላጎት መሠረት እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ፣
- የተማሪውን ልዩ ፍላጎት ለማርካት በነፍስ ወከፍ እንዴት ማስተማር እንደሚቻል፣
- ለተማሪዋ/ው የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችና አገልግሎቶች ላይ ሃሳብ ይሰጣል፣
- ተማሪዋ/ውን በተጓዳኝ ትምህርቶችና ሌሎች ተግባራት እንዴት ማሳተፍ እንደሚቻል፣
- ተማሪዋ/ው የተማረችውን/የተማረውን የችሎታዋን/የችሎታውን እንድታሳይ/እንዲያሳይ ፈተናን እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን በአግባቡ በመሙላት ይሳተፋል ፣
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን መተግበሩን ይከታተላል፣
- የትምህርት ልምዱንና እውቀቱን ያካፍላል ከዚህም በመነሳት ወላጆች ልጅን እንዴት ማሳደግ/ ማስተማር እንዳለባቸው እውቀት በመገብየት ይጠቀማሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

የክፍል /የትምህርት ዓይነት መምህሩ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብሩን ለመተግበር ከተማሪው ጋር የመስራት ኃላፊነት አለበት፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፡ መምህሯ/መምህሩ፤

- ከልዩ /ተዘዋዋሪ መምህር ጋር በመተባበር ይሰራል፣
- ከልዩ/ተዘዋዋሪ መምህር ጋር በክፍል ውስጥ በቡድን ያስተምራል፣
- ከሌሎቹ መምህራንና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር በመተባበር ይሰራል፣

4.4.3.5 ልዩ መምህር/ተዘዋዋሪ መምህር

የልዩ ትምህርት መምህር/ተዘዋዋሪ መምህር የሚከተለውን ሚና ይጫወታል፡-

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ስለሚማሩበት መንገድ ያለውን ጠቃሚ መረጃና ልምድ ያካፍላል፣
- ተማሪዎቹ በተገቢው ሁኔታ እንዲማሩ ለመርዳት ይቻል ዘንድ ሥርዓተ ትምህርትን እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ያለውን እውቀት ያካፍላል፣
- ተማሪዋ/ው የተማረችውን/የተማረውን የችሎታዋን/ውን እንድታሳይ/ እንዲያሳይ የፈተና ማሻሻያ መንገዶችን ያመለክታል፣
- አስፈላጊ ስለሆኑ ተጨማሪ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መረጃ ይሰጣል፤ የትና እንዴት እንደሚገኙም ይጠቁማል፣
- የተማሪውን ልዩ ፍላጎት ለማርካት የነፍስ ወከፍ ትምህርት ሲሰጥ እገዛ ያደርጋል፣
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን ይፅፋል፣

የልዩ ትምህርት መምህር/ተዘዋዋሪ መምህር የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብሩን ለመተግበር ከተማሪው ጋር የመስራት ኃላፊነት አለበት። ስለዚህም እሷ/እሱ፣

- በድጋፍ መስጫ ክፍል ወይም በልዩ ክፍል ውስጥ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ከሚጠቀሙ ተማሪዎች ጋር ይሰራል፣
- ከመደበኛው ትምህርት መምህር ጋር በመሆን በክፍል ውስጥ ያስተምራል፣
- የትምህርት ቤቱ መምህራን በተለይም የመደበኛ ትምህርት መምህራን የተማሪዎቹን ልዩ ፍላጎት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ማስተማር በሚችሉበት መንገድ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል።

4.4.3.6 ሌሎች

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ተጨማሪ ሌሎች ባለሙያዎችን እውቀትና ሙያ ያካትታል፣ ይህም በተማሪው ሁኔታና በባለሙያዎቹ መገኘት ይወስናል። ምናልባትም የሚከተሉትን ባለሙያዎች ሊጨምር ይችላል።

- የተጓዳኝ አገልግሎቶች ባለሙያዎች፣ ለምሳሌ የወጌሻ ባለሙያዎች፣ ማህበራዊ ሠራተኞች፣ የጤና አጠባበቅ ተወካይ (አስፈላጊ ከሆነና የሚገኝ ከሆነ)፣
- ምቹ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለማዘጋጀት እንዲቻል የግምገማ ውጤቶችን የሚተነትን ባለሙያ፣
- ተማሪዋ/ው በሽግግር ወቅት እድሜ ውስጥ ከሆነች/ ከሆነ የሽግግር ወቅት አገልግሎት ኤጀንሲ ተወካይ ፣ለምሳሌ ከመዋዕል ህፃናት ወደ መጀመሪያ ደረጃ፣ ከመጀመሪያ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ወይም ወደ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ወዘተ ናቸው፡፡

4.5 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን ስብሰባ

አጠቃላይ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር እቅድ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃግብር ቡድኑ አባላት ስለ ተማሪዋ/ው፣ ስለትምህርት ቅስሞሽ ሂደቶችና እየተሰጠ ስላለው ድጋፍ ባላቸው እውቀት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ የቡድኑ አባል በእቅዱ ወቅት የራሷን/የራሱን አስተዋፅኦ ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡

የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ስብሰባ በፊት የጊዜ ሠሌዳ ማውጣት ይኖርበታል፡፡ ትምህርት ቤቱም፡-

- ከቡድኑ አባላት ወላጆችን ጨምሮ ግንኙነት ያደርጋል፣
- ከወላጆች ጋር ግንኙነት በመፍጠር በስብሰባው ላይ መገኘታቸውን ያረጋግጣል፣
- ለወላጆችና ለትምህርት ቤቱ ምቹ የሆነ የጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል፣
- ለወላጆች የስብሰባውን አላማ፣ ቦታና ጊዜ ይነግራል፣

በስብሰባውም፣

- የተማሪዋ/ው ሁኔታ ይገለፃል፣
- እያንዳንዱ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አባል ስለተማሪው ሁኔታ ያለውን ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፣
- ለእያንዳንዱ የቡድን አባላት ሃሳቦችና ግብዓቶች ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል፣
- የተማሪዋ/ውን ፍላጎት እንዴት ማርካት ይቻላል በሚለው ሃሳብ ዙሪያ ውይይት ይደረጋል፣
- የተማሪዋ/ው የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ይዘጋጃል፣

4.6 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ማዘጋጀት

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ሲዘጋጅ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ሊተኮር ይገባል

- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የተዘጋጀበትን ቀን፣
- የተማሪዋ/ው ግለ ታሪክ መረጃ፣

- የተማሪዋ/ው ብቃት
- በትምህርት ቤትየተማሪዋ/ው ሁኔታና የመማር ችግሮችመግለጫ ሲሆኑ፤

ግቦቹም፤

- የረጅም ጊዜ ግቦች
- የአጭር ጊዜ ግቦች
- ዘዴዎች
- የቁሳቁሶች አቅርቦት
- አደረጃጀትና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢ
- የሚሰጥ ድጋፍ
- ምዘና
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ግምገማ ሥርዓትን ያካትታል፡፡

4.6.1 የተማሪዋ/ው ብቃት

- የሚታቀደው እቅድ የተማሪዋ/ውን ጠንካራ ጎኖችና ክሂሎት መሠረት ማድረግ አለበት፣
- የተማሪው የትምህርት ፣ ማህበራዊና ሥነልቦናዊ ችሎታ(ብቃት)ግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል፣

4.6.2 በትምህርት ቤት የተማሪዋ/ው ሁኔታና የመማር ችግሮች መግለጫ

- ተማሪዋ/ው በአሁኑ ጊዜ በትምህርት ቤት /ከትምህርት ቤት ውጭ እየሰራችበት/ እየሰራበት ያለችበት/ያለበት ሁኔታ ለእቅድ አውጣጡ በጣም አስፈላጊ ነው፣
- ተማሪው በትምህርት ቤት በሚማርበት ወቅት የሚያጋጥሙትን የተለያዩ ተግዳሮቶች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል (ይህም በትምህርት፣ በስሜት ወይም በማህበራዊ ግንኙነት ክሂሎት አካባቢዎች ያሉትን ለማለት ነው፡፡)

4.6.3 ግቦች

- በእቅዱ መጀመሪያ ላይ ግቦች በጥቅል መቀመጥ ይኖርባቸዋል
- የእያንዳንዱን የትምህርት ዓይነት በሚመለከት የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት በሚያስችሉ ክሂሎትና ችሎታ ላይ ማተኮር ይገባል፡፡
- ግቦቹ የተማሪዋ/ውን ፍላጎት ማርካት በሚችሉ መልኩ መጣል ይኖርባቸዋል፣
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ግቦች ተግባራዊ ክሂሎትን ኢላማ ያደረጉና የአጠቃላይ ሥርዐተ ትምህርቱ ማዕቀፍ አካል መሆን ይኖርባቸዋል፣

- የተማሪውን አላማዎችና ግቦች በክፍል ውስጥ ተግባራት ውስጥ ለማካተት የሚያስችሉ፤ ዓላማዎቹና ግቦቹ ሊተገበሩ የሚችሉና እድሜን የሚመጥኑ መሆን ይኖርባቸዋል።
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር መመዘንና መለወጥ ያለበት የተማሪዋ/ውን እድገትና ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ መሆን ይኖረበታል።

የረጅም ጊዜ ግቦች

- እቅድ መጀመሪያ ይጣላል፣
- ለአንድ የትምህርት ዘመን ሳይለወጥ ልንጠቀምበት እንችላለን፣
- ተማሪዋ/ው በምታዳብራቸው/በሚያዳብራቸው ክሂሎትና በሚያጋጥሟት/ በሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች ላይ ትኩረት ይሰጣል፣
- በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ የተጣሉት የትምህርት ግቦች ከአገር አቀፍ ሥርዓተ ትምህርቱ ጋር የተጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል፣ግቦቹን ማሻሻል ቢያስፈልግም የተማሪዋ/ውን የነፍስ ወከፍ ችሎታና ፍላጎቶች መሠረት ማድረግ ይኖርበታል።

የአጭር ጊዜ ግቦች

- ተግባር ተኮር ሆነው ግን ከረጅም ጊዜ ግቦች ጋር መጣጣም አለባቸው
- በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ስብሰባ ላይ ግቦቹን የመለወጥ ወይም የማሻሻል ጥያቄዎች ከተነሱ በተማሪዋ/ው ላይ ተከታታይ ምልከታ ካደረጉ ሰዎች ጋር በመወያየትን መሆን ይኖርበታል።

4.6.4 ዘዴዎች

- ተማሪዋ/ውን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል የሚወስኑትን የረጅምና የአጭር ጊዜ ግቦች ማንፀባረቅ አለበት፣
- ግቦቹን ለመምታት በጣም ውጤታማና ምቹ የሆኑ ድጋፍ መስጫ መንገዶች ምን እንደሆኑ ያብራራል፣
- ተማሪዋ/ውን ለማስተማር የትኞቹ ስትራቴጂዎች/ዘዴዎች እንደሚያስፈልጉ ይገልፃል፣
- ምን አይነት የማስተማር ማስማማቶች ያስፈልጋሉ? ለሚለው ምላሽ ይሰጣል።

4.6.5 የቁሳቁሶች አቅርቦት

- ለተማሪው የሚቀርቡ የነፍስ ወከፍና አጠቃላይ ቁሳቁሶችን ያመላክታል፣

- ምን አይነት ተጨማሪ የማስተማሪያ መሣሪዎች ያስፈልጋሉ/አሉ? ለሚለው መልስ ይሰጣል፡፡
- ከክፍል ጓደኛዋ/ው ጋር ስትነፃፀር/ሲነፃፀር ተማሪዋ/ው አንድ አይነት/ተመሳሳይ/ቁሳቁስ ለምን ያህል ጊዜትጠቀማለች/ይጠቀማል የሚለውን ይለያል፡፡
- ምን ዓይነት አማራጭ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች ይገኛሉ? የሚለው ይመለሳል፡፡
- ቁሳቁሶቹ እንዴትና በማን እንደገና ይደራጃሉ? ለሚለው መልስ ይሰጣል፡፡

4.6.6 አደረጃጀትና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢ

- ግቦቹን ለመምታት በጣም ውጤታማና ለተማሪዋ/ው ድጋፍ አሰጣጥ ምቹ የሆኑ መንገዶች ምን እንደሆኑ ይገልፃል፣
- የክፍል ውስጥ ወይም የትምህርት ቤቱን ሁኔታ ይገልፃል፣
- ተማሪው ከምክር አገልግሎት እንዲጠቀም ምን ዓይነት ተግባራዊ ድጋፎች እንዳሉ የማወቅ፤ (ምቹ መቀመጫና የጥሞና ቦታ፣ ምቹ መሣሪያዎች፣ የሚፈልገው ድጋፍ)
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን አባላት ልምዶች እኩል ዋጋ ያላቸውና በውይይት ወቅት ጠቃሚ ናቸው፡፡አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማስተማር ዘዴዎች ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች ማብራሪያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

4.6.7 በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጭ የሚደረግ ድጋፍ

- ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚያስፈልግና/እንዳለ መገንዘብ፤
- የተዘዋዋሪ መምህራንን ድጋፍ ሰጭነት ሚና መረዳት፤
- ከመምህሩ ሃሳብ/ምክር እየተሰጣቸው ወላጆች ለልጃቸው የትምህርት ድጋፍ መስጠት እንደሚችሉ መረዳት፣
- ሌላ የሚሰጥ ተጨማሪ ድጋፍ ካለ የመግለፅ፤ ለምሣሌ ከጤና አጠባበቅ ዘርፍ፣ ከማህበራዊ ሠራተኞች፣ ከማህበረሰብ ሠራተኞች አስፈላጊ ከሆነ/ካለ

4.6.8ምዘና

ምዘና ተማሪዋ/ው በምታስመዘግበው/በሚያስመዘግበው ውጤቶችና በትምህርት ቅስሞሽ ሂደቶች ላይ እንዲያተኩር መደረግ አለበት፤

- ተማሪዋ/ው ያሳየችውን /ያሣየውን ለውጥ እንዴት መገምገም እንደሚቻል ያብራራል፣
- ግምገማው መቼ መካሄድ እንዳለበት ይገልፃል፣
- ተማሪዋ/ው ያለችበትን/ያለበትን ደረጃ ለማወቅና አስፈላጊ ሆኖም ሲገኝ ተጨማሪ ስራ ለመስራት ማን እንደሚገመግመው ይገልፃል፣

4.6.9 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ምሣሌ

ለነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አንድ ደረጃውን የጠበቀ መመሪያ ባይወጣለትም ከዚህ በታች አንድ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቅፅ በምሣሌነት ተሰጥቷል (ተቀጺላ 3) ይህ ቅፅም እንዴት እንደሚሞላና ምን ዓይነት መረጃዎችን ማካተት እንዳለበት አቅጣጫ ይሰጣል። ከዚህ በላይ ደግሞ እያንዳንዱ ትምህርት ቤትና እያንዳንዱ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን የራሱን ቅጽ ሊያዘጋጅ የሚችል መሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው ።

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር (የተማሪው ስም) _____

I. **ግለ ታሪክ መረጃ**

ተማሪዋ/ው ሥም የተወለደ/ች/በት ቀን	አድራሻ
ወላጅ/አሳዳጊ	ስልክ ቁጥር፡- አድራሻ፡-
የትምህርት ቤቱ ሥም	• ይህ ዶክመንት የተዘጋጀበት ቀን • ይህ ዶክመንት የተሻሻለባቸው ቀናት
የመምህራኑ ሥም	

II. ግቦች ፣ የሚሰጡ የድጋፍ አይነቶች እና ምዘና

ብቃት

እዚህ መገለፅ ያለበት

- የብቃት ወይም የክሂሎት ደረጃ
- በትምህርት ቅስሞሽ ወቅት የሚታዩ ጠንካራ ጎኖች
- የመማሪያ አማራጭ መንገዶች
- ማህበራዊ ክሂሎት
- የሚያስደስቱ/ቷ/ትና የሚያዝና/ኗ/ኑት ነገሮች ይሆናሉ፡፡

በትምህርት ቤት የተማሪዋ/ው ሁኔታና የመማር ችግሮች መግለጫ

እዚህ መገለፅ ያለበት

- ተማሪዋ/ው በአሁኑ ጊዜ በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጪ እንዴት በመሥራት ላይ እንዳለች/እንዳለ
- በትምህርት ቅስሞሽ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የረጅም ጊዜ ግቦችና ይዘቶች

እዚህ መገለፅ ያለበት

- ተማሪዋ/ው ውጤት እንድታስመዘግብባቸው/እዲያስመዘግብባቸው በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን የተጣሉ የረጅም ጊዜ ግቦች የትኞቹ እንደሆነ ይዘረዝራል፡፡

ግቦቹም

- የተማሪዋ/ውን ፍላጎቶች መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው
- በተማሪው ጠንካራ ጎኖች ላይ የተገነቡ መሆን ይኖርባቸዋል
- የሚለኩ መሆን አለባቸው

– የሚተገበሩ መሆን አለባቸው

እነሱም ማካተት ያለባቸው

- ትምህርታዊ
- ማህበራዊ
- የባህርይ
- አካላዊ
- ሌሎች የትምህርት ፍላጎቶችን

ለእያንዳንዱ ግብ ቁጥር መስጠት ይቻላል

በተለይም ተማሪው የሽግግር ወቅት ላይ ሲደርስ የረጅም ጊዜ ግቦች መጣል አስፈላጊ ነው። ግቦች መጣል ያለባቸው በጥቅል መልኩ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ግብ ይጣላል።

የአጭር ጊዜ ግቦችና ይዘታቸው፤

እነዚህ ግቦች የአጭር ጊዜ ግቦች ከ1 እስከ 6 ወራት ወይም ከዚያ ላጠረ ጊዜ የሚነደፉና የአጭር ጊዜ ውጤቶችን ኢላማ ያደረጉ ናቸው፤ መገለፅ ያለበትም፤

- የተማሪዋ/ው ውጤት እንድታስመዘግብባቸው/እዲያሰመዘግብባቸው በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን የተጣሉ የአጭር ጊዜ ግቦች ምን ምን እንደሆኑ ነው።

ግቦቹም

- የረጅም ጊዜ ግቦችን መሠረት ያደረጉና የተጣጣሙ መሆን አለባቸው
- በተማሪዋ/ው ፍላጎቶች ላይ መመስረት አለባቸው
- የሚለኩ መሆን አለባቸው
- ሊተገበሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው
- በአጭር ጊዜ ውጤት የሚመዘገብባቸው መሆን አለባቸው (ከ1-6 ወራት)

የእነሱም ሂደት ከረጅም ጊዜ ግብ አኳያ የሚለካ ሆኖ መዘጋጀት አለበት

እያንዳንዱ የረጅም ጊዜ ግብ ቢያንስ አንድ የአጭር ጊዜ ግብ አለው

የአጭር ጊዜ ግቦች ቁጥሮች የረጅም ጊዜ ግቦች ቁጥሮች ነፀብራቅ መሆን አለባቸው።

ዘዴዎች

የማስተማሪያ ዘዴዎች የረጅምና የአጭር ጊዜ ግቦች ውስጥ በጥንቃቄ ታስቦ መካተት አለባቸው። ይህም ተማሪዋ/ውን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ለመወሰን ያስችላል።

እዚህ የሚገለፀው፤

- ተማሪውን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ስትራቴጂዎችን/ዘዴዎችን
- ትምህርቱን በማስማማት ለማስተማር ያወጣሽው/ያወጣኸው እቅድ ይሆናል።

የቁሳቁሶች አቅርቦት

እዚህ ሊገለፅ የሚገባው፤

- አስፈላጊ የሆኑ ምቹ/ተስማሚ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን
- በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችና አገልግሎቶችን ነው።

አደረጃጀትና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢ

እዚህ መገለፅ የሚገባው፤

- የታቀዱ ምቹ የአደረጃጀት ሁኔታዎችንና
- የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢን ምቹ ለማድረግና እንደገናም የተዘጋጀ ነገር ካለ ነው።

በት/ቤትና ከት/ቤት ውጪ የሚሰጥ ድጋፍ

እዚህ የሚካተተው፤

- ተማሪዋ/ው የምታገኛቸው/ የሚያገኛቸው የአገልግሎት አይነቶች
- ለምን ያህል ጊዜ አገልግሎቱን እንደምታገኝ/እንደሚያገኝ ለምሣሌ በሳምንት ሁለት ጊዜ፣ በየቀኑ ..ወዘተ
- ይህ ድጋፍ የሚሰጠው ከየት እንደሆነና
- ሰጭው ክፍል/አካል/ ማን እንደሆነ ይገለፃል።

የምዘና መርሆዎች

ምዘና ተማሪዋ/ው በምታስመዘግበው/በሚያስመዘግበው ውጤቶችና በትምህርት ቅስሞሽ ሂደቶች ላይ እንዲያተኩር መደረግ አለበት፤

እዚህ መገለፅ ያለበት፤

- የተማሪዋ/ው መሻሻል እንዴት እንደተገመገመ/እንደተመዘነ
- ግመገማው/ምዘናው መቼ እንደሚካሄድና እንደተካሄደ

• ማን እንደገመገመውና ተጨማሪ የማሻሻል ስራ ቢያስፈልግ ይዘቱ ምን መሆን እንዳለበት ይገለፃል፡፡
የሚቀጥለው የማሻሻያ ቀን

የቡድኑ አባላት ፊርማ (ርዕሰ መምህር ፣ መምህር፣ የልዩ ትምህርት መምህር/ ተዘዋዋሪ መምህር፣ ወላጅ /አሳዳጊ ፣ ተማሪዋ/ው)

1. _____ 2. _____

3 _____ 4. _____

4.7 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን መተግበር

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ከተዘጋጀ በኋላ መተግበር ይኖርበታል፡፡ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን ለተማሪዋ/ው የተጣሉትን ግቦች በተሻለ ሁኔታ ለመምታት ያስችላል ብሎ የለያቸው እንደ ተጨማሪ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አገልግሎቶችና የፕሮግራም መሻሻሎች የመሳሰሉት ተማሪዋ/ው በአጠቃላይ ስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በመካተት መሻሻል እንድታሳይ/እንዲያሳይ ይረዳታል/ ይረዳዋል፡፡ ስለተማሪዎቹ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አተገባበር ከዚህ በላይ በዝርዝር ማካተቱ ከዚህ መመሪያ አላማ ውጪ ቢሆንም መሠረታዊ ሃሳቦቹን ግን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን ለመተግበር በአገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ የተካተተ እያንዳንዱግለሰብ ኃላፊነቱን ጠንቅቆ መረዳትና መወጣት አለበት፡፡ ይህም ተማሪው በእቅዱ መሠረት አገልግሎት እንዲያገኝ ይረዳዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አባላት እንደየአስፈላጊነቱ ለማሻሻልና ለማካተት የለዩዋቸውን ነገሮች ለመጨመር ያስችላል፡፡
- የቡድን ሥራ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን ለመተግበር ጠቃሚ ሚና ይጫወታል፡፡ ለተማሪዋ/ው ድጋፍና ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ብዙ ባለሙያዎች ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ልምድን መለዋወጥና ነገሮችን በትኩረት መመልከት የእያንዳንዱን ሰው ሥራ ከማቅለሉም ባሻገር ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ውጤት እንደሚያሻሽል በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡
- ትምህርት ቤቶች ለመምህራን፣ ለድጋፍ ሰጪ አካላት ለወላጆችና ወይም ለሌሎች ባለሙያዎች በቡድን እንዲሰሩ ጊዜ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም እቅድን ለማዘጋጀት

ወይም ሥርዓተ ትምህርቱን በማስማማት የልጅቱን/የልጁን ልዩ ፍላጎት ለማርካት ያስችላል፡፡

- በቤትና በትምህርት ቤት መካከል ያለው ግንኙነት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ወላጆች እቤት ውስጥ ምን እየተከናወነ እንደሆነ መረጃ ይሰጣሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዋ/ው በትምህርት ቤት የተማረችው/የተማረው ላይ ሃሳብ በመጨመር እውቀታቸውን ይገነባሉ፡፡ ልጅቷ/ልጁ በትምህርት ቤት ችግር ከተፈጠረባት/ከተፈጠረበት ወላጆች የተፈጠረውን ችግር በመለየት ሂደት ውስጥ ለትምህርት ቤቱ እገዛ ያደርጋሉ፡፡የመፍትሄ ሃሳብም ይጠቁማሉ፡፡
- ተማሪው የሚያገኘውን የድጋፍ አገልግሎት የሚያስተባብርና የሚከታተል አንድ ኃላፊነትየተሰጠው ሰው ቢኖር ጥሩ ነው፡፡ ከልዩ ፍላጎት ትምህርት በተጨማሪ ተማሪው ተዛማጅ የሆኑ የተለያዩ አገልግሎቶችን ሊያገኝ ይችላል፡፡ የሚሰጡት አገልግሎቶች በእቅዱ መሠረት መሆናቸውን የሚከታተል ሰው መኖሩ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብሩ በአግባቡ መተግበሩን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡
- የመደበኛ ሪፖርቶች መኖር ወላጆችና ትምህርት ቤቶች ልጅቷ/ልጁ ከአመታዊ ግቡ አንፃር ለውጥ እያሳየች/እያሳየ መሆኗን/መሆኑን ለመከታተል ያስችላል፣ ልጅቷ/ልጁ የሚጠበቀውን ያህል ለውጥ አለማሳየቷን/አለማሳየቱን ወይም ከሚጠበቀው በላይ ፈጥና/ፈጥኖ ለውጥ ማሳየቷን/ማሳየቱን ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ የልጅቷ/የልጁ ፍላጎቶች ከታወቁ ወላጆችና የትምህርት ቤት ኃላፊዎች እነዚህን ፍላጎቶች ለማርካት በጋራ መስራት ይችላሉ፡፡
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር በትምህርት ቤትም ሆነ በሌሎች አውዶች በእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴ ውስጥ መተግበር አለበት፡፡ ተማሪዋ/ው በምትሳተፍባቸው/በሚሳተፍባቸው ሁሉም ተግባራት ውስጥ የተለያዩ ድጋፎች ሊደረጉላት/ሊደረጉለት ይገባል፡፡ ይህም ማለት አብዛኛውን ጊዜ ሌሎች ተማሪዎች በአማራጭ የአጠናንና አሰራር መንገዶች ሊጠቀሙ ይችላሉ (ከመፃፍ ይልቅ በንግግር ማቅረብን፣ እንደችሎታዋ/ው በተግባር መሣተፍ)፡፡ ለተለያዩ ሁኔታዎች ተግባራዊ የሚሆኑ የመፍትሄ ሃሳቦች በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የእቅድ ስብሰባ ላይ ለውይይት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር በክፍል ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት እንደማዕቀፍ ሆኖ ያገለግላል፡፡ መምህራን በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ሁሉንም ተማሪዎችን ለማርካት የሚያስችል ተግባራዊ የመፍትሄ ሃሳቦችን ማፈላለግ ይኖርባቸዋል፡፡ በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርና በመደበኛው ሥርዓተ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ስለሚገኙ የክፍል ውስጥ የማስተማር ሥራው ከነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አባላት ጋር በመሆን በጥንቃቄ

መታቀድ አለበት ። እነዚህ የማስተማር ሥራዎች የሥርዓተ ትምህርቱን ይዘቶች ልጅቷ/ልጁ እንድትማር/ እንዲማር ሊረዱ የሚችሉ ክሂሎችን ማስተማርን ያጠቃልላል።

በአካቶ ትምህርት አሰጣጥ በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የሚማሩ ተማሪዎች ድጋፍ እየተደረገላቸው በመደበኛው ትምህርት ውስጥ ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር አብረው ይማራሉ። ዋናው ሃሳብም የተማሪዋ/ውን ግቦች በእለት ተእለት ተግባራት ውስጥ ለማካተትና የሚሰጠው ድጋፍ መጠን ውጤታማ፣ የነፍስ-ወከፍና ምቹ በማድረግ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ወጣቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ነው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብሩ ተማሪዋ/ው በክፍል ውስጥ በሚካሄዱ ተግባራት ውስጥ ምን ያህል መሳተፍ እንዳለባት/እንዳለበት ማብራሪያ ይሰጣል።

4.8 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን መመዘን

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የሚመዘነው ተማሪዋ/ው ያመጣ/ች/ውን ለውጥ ከተቀመጠው አላማ ጋር በማወዳደር ነው። ይህም ማለት ትምህርቱን እንዴት መቀጠል እንደሚቻል ውሳኔ ለመስጠት ያስችላል። ምዘና የአንድ ጊዜ ሥራ ሳይሆን ተከታታይ ሂደት ነው። የዚህ ምዘና ሂደት አላማም ስለተማሪዋ/ው የትምህርትአሰራር አቀባበልና ያሳየ/ች/ው ለውጥ ለመምህራንና ለወላጆች መረጃ ለማቅረብ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ምዘናው በቀጣይ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ያመለክታል።

የምዘና መርሆዎች

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን ስንጠቀም፤ ቡድኑ የተለያዩ ጠቃሚ ክሂሎትና ሂደቶችን የያዙ መመዘኛዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን መመዘኑ ጠቀሜታ አለው። እነዚህ ሂደቶችም ከአንድ ዓይነት ባህርይ ይልቅ ሰፊ ዓላማዎች ያሉትን የትምህርት ቅስሞሽ ውጤቶችን ያሳያሉ። ይህም በነፍስወከፍ የሚሰጠውን ድጋፍ ለማሻሻል ይረዳል። (Grisham —Brown etal: 2002)

የሚመዘኑት ምን ዓይነት ፍላጎቶች ናቸው?

- የትምህርት ክሂሎት
- ማህበራዊ ክሂሎት
- የባህርይ ክሂሎትና
- የግንዛቤ ክሂሎት ናቸው።

ግቦቹ በሚገለፁበት ጊዜ ምዘናውም ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል። የማህበራዊና ባህርይ ግቦች እንደተጨማሪ እንጂ የሥርዓተ ትምህርቱንና ተዛማጅ ግቦችን የሚተኩ ሆነው መታየት የለባቸውም።

ተማሪዎች ስለራሳቸው ያላቸውን ግምትና የግንዛቤ ክሂሎት እንዲያዳብሩ ግለምዘና እንዲያካሄዱ ይበረታታሉ(ተቀጺላ 5, ግለ-ምዘና ቅፅ)፡፡

ምዘና ማስረጃን የመፈለግና የመተንተን ሂደት ሲሆን ይህም ተማሪዎቹ በትምህርታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ የት ሊሄዱ እንደሚችሉና የሚሄዱበት ቦታ ምን ያህል ምቹ እንደሆነ ለመወሰን ለተማሪዎቹም ለመምህራኑም ይረዳል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ባለሙያዎች ተማሪዋ/ው ያገኘ/ች/ውን መልካም አጋጣሚ ተጠቅማ/ሞ የሥራ ውጤቷን/ ውጤቱን በአግባቡ ማሳየት መቻሉን ሊያምኑበት ይገባል፡፡ ይህም ተማሪዋን/ውን የትምህርት ውጤትና የተግባር ክንውኖች በአግባቡ ለመመዘን በግል የምትሰራበት/ የሚሰራበት ምቹ ቦታ ሊያስፈልግ ይችላል

የምዘና መርሆዎች በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቅፅ ውስጥ መገለፅ አለባቸው፡፡

- ምዘና የነፍስ ወከፍ መርሃ ግብሩን ግቦች መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣
- የሚለኩ ወይም በገለፃ መልክ ሊመዘኑ የሚችሉ ግቦችን መምረጥ ይገባል፤
- ወደ ግቦቹ ለመድረስ እየተረገ ያለው መሻሻል እንዴት እንደሆነ ተከታታይ ምልከታና ግምገማ ማካሄድ ይጠበቃል፤
- ግለ-ምዘናን መካተቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር በሚዘጋጅበት ወቅት ቡድኑ ስለክትትል በእቅዱ ሰነድ ውስጥ በግልፅ ማስቀመጥ አለበት ፡፡ ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል

- ክትትል በምን ላይ ይደረጋል፣
- ክትትል የሚያደርገው ማነው ፣
- መቼና የት ክትትሉ ይደረጋል፣
- መረጃው እንዴት ሪፖርት ይደረጋል የሚሉትን መመለስ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

4.9 የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቅፅን መፈራረም

በሚከተሉት የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ላይ በመፈራረም ሁሉም ተሣታፊዎች ለሂደቱ መሣካት ቁርጠኝነታቸውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- የትምህርት ቤት አመራሮች ለተማሪው የነፍስ ወከፍ ድጋፍ ለመስጠት ጥረት እንደሚያደርጉ ማረጋገጥ አለባቸው፣

- ወላጆች/አሳዳጊዎች በሥርዓተ ትምህርቱና በምዘና ሂደቱ ላይ የተደረገውን ለውጥ መቀበል አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዋ/ው የተጣሉትን ግቦች ለማሳካት ቁርጠኛ መሆናቸውን መግለፅ አለባቸው፡፡

ተቀፅላ 1፡ የትምህርት ቅስሞች መንገዶች (learning Styles)

ተማሪዎች በመነካካት፣ በማየት እና በማዳመጥ ሊማሩ ይችላሉ፣

በመነካካት የሚማሩ	**በማየት የሚማሩ**	**በማዳመጥ የሚማሩ**
• እጅግ በተሻለ ሁኔታ የሚማሩት • በመስራትና በመንቀሳቀስ ነው፣ • በተግባር ሥራ ውስጥ ይሳተፋሉ፣ • በፕሮጀክት፣ በፈጠራ ሥራ ፣ በሚና ጫወታ፣ በእውነታ የህይወት ጨዋታ ይሳተፋሉ • ቆመው ይማራሉ፣ • መቀመጥ አይወዱም፣	• እጅግ በተሻለ ሁኔታ የሚማሩት በማየት ነው፡፡ ስዕሎችን፣ ግራፎች፣ ስላይዶች፣ ፊልሞች ተግባራትን በመመልከት ይማራሉ፡፡	• እጅግ በተሻለ ሁኔታ የሚማሩት በማዳመጥ ነው • እራሳቸው ለራሳቸው ወይም ከሌሎች በሚሰጣቸው የንግግር መመሪያ ይማራሉ • ያዳመጡትንለራሳቸው ይደግማሉ
<u>በንባብ ጊዜ</u> ፡- ሲያነቡ እንቅስቃሴ ያበዛሉ ፊደል ይገድፋሉ፣	**<u>በንባብ ጊዜ</u>** ፡- በመመልከት ፊደሎችን ይለያሉ፡፡ በተማሪው የመማሪያ መፅሐፍና በመልመጃ ወረቀቶች ላይ በደንብ ይሰራሉ፡፡	**<u>በንባብ ጊዜ</u>** ፡- ጮክ ብለው ያነባሉ፣ በራሳቸው ድምፆች ቃላትንያወጣሉ፡፡
<u>በፅህፈት ጊዜ</u>፡- ሲጀምሩ ጥሩ ይፅፋሉ እየቀጠሉ ሲሄዱ በቃላት መካከል የሚሰጡት ቦታ እያነሰ አፃፃፋቸውም እየተበላሸ ይመጣል፡፡	**<u>በፅህፈት ጊዜ</u>፡-** የፊደል አጣጣልና በቃላት መካከል የሚሰጡት ቦታ ጥሩ ነው፡፡ አፃፃፍ ያሳምራሉ፡፡	**<u>በፅህፈት ጊዜ</u>፡-** ሲፅፉ አይጫኑም፣ በትላልቅና በትናንሽ ፊደላት (Capital & Small) መካከል ልዩነት የለም፡፡
<u>የችግር አፈታት ዘዴ</u>፡- በድፍረት ለመፍታት ይጋፈጣሉ፡፡	**<u>የችግር አፈታት ዘዴ</u>፡-** በቅድሚያ ያቅዳሉ ከዚያም ችግሩን በቅደም	**<u>የችግር አፈታት ዘዴ</u>፡-** ስለችግሩ ያወራሉ፣ በንግግር መፍትሄ

በመነካካት የሚማሩ	በማየት የሚማሩ	በማዳመጥ የሚማሩ
	ተከተል ያስቀምጣሉ፣ ሥርዓት ባለው መንገድ ይሰራሉ፣	ለመስጠት ይሞክራሉ፣
ማስታወስ፡- ካዩትና ከሰሙት ይልቅ በተግባር የሠሩትን ያስታውሳሉ፡፡	**ማስታወስ**፡- ያዩትንና የፊት ገፅታን ያስታውሳሉ፣ ስም ይረሳሉ፣ የሚፈልጉትን በማስታወሻ ይፅፋሉ፣	**ማስታወስ**፡- ስም ያስታውሳሉ ፣ የፊት ገፅታን ይረሳሉ፡፡ በመደጋገም በቀላሉ ይሸመድዳሉ፡፡
በአዲስ ሁኔታ፡- አዲስ አካባቢ ሲገጥማቸው ነገሮችን በመነካካት ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡	**በአዲስ ሁኔታ**፡ አካባቢያቸውን ይቃኛሉ፡፡ የነገሮችን እንቅስቃሴና ሰዎችን ያያሉ፡፡	**በአዲስ ሁኔታ**፡ ስለአካባቢው ሁኔታ ይናገራሉ፣ ጥያቄ ይጠይቃሉ፣
የስሜት አገላለፅ ፡- በደስታ ጊዜ ይዘላሉ፡፡ ሲናደዱ መሬቱን ድምድም እያደረጉ ይሄዳሉ፡፡	**የስሜት አገላለፅ** ፡- ሲናደዱ ትክ ብለው ያያሉ፡፡ ሲደሰቱ ፈገግ ይላሉ፡፡ የፊት አገላለጣቸው የስሜታቸው ጥሩ መገለጫ ነው፡፡	**የስሜት አገላለፅ**፡- ስሜታቸውን በንግግራቸው ውስጥ የድምፃቸ ውን ቃና፣ ከፍታ ወይም የድምፅ አወጣጥ በመለዋወጥ ይገልፃሉ፡፡
ተግባቦት ሲናገሩ አካላቸውን ያንቀሳቅሳሉ ፡፡ በንግግራቸው ውስጥ ማግኘት መውሰድ ወዘተ የመሣሰሉትን ቃላት ይጠቀማሉ፣	**ተግባቦት**፡- ዝምታ ያበዛሉ፣ ለረጅም ጊዜ አይናገሩም፣ በንግግራቸው ውስጥ ተመልከት፣ እይ ወዘተ የመሳሰሉትን ቃላት ይጠቀማሉ፣	**ተግባቦት**፡- ረጅም ገለፃ ይሰጣሉ፣ በንግግራቸው ውስጥ አድምጥ፣ ስማ ወዘተ የመሣሰሉትን ቃላት ይጠቀማሉ፣
ሥራ በሚፈቱበት ጊዜ የሚፈጥሩት መስተጋብር፡- እንቅስቃሴ ያበዛሉ፣ ቦታቸውን ለቀው ለመሄድ ምክንያት ይደረድራሉ <ለመስራት> የሆነ ነገር ያመጣሉ	**ሥራ በሚፈቱበት ጊዜ የሚፈጥሩት መስተጋብር**፡- ትክ ብለው ያያሉ በአእምሯቸው ውስጥ የሆነ ነገር ሥዕል ፈጥረው ያሰላስላሉ፡፡ የሚታይ ነገር ይፈልጋሉ፡፡	**ሥራ በሚፈቱበት ጊዜ የሚፈጥሩት መስተጋብር**፡- በዝቅተኛ ድምፅ ያንሾካሿኳሉ፣ ይዘምራሉ፣ ለራሳቸው ወይም ለሌላ ሰው ያወራሉ፡፡
ውጫዊ ገፅታ ፡- ንፁህ ናቸው ነገር ግን ተግባራትን ሲያከናውኑ ልብሳቸው ይጨማደዳል፣	**ውጫዊ ገፅታ** ፡-ንፁህ ናቸው፣ ጥንቃቄ ያበዛሉ፣ ሥርዓት ያለው ነገር ይወዳሉ፣ ስለአለባበሳቸው ግድ የለሽ ናቸው፡፡	**ውጫዊ ገፅታ** ፡- ለተጣመረና ሳቢ አለባበስ ግድ የላቸውም፡፡ ልብሳቸውን ለምን እንደሚመርጡ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

የጋርድነር ሰባት ጉብዝናዎች (Gardner H -1983)

የጉብዝናው ዓይነት	ባህርያትና ጠንካራ ጎኖች	የማነሳሻ/የመቀስቀሻ መንገዶች፣ የሚገኝ ጥቅም
የንግግርና - ሥነልሳን	የህትመት ወይም የንግግር ቃላት፣ ንባብ፣ ፅሁፍ፣ ንግግርን ማስታወስ፣ በእይታ ሁኔታዎችን መረዳት	ማንበብ፣ ማዳመጥና መፃፍ፣ ጋዜጣ መያዝ፣ማስታወሻ መያዝና የጥናት መመሪያ ማዘጋጀት፣ ለማስታወስ የሚረዱ ቃላትን በመያዝ እያነበበ በድምፅ ማጫወቻ መሣሪያ የሚተላለፍ ነገርን ጽሁፉን በመከታተል ማዳመጥ
ሳይንሳዊ አስተሳሰብ	ቁጥሮችእውነታ ቅደም ተከተል፣ ረቂቅ ሃሳብ፣ የነገሮችን አካሄድ መረዳት	ዲያግራም መፍጠር፣ ነገሮችን ማወዳደር፣ ምክንያታዊነት በመጠቀም ትንተና መስጠት፣ እራስን ችሎ ማጥናት፣ ላብራቶሪ፣ ጥናትና ምርምር፣ ፕሮጀክቶችን መስራት፣
አካላዊ እንቅስቃሴ መነካካት	መንቀሳቀስ፣አካላዊ ተግባራትን ማከናወን	ሰርቶ ማሣየት፣ ድራማ መስራት፣ ጌሞችን መጫወት፣ መራመድ፣ መደነስ፣ የሚና ጨዋታ የእግር ጉዞ
ሥርጭትን በእይታ መገንዘብ (Visual - Spatial)	ሥዕሎች፣ በእይታ መሣል (Visual —images)	በስዕልና በቅርፅ መወከል፣ የቀለም ቅብ፣ ፓርቲፎሊዮ መፍጠር
ሙዚቃ (የድምፅ አወራረድ)	የድምፅ ምትና ቃና	ሙዚቃ መቀመር፣ መዘመር፣ ማድመቂያ ሙዚቃን መፍጠር
በሰዎች መካከል ያለግንኙነት	ተግባቦት፣፣ ከሌሎች ጋር መተባበር	ጮክ ብለህ ለጓደኛህ ንገረው፣ በቡድን መሥራት መተጋገዝ፣ በንግግር ሪፖርት ማቅረብ፣
ውስጣዊ አስተሳሰብ (Intra Personal)	ምልከታ፣ ቁጭ ብሎ ለተወሰነ ጊዜ ማሰብ፣ የራሱ ግምት ነፀብራቅ፣	ማስታወሻ መያዝ፣ የነፍስ ወከፍ ፓርቲፎልዮ እራስን ችሎ ማጥናት

- እንደመምህራን፣ ልምዳችን የሚያረጋግጥልን ተማሪዎች መረጃንና ችግሮችን የሚገነዘቡት በራሳቸው በተለየ ማጣሪያ በማጣራት መሆኑ፤

- የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበል ዘዴ መምህሩ ከሚያስተምርበት ዘዴ ጋር ካልተጣጣመ ለመማር ችግሮች የሚጋለጡ ተማሪዎች መኖራቸውንና
- የተማሪዎቹን የትምህርት ቅስሞሽ ባህርያትን ማርካትና አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው መስራት ማካተትና ለሁሉም ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት ጠቃሚ መሆኑን ነው፡፡

በመጨረሻም

- ተማሪዎች በተለያየ መንገድ እንዲያስቡ ወይም አስተሳሰባቸው ተለማጭ እንዲሆን ማበረታታት ፣
- በክፍል ውስጥ ለሚነሱ የተለያዩ ሃሳቦች ዋጋ በመስጠት ምንጊዜም የተለያዩ ሃሳቦችን ማስተናገድ፤
- በውይይት ወቅት እያንዳንዱን ሃሳብ ማድነቅና በጥቁር ሠሌዳ ላይ ፅፎ ማስገንዘብ ተገቢ መሆኑን ነው፡፡

ተቀፅላ 2፡ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቅፅ

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቅፅ (የተማሪው ስም)

I. **ግለ ታሪክ መረጃ**

የተማሪዋ/ው ሥም **የተወለደ/ች/በት ቀን**	**አድራሻ**
ወላጅ/አሳዳጊ	**ስልክ ቁጥር** **አድራሻ**
የትምህርት ቤቱ ሥም	• **ይህ ዶክመንት የተዘጋጀበት ቀን** • **ይህ ዶክመንት የተሻሻለበት ቀን**
የመምህራኑ ሥም	

II. ግቦች ፣ የድጋፍ ዓይነቶችና ምዘና

የተማሪው ብቃት (ጠንካራ ጎኖች)

በትምህርት ቤት የተማሪው ሁኔታና የመማር ችግሮች መግለጫ
የረጅም ጊዜ ግቦችና ይዘቶች
የአጭር ጊዜ ግቦችና ይዘቶች
ዘዴዎች
የቁሳቁሶች አቅርቦት
አደረጃጀትና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢ

የትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጪ የሚደረጉ የድጋፍ ዓይነቶች

የምዘና መርሆዎች
የሚቀጥለው የማሻሻያ ቀን

የቡድኑ አባላት ፊርማ

1. _____ 2. _____

3. _____ 4. _____

ተቀፅላ 3፡ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ናሙና 1

ናሙና ቅፅ 1

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ለአለሚቱ ተ.

I. ግለ ታሪክ መረጃ

ተማሪዋ ሥም ፡ አለሚቱ ተ.	አድራሻ፡ ደ/ብ/ብ/ህ/ክልል xx ዞን YY ከተማ ከፍተኛ 1 ቀበሌ 02

የተወለደችበት ቀን ፡- 14/10/92	(የቤት ጉብኝት የሚደረግ ከሆነ ይህ መረጃ በጣም ጠቃሚ ነው)
ወላጅ /አሳዳጊ • አቶ ተ.ደ. አባት • ወ/ሮ ከ.ደ. አናት	**ስልክ ቁጥር**…… **አድራሻ** ፡ደ/ብ/ብ/ህ/ክልል xx ዞን YY ከተማ ከፍተኛ 1 ቀበሌ 02
የትምህርት ቤቱ ሥም ፡- xx የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት	• **ይህ ዶክመንት የተዘጋጀበት ቀን** • ህዳር 10 ቀን 2003 • **ይህ ዶክመንት የሚሻሻልበት ቀን**
የመምህራኑ ስም • አቶ መ.በ. የክፍል ኃላፊ መምህር • ወ/ሮ ሀ.አ. የሂሳብ መምህርት • አቶ ተ.ወ. የልዩ ትምህርት መምህር • አቶ ገ.መ. የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር	

II. ግቦች፣ የድጋፍ ዓይነቶችና ምዘና

የተማሪዋ ብቃት (ጠንካራ ጎኖች)፡ አለሚቱ እድሜዋ 11 ዓመት ሲሆን የ5ኛ ክፍል ተማሪ ናት። አለሚቱ ንቁና ቅን አሳቢ ልጅ ስትሆን ትምህርት ቤት መሄድ ትወዳለች። ብዙ ጓደኞችም አሏት። የአብዛኞቹን ትምህርቶች የቤት ስራዋን እራሷን ችላ ትሠራለች።

በትምህርት ቤት የተማሪው ሁኔታና የመማር ችግሮች መግለጫ፡ የሚሠራው ተግባር ረጅም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ አለሚቱ የትኩረት ማጣት ችግሮች ይታዩባታል። ከዚህም በተጨማሪ የተሰጣትን መመሪያ ዝርዝር ሁኔታዎች ወይም መረጃዎች ማስታወስ ትቸገራለች። አለሚቱ ከፍተኛ ችግር የሚታይባት በሂሳብ ሲሆን በተለይም ማባዛት ነው።

የረጅም ጊዜ ግቦችና ይዘቶች • ለረጅም ጊዜ ትኩረት እንደትሰጥ ችሎታዋን ማዳበር • ትውስታዋን የምታዳብርበት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ማስተማር • የሂሳብ መሠረታዊ ክሂሎት ማዳበር፡ ከ1-10 ባሉ ቁጥሮች ማባዛትን ያለደጋፊ እንድታሰላ ማሳወቅ
የአጭር ጊዜ ግቦችና ይዘቶች • ልታስታውሳቸው የማትችላቸውን ተግባራት ለማስታወስ የትውስታ ዘዴዎችን ወይም ከሌሎች ነገሮች ጋር በማዛመድ የምታስታውስበትን መንገድ ማሳየት • ከ1-4 ያሉ ቁጥሮችን ማባዛት ማስተማር
አደረጃጀት፣ ዘዴዎችና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢ በሁሉም ክፍለ ጊዜያት በክፍል ውስጥ አለሚቱ ከመምህሩ በአጭር ርቀት ብቻዋን በአንድ ዴስክ ላይ መቀመጥ ይኖርባታል። ረጃጅም ተግባራትን ወደ አጫጭር ተግባራት መከፋፈልና በየተግባራቱ መካከል እረፍት እንድትወስድ ማድረግ። ረጅም ተግባራትን ማከናወን ቀስ በቀስ የምታዳብረው ችሎታ ነው። አለሚቱ እንድታስታውሳቸው የሚገቡ ነገሮች ትኩረት ተደርጎበት ሊነገራት ይገባል። በመጀመሪያ እንድታስታውሳቸው የሚገቡ ነገሮች ትንሽ ስለሚሆኑ በቃል ይነገራታል። ከዚያም መረጃው ወደ ፅሁፍ ይለወጣል።

አለሚቱ ትውስታዋን ሊያካክስላት የሚችል ስትራቴጂ መማርና የማስታወስ ችሎታዋን ማዳበር ይኖርባታል። **ሂሳብ** • የብዜት ክሂሎትን ሊያዳብሩ የሚችሉ ተግባራትን መስራት አለባት (በተለይም መደመር) • ወደ ቀጣይ ተግባራት ከማለፏ በፊት ከ1-4 ያሉ ቁጥሮች ላይ በማተኮር የገባት መሆኑ መረጋገጥ አለበት • አስቸጋሪ ተግባራት ሲገጥሟት በክፍል ውስጥ የወሰደችውን ማስታወሻ ደብተር በማንበብ ለማስታወስ ልትገለገልበት ትችላለች።

የቁሳቁሶችአቅርቦት ፡-

- በትንንሽ ምዕራፎች የተዘጋጁ የሚነበቡ ፅሁፎች፣
- ተግባራትን ለማከናወን የሚረዱ በፅሁፍ የተዘጋጁ መመሪያዎች፣
- ሊታወሱ የሚገባቸው ነገሮች ዝርዝር በፅሁፍ መልክ የተዘጋጀ፣
- ለሂሳብ የሚያስፈለጉ ቁሳቁሶች በሁዋላ በዚህ ቅፅ ላይ ይገለፃሉ፣

ከትምህርት ቤት ውጪ የሚያስፈልግ ድጋፍ፣ በቤት ውስጥ አለሚቱ የቤት ሥራዋን በራሷ እንድትሠራ መበረታታት አለባት። ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እርዳታ መጠየቅ ትችላለች። የቤት ሥራዋን የምትሠራበት ቦታ በተቻለ መጠን ፀጥታ የሰፈነበት መሆን ይኖርባታል። እሷም የትውስታ ጨዋታዎችን ከወንድሞቿና ከእህቶቿ እንዲሁም ከእናቷ ጋር እንድትጫወት ማበረታታት ያስፈልጋል።

የምዘና መርሆዎች፣ የአለሚቱ ውጤት የሚመዘነው በአጠቃላይ ትምህርቱ የሁሉም የትምህርት አይነቶች ውጤትአንፃር ነው። አስፈላጊ ከሆነ በምዘና ወቅት በቃሏ እንድትይዛቸው የተሰጧት ነገሮች ዝርዝርን እንድትጠቀም ሊፈቅድላት ይገባል። ምዘናውም የሚያተኩረው በልጅቷ የነገሮች መረዳትና በመረጃ አጠቃቀም ችሎታዋ ላይ ነው።

አለሚቱ በትኩረት ክሂሎቷ ላይ የቃል ግብረ-መልስ ማግኘት አለባት። ከዚህ በተጨማሪ አለሚቱ ግለ ግምገማ በማድረግ በየሳምንቱ ከመምህሯ ጋር ትወያያለች ።

ሂሣብ፡-

- በውጤቷ ላይ የመጣውን ለውጥ በየጊዜው መከታተል
- ግለግምገማና በሁኔታው ላይ ውይይት ማድረግ
- በምዘናው መሠረት አስፈላጊ ከሆነ መምህሩ ግቦቹን ሊከልሳቸው ይችላል። የአጭር ጊዜ ግቦች በተሰጠው ድጋፍ መጨረሻ ላይ ይከለሳል።

የሚከጥለው የማሻሻያ ቀን

የቡድኑ አባላት ፊርማ 1. _____ 2._____ 3._____ 4. _____

ተቀጽላ 4፡ የነፍ ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር ናሙና 2

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃግብር ለጉደታ ፈ.

I: ግለታሪክ መረጃ

ተማሪው ***ሥም*** ፦ ጉደታ ፈ. **የተወለደበት ቀን፤** 20/03/1990	**አድራሻ** ፦ ኦሮሚያ ክልል XX ዞን yy ከተማ ከፍተኛ 1 ቀበሌ 03 (የቤት ጉብኝት ሲያስፈልግ ይህ በጣም ጠቃሚ መረጃ ነው፡፡)
ወላጅ/አሳዳጊ፥ • አቶ ፈ.መ. አባት • ወ/ሮ ለ.መ እናት	**የሥልክ ቁጥር** **አድራሻ** ፦ ኦሮሚያ ክልል XX ዞን yy ከተማ ከፍተኛ 1 ቀበሌ 03
የት/ቤቱ ሥም፥ XX የመጀመሪያ ደረጃ	• **ይህ ዶክመንት የተዘጋጀበት ቀን**

ት/ቤት	ጥቅምት 7 ቀን 2003 ዓ.ም • **ይህ ዶክመንት የሚሻሻልበት ቀን**
የመምህራን ሥም • ወ/ሪት መ.ሀ፤ የክፍል ኃ/ፊ መምህርት • አቶ ሰ.በ፤ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምር • አቶ በ.እ ፤ የልዩ ትምህርት መምህር • ወ/ሮ ከ.ተ፤ የት/ቤቱ ርዕሰ መምህርት	**አድራሻ፡** ኦሮሚያ ክልል XX ዞን yy ከተማ

II. ግቦች የድጋፍ አይነቶችና ምዘና

የተማሪው ብቃት(ጠንካራ ጎኖች)፡ ጉደታ የ13 ዓመት ልጅ ሲሆን የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ልጁ ንቁና በክፍል ውስጥ በሚሰጡ ተግባራት በፍጥነት ይሳተፋል፡፡
በትምህርት ቤት የተማሪው ሁኔታና የመማር ችግሮች መግለጫ፡ ፥ ጉደታ በመፃፍና በማንበብ ችግሮች ይታዩበታል ከጓደኞቹ ጋር መጫወትና በተግባራት ውስጥ መሣተፍ ይወዳል፡፡ ነገር ግን ከሱ ጋር የሚጫወቱት የክፍል ጓደኞቹ ጥቂቶች ሲሆኑ አብዛኞቹ ግን በሱ የመፃፍና የማንበብ ደካማ ክሂሎት ያላግጡበታል፡፡ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የንባብ ክፍለ ጊዜ መሳተፍ ቢወድም ብዙ ቃላትን ይገድፋል፡፡ የክፍሉ ተማሪዎች በእሱ ደካማ አነባበብ ይስቁበታል፡፡ በዚህም ምክንያት እሱ በተለይም በእንግሊዝኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ጓደኞቹና እንዲሁም በአጠቃላይ በት/ቤቱ ላይ አሉታዊ አመለካከት እያደገበት መጥቷል፡፡
የረጅም ጊዜ ግቦችና ይዘቶች • በራስ መተማመንን ማሳደግ • የማንበብና የመፃፍ ክሂሎት ማዳበር • የቃላት መረዳት ችሎታን ማዳበር • የቃላትን ትርጉም የመረዳትና በአግባቡ የመጠቀም ስትራቴጂዎችን መማር • ከላይ የተቀጠሉትንም በማድረግ አዎንታዊ አመለካከትን ማሳደግ • መሠረታዊ የማንበብ ክሂሎት ማሻሻል ናቸው፡፡

የአጭር ጊዜ ግቦችና ይዘቶች

- ብዙ መሠረታዊ ቃላትን ለማወቅ መጣር፣
- ቃላትን መገንዘብና በተሰጠው ምንባብ ውስጥ በትክክል ትርጉማቸውን ማስታወስ፣
- መሠረታዊ ቃላትን በመጠቀም አጫጭር አረፍተነገሮችን መሥራት/መሠረታዊ ቃላት የሚባሉት የትኞቹ እንደሆኑ በትክክል ትርጉማቸው ሊሰጥ ይገባል። ከአገር አቀፍ ሥርዓተ ትምህርቱ ጋርም መጣጣማቸው መታየት አለበት። በተጨማሪም የአረፍተነገሮቹ ደረጃ (የሚፃፈውና የሚነበበው) ትርጉም ሊቀመጥለት ይገባል።

አደረጃጀት፣ ዘዴዎችና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢ

በሁሉም ክፍለጊዜያት።

- ድምፅን የመለየትና የመረዳት ሥልጠና መሰጠት ይኖርበታል፤
- ቃላትን የመለየትና የመረዳትሥልጠና መሰጠት ይኖርበታል፤
- የአነባበብ ሥርዓትንና የዓረፍተነገር አረዳድን ለመለየት የሚያስችል ሥልጠና መሰጠት ይኖርበታል፤
- በቃሉ ሊይዛቸው ወይም ሊያስታውሳቸው የሚገቡ ቃላት በጥንቃቄ ይመረጣሉ፤
- በመጀመሪያ ጥቂት ቃላትን ያጠናል፣ ቀስ በቀስ ግን እየጨመረ ይሄዳል።

ጉደታ እንዴት የተለያዩ ስትራቴጂዎችን እየተጠቀመ ትውስታውን እንደሚያዳብርና ቃላትን ከድምፃቸውና ከትርጉማቸው ጋር በማስታወስ በተለያዩ አውዶች፣ መጠቀም እንዳለበት መማር አለበት፤

በአጠቃላይ በክፍሉ ውስጥ መደረግ ያለበት፡

- መደባደብ/ መተንኮስ በፍፁም የተከለከለ ነው፤
- ስህተት መስራት የተፈቀደ ነው፤
- የንባብን ክሂሎት የሚያጠናክሩ ተግባራት (በተለይም ቃላትን መለየትና መጥራት)
- በእንግሊዝኛ ቋንቋ ቃላት ድምጾች ላይ ማተኮርና ወደሚቀጥለው ተግባር ከማለፉ በፊት መረዳቱን ማረጋገጥ፤
- የፊደላትን ድምጾች እንዲጠራ ቃላትን እንዲያነብና እንዲሁም ትርጉማቸውን እንዲረዳ ማገዝ፤

ጉደታ ሳይሳቅበትና ሳይሳቀቅ ማንበብን እንዲለማመድ እድል ሊሰጠው ይገባል።

ሁሉም ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ፊት ቆሞ ሳይሆን በጥንድ ወይም በትንሽ ቡድን ውስጥ ማለማመድ ይገባል።

የቁሳቁሶችአቅርቦት ፡-

- የድምጽ መቅረጫ/ቴፕ ሪኮርደር/፣
- ስለድምፅ፣ስለቃላት፣ ስለዓረፍተነገሮች አነባበብ የሚያስረዱ የተቀረፁ ካሴቶች
- ቃላትን የሚወክሏቸው ስእሎችን መጠቀም
- ቀላል ቃላትንና አጫጭር አረፍተነገሮችን የያዙ የሚነበቡ ፅሑፎችን በትንንሽ ምዕራፎች አዘጋጅቶ መስጠት፣
- ተግባራቱን ለማከናወን የሚሰጡ መመሪያዎች በንግግር መስጠት አለበት፣
- ሊያስታውሳቸው የሚገቡ የነገሮች ዝርዝር በንግግር መስጠት አለበት፣

ከት/ቤት ውጪ የሚደረግ ድጋፍ፡

እቤት ውስጥ ጉደታ የቤት ሥራውን እራሱ እንዲሰራ ማበረታታት ያስፈልጋል። ነገር ግን አስፈላጊ ሲሆን እገዛ መጠየቅ ይችላል። የቤት ሥራውን የሚሰራበት ቦታ ፀጥታ የሰፈነበት ቢሆን ይመረጣል። በማንበብእየተጋዘ የማንበብ ክሂሎቱን እንዲያዳብር መበረታታት አለበት። ወላጆች ለጉደታ በግል ስለተሰጡት ተግባራት መረጃ እንዲኖራቸው ሊገለፅላቸው ይገባል።

የምዘና መርሆዎች

የጉደታ የትምህርት ውጤት ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት በስተቀር በሁሉም የትምህርት አይነቶች በአጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርቱ መሠረት መመዘን ይኖርበታል። በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ግን ምዘናው የሚካሄደው የተጣሉትን የነፍስወከፍ ግቦች መሠረት በማድረግ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ጉደታ በየሳምንት ሥራው ክንዋኔ ዙሪያ የቃል ግብረመልስ ማግኘት ይኖርበታል።

በፈተና ወቅት ብዙ የፅሕፈት ሥራ የሚጠይቁ የትምህርት ዓይነቶች ካሉ ጉደታ ፈተናውን በንግግር በመመለስ ችሎታውን እንዲያሳይ እድል ሊሰጠው ይገባል።

ጉደታ በእለት ተዕለት ተግባራቱ መደበኛ የሆነ የቃል መልስ ማግኘት ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ ግለ ግምገማ በማድረግ በየሣምንቱ ከመምህሩ ጋር መወያየት አለበት።
በምዘናው ውጤት መሰረት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መምህሩ ግቦቹን ሊከልስ ይችላል።
የአጭር ጊዜ ግቦች በተሰጠው ድጋፍ መጨረሻ ላይ እንደገና ሊጣሉ ይችላሉ።

በሚቀጥለው የማሻሻያ ቀን

የቡድኑ አባላት ፊርማ

1.---------- 2. ----------

3.---------- 4.----------

ተቀጺላ 5፡ የግለ ግምገማ ቅፅ

ከዚህ በታች የተሰጡ ምሳሌዎች የክፍለ ጊዜውን ርዕሰ በቀላሉ እንደተማሪው ችሎታ ለማሻሻል የሚረዱ ናቸው፡፡

1. በጣም አልስማማም 2. አልስማማም 3. አልወሰንኩም

4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

የተሰጠኝን መመሪያ ተረድቻለሁ	1	2	3	4	5
ካልተረዳሁ ከመምህሩ እገዛ እጠይቃለሁ	1	2	3	4	5
ካልተረዳሁ ከክፍል ጓደኞቼ እገዛ እጠይቃለሁ	1	2	3	4	5
በክፍለጊዜ ትኩረት ሰጥቼ መማር ችያለሁ	1	2	3	4	5
የቤት ሥራዬን ትኩረት ሰጥቼ መሥራት ችያለሁ	1	2	3	4	5
የቤት ሥራዬን ለመሥራት ሞክሬአለሁ	1	2	3	4	5
የቤት ሥራዬን መስራት ቀላል ሆኖ አግኝቼዋለሁ	1	2	3	4	5
ችግር ከገጠመኝ ከቤት እገዛ እጠይቃለሁ	1	2	3	4	5

ከ2-5 ባሉ ቀጥሮች ማብዛት እችላለሁ ----------

በ6 እና 7 ቁጥሮች ማብዛት እችላለሁ ----------

በ8 እና 9 ቁጥሮች ማብዛት እችላለሁ ----------

ተቀጺላ 6 ፡ የሥርአተ-ትምህርት ፅንሰ-ሃሳቦች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች

የአካል ጉዳት ዓይነት	መሠረታዊ የሥርዓተ ትምህርት ይዘት	አጠቃላይ የማስማማት ወይም የማሻሻል ሥራ
የአእምሮ እድገት ውስንነት	• ጥሞና ክሂሎት፣ • ትውስታ ክሂሎት፣ • ተግባራዊ ትምህርት /የሥራ ማመልከቻ መሙላትን፣ መሰረታዊ የመግባቢያ ቃላትን መማር፣ትውስታን መጠቀም፣ በንግግር መግባባትን ማዳበር/ • መምረጥ መቻል፣ • ትምህርት ቅስሞሽ ስትራቴጂዎች፣ • ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣ • የማደራጀት ክሂሎት፣ • ሃሳብን የማቃለል ክሂሎት፣ • ለራስ ተሟጋች መሆን፣	• እራስን ችሎ ህይወትን ለመምራት የሚያስችሉ ክሂሎትን ማለትም የእለት ተዕለት ተግባራትን በቤት በት/ቤት፣ በሥራ ቦታ ወይም በማህበረሰብ አካባቢ ለመስራት የሚያስችሉ እድሎችን ይፈጥራል ።(ጫማ ማሰር፣ ቢስኪሌት መንዳት፣ ከአንድ ክፍል ወደ ሌላ ክፍል መዘዋወር፣ለሰዎች በተገቢው መንገድ ሰላምታ መስጠት)የመሳሰሉትን ለመተግበር የሚያስችል ነው። • ተጨባጭ፣ እድሜን ያማከለ፣ በእውነተኛ ህይወት ላይ የተመሠረተ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን መጠቀም፤ • አዳዲስ ነገሮችን በቅደም ተከተል ማሳየት፣ መረዳታቸውን ማረጋገጥ፤ • በእያንዳንዱ ደረጃ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የመለያ ጥያቄዎችን መጠቀም፤ • የእይታ (አመልካች፣ ግራፎችና ስዕሎች፣ ቀለም) ፍንጭ ሰጪዎች ወይም የመስማት “ ለ-- ዝግጁ ሁን“ “ ቁም“ “ ወደኔ ተመልከት“ “ አዳምጥ“ የመሳሰሉትን ፍንጭ ሰጪዎች በመጠቀም ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ወይም የራሳቸው የትምህርት ቅስሞሽ እንዲመሩ እገዛ ያደርጋል፣ • መረጃን ለማስተላለፍ ቀላል ቋንቋና መመሪያ መጠቀም፤ • ረቂቅ መረጃን ለተማሪው ህይወት ተገቢ ወደ ሆነው ተጨበጭ ሁኔታ መተርጎም፤ • ተማሪዎች ውሳኔ ለመስጠት ወይም ችግራቸውን ለመፍታት ውጤታማ የሆኑ አማራጮችን እንዲያፈላልጉ በሀሳብ ማገዝ፤ • ተማሪዎች መልሳቸውን እንዲያደራጁ በቂ የቆይታ(በትንሹ አስር ደቂቃ) ጊዜ የመስጠት፤
ማየት መሣን	• የራስ እይታ • የተለያዩ ገፅታዎች ፅንሰ ሃሳቦች • ለመጓዣ መንገድ ምልክቶችን የመምረጥ ቴክኒክ • በአይናማ መሪ የመጓዣ ቴክኒክ • ቀሪ እይታን መጠቀም፣ • ብሬል፣ • የትውውቅና እንቅስቃሴ ክሂሎት፣ • መረጃን ለመግኘት ለመረዳትና ለማስታወስ የትምህርት ቅስሞሽ ስትራቴጂዎች፣ • ለራስ ተሟጋች መሆን፣	• ቋሚ በሆነ መንገድ ማደራጀት ይህም በመሣሪያዎችና ቁሳቁሶች መካከል በቀላሉ ለመንቀሳቀስ ያስችላል፣ • ጎላ ያሉ ፊደሎች ይዘው የታተሙ ቁሳቁሶች ወይም ሶፍትዌር ወይም የብሬል ቁሳቁሶች መስጠት፣ • በድምፅ መቅረጫ የተቀረፁ ማቴሪያሎችን መስጠት፣ • ድጋፍ ሰጪ የቴክኖሎጂ፣ መሣሪያዎችን መጠቀም/የብሬል መሣሪያ ፣አጉሊ መነፅር፣ ብቃትን በማተም ለማወቅ የሚያስችሉ የሚናገሩ ኮምፒዩተሮች፣የማንበቢያ ማሽን፣በጥቁር ማርከር የሚፃፍበት ነጭ ሠሌዳ ፣የሚናገር ካልኩሌተር • የሚነካኩና የሚገጣጠሙ ቁሳቁሶችን መስጠት፣ • የማያንፀባርቁና ተቃራኒ ቀለም ያላቸው ቁሳቁሶችን መስጠት፣ • ተማሪዎች ከተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጮች የሚጠቀሙበት መንገድ መፈለግ፣
መስማት መሣን	• ንግግርን ማንበብ፣ • የምልክት ቋንቋ፣ • የጣት ፊደላት፣ • የማዳመጥ ችሎታ ስልጠና፣	• ድምፅን የሚያጎሉ መሣሪያዎችን መጠቀም (ማዳመጫ መሣሪያ፣ በክፍል ውስጥ የድምፅ ማጉያ መሣሪያ፣ወዘተ)፣ • ያልተጋነነ ግልፅና ተፈጥሯዊ የቋንቋ ዘይቤ መጠቀም፣ • ስትናገር ፊትህን ወደታዳሚው አዙር ሙሉ ፊትህ የሚታይ ይሁን፣

	• በአፍ መፍቻ ቋንቋ ሃሳብን መግለፅ፣ • መስማት የተሣናቸው የባህል ገፅታ፣ • ለራስ ተሟጋች መሆን፣	• ጠቃሚ መረጃዎችን በሰሌዳ ላይ ፃፍ ወይም ማስታወሻ አዘጋጅተህ ለተማሪዎችህ ስጥ፣ • ማስታወሻ እንዴት እንደሚወሰዱ መመሪያ መስጠት ወይም ጓደኞቻቸው ማስታወሻ እንዲወስዱላቸው አድርግ፣ • የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ መጠቀም • መስማት ለተሣናቸው ተማሪዎች ሥርዓተ ትምህርቱን ማስማማት • የተማሪው መማሪያ መፃሕፍትና ወርክሺቶችን በዝቅተኛ የንባብ ደረጃዎች እንዲያነቡ ማድረግ • ረቂቅ መረጃዎችን ተጨባጭነት ወዳላቸው ነገሮች መተርጎም • የእይታ መረጃ መሣሪያዎችን (የስልክ ዕሑፍ፣ምልክት ያላቸው የሚነካኩ የበር ደውሎች፣ሰዓቶች፣ የጭስ ማንቂያ ደውሎች) መስጠት፣ • በምርጫቸው መሠረት እንዲቀመጡ ማመቻቸት ፣
መሠረታዊ የመማር ችግሮች	• የሙከራ (test) አወሳሰድ ስትራቴጂዎች • የማስታወሻ አወሳሰድ ስትራቴጂዎች፣ • የማደራጀት ክሂሎት፣ • ፍሬነገሩን የመምረጥ ክሂሎት • በማዛመድ የማስታወስ ስትራቴጂዎች • መረጃን ለማግኘት ለመረዳትና ለማስታወስ የትምህርት ቅስሞሽ ስትራቴጂዎች፣ • ለራስ ተሟጋች መሆን፣ • አስቸጋሪ ሁኔታዎችን መጋፈጥ • የመስማትና የእይታ ክሂሎት ማዳበር፣ • የተግባቦት ክሂሎት፣ • የችግር ፈቺ ክሂሎት፣	• እንዴት እንደሚያጠኑ መምራት፣ ሙከራን ደጋግሞ መሥራት፣ የተማሪው መማሪያ መፃህፍት አንኳር ነገሮችን መለየትና በድምፅ መቅረጫ መቅረጽ፣ • አማራጭ የመልስ መስጫ መንገዶችን፣ተጨማሪ ሰዓት ወይም አማራጭ የተግባር ማከናወኛ ቦታዎችን ወይም ሙከራዎችን መፍቀድ፣ • የተማሪውን የነፍስ ወከፍ ግቦች መሠረት በማድረግ አማራጭ የውጤት አሰጣጥ መስፈርት መጠቀም፣ • ጠቃሚ መረጃዎችን ለመስጠት የፍንጭ መስጫ ሥርዓትና አደረጃጀት መዘርጋት፣ • የተማሪውን መማሪያ መፃህፍትና ወርክሽቶችን ዝግ ብለው እንዲያነቡ (ሳይፈጥኑ) ማድረግ፣ • ረቂቅ መረጃዎችን ተጨባጭነት ወዳላቸው ነገሮች መተርጎም፣ • በተማሪው የመማሪያ መፃህፍት፣ ወርክ ሽቶች፣የሙከራ ማቴሪያሎችና የቤት ሥራዎች ውስጥ የተሰጡትን መረጃዎች ማደራጀት • ለቁልፍ መረጃዎች የእይታ ኮድ መስጠት፣ • የተማሪው የነፍስ-ወከፍ የመማር ፍላጎቶች መልስ ለመስጠት አማራጭ የግምገማ ዘዴዎችን መጠቀም፣ • በተለያዩ መንገዶች መረጃን ለማስተላለፍና የተማሪውን ውጤት ለመመዘን የተለያዩ የትምህርት ቅስሞሽ ዘዴዎች ላይ ማተኮር ይገባል፣ • አልፋ ስማርትስና ስፔልቼከርስን የመሳሰሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም
የስሜት መረበሽና የባህርይ ችግሮች	• ግቦችን መጣልና ውሳኔ መስጠት፣ • እራስን መጠየቅ፣ • እራስን መቆጣጠር፣ • እራስን መገምገም፣ • እራስን ከሁኔታዎች ጋር ማጣጣም፣ • የራስ ተነሳሽነት፣ • በሚገኘው ግብረ መልስ ራስን	• ተማሪዎችን ወደተፈለገው ተግባር ለመምራት ፍንጭ መስጠት፣ • ተማሪዎች ክሂሎትን ለማዳበር የሚጠቀሙበትን የተግባር ክንውን ጊዜ መጨመር፣ • የሚፈለገውን ባህርይ ሞዴል ማድረግ • የተማሪዎቹን የምርጫ እድሎች ማስፋትና በእለት ተእለት ውሣኔዎች መሣተፍ፣ • ተማሪዎች ተስፋ የሚያደርጓቸውን ሁኔታዎችና የውጤታቸውን ሂደቶች እንዲያውቁ እድል መስጠት • ተማሪዎቹ አካባቢያችንን መቆጣጠር እንችላለን ብለው በሚያስቡት ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፉ መፍቀድ፣

	መቆጣጠር • ፍላጎታቸውን በአዎንታዊ መንገዶች የሚገልፁበት ቋንቋ፣ • ማህበራዊ ክሂሎት (መስተጋብርን የሚያነሣሣ፣ ተራ መጠበቅ)፣ • ንዴት መቆጣጠር፣ • ጭንቀትን መቆጣጣር፣ • ለራስ ተሟጋች መሆን፣	
የንግግር የቋንቋ ችግሮች	• አማራጭ የተግባቦት ክሂሎት • ቋንቋን የመግለፅ ክሂሎት • ቋንቋን የመቀበል ክሂሎት • የማብራሪያ ስትራቴጂዎች • የንግግርና የቋንቋ ችግሮችን ማሻሻል • መረጃን ለማግኘት ለመረዳትና ለማስታወስ የትምህርት ቅስሞሽ ስትራቴጂዎች፣ • እረፍትና ፀጥታ የማግኛ ቲክኒኮች • ለራስ ተሟጋች መሆን	• መልእክቶች በትክክል መቀባሉን ማረጋገጥ • አማራጭ የተግባቦት ዘዴዎችን (የምልክት ቋንቋ፣የጣት ፊደላት፣ወዘተ) መጠቀም፣ • አማራጭ የተግባቦት መሣሪያዎችንንና ሥርዓት (የማዳመጫ መሣሪያ፣ የማዳመጥ ስልጠና፣የድምፅ ማጉያ መሣሪያ) መጠቀም • የእይታ (አመልካች፣ ግራፎችና ስዕሎች፣ ቀለም) ፍንጭ ሰጪዎች ወይም የመስማት “ ለ-- ዝግጁ ሁን“ “ ቁም“ “ ወደኔ ተመልከት“ “ አዳምጥ“ የመሳሰሉትን ፍንጭ ሰጪዎች በመጠቀም ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ወይም የራሳቸው የትምህርት ቅስሞሽ እንዲመሩ እገዛ ያደርጋል፣ • ቴክኖሎጂን መጠቀም (የቃላት ግምት መስጠት መርሃግብር፣አማራጭ የግብዓት ዘዴዎችን) • በቂ የመልስ መስጫ ጊዜ መፍቀድ
ከፍተኛና ድርብርብ የአካል ጉዳቶች	• ተግባራትዊ ትምህርት (ገንዘብ መቀጠም፣ እቃ ዎችን በቦታቸው ማስቀመጥ፣የመግባቢያ ቃላትን መማር፣ከካፊቴሪያ ውስጥ የሚፈልጉትን መምረጥ) • መምረጥ መቻል (መርጦ ግንኙነት መፍጠርና የሚጎዱ ሹል ነገሮችን ያለመጠቀም ክሂሎት) • በአካባቢው ውስጥ እራስን መምራት • የግል ንፅህና አጠባበቅ እራስን ከአደጋ መጠበቅ ክህሎት በተለይም ተማሪዎች	• የተለያዩ የተግባቦት ክሂሎትን መጠቀም (የፊት ገፅታ፣የእጅ የእግርና የራስ እንቅስቃሴ፣ ንግግር፣ ቋንቋ አልባ መግባባት፣ የምልክት ቋንቋ፣ ድጋፍ ሰጪ ቴክኖሎጂ) • የንግግር የእይታና የመነካካት ፍንጭ ሰጪ ነገሮችን መጠቀም ተግባሩን ወዲያው እንዲሰሩት ማድረግ • ብልሃት የተሞላበት መመሪያ መጠቀም • ተፈጥሯዊ የሆኑ ፍንጭ ሰጪ ነገሮችን መጠቀም • ምቹና ተስማሚ የሆኑ መሣሪያዎችን መጠቀም /ድምፅ አነቃቂ ኮምፒዩተሮች፣ግለሰቦች እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ የሚያነቃቁ መሣሪያዎች ወይም የማንበቢያ መሣሪያዎች • ሁሉም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች በመመሪያው ውስጥ መካተታቸውን በማረጋገጥ የተግባር ትንተና መጠቀም • ተደጋጋሚ ግብረመልስና ማትጊያ መስጠት • መደበኛ የእረፍት ጊዜ እንዲኖር ማደራጀት

	በሚሣተፉበት አካባቢ የሚያስፈልጉ ናቸው • ማህበራዊ ክሂሎት • የተግባቦት ክሂሎት (መስተጋብራዊ ተግባቦትን ማነሣሣትና ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ) • ምክንያትና ውጤት • የመዝናኛ የመጫወቻ ቦታ ክሂሎት • ለራስ ተሟጋች መሆን	
ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ	• በጥልቀት የማሰብና የፈጠራ ክህሎት፣ • የጥናትና ምርምር ክሂሎት • እራስን ችሎ የማጥናት ክሂሎት • ለራስ ተሟጋች መሆን	• የተለያየ ጭብጥ ያላቸውን የጥናት መስኮችን ወይም የተለያየ ሁኔታ ላይ የሚያተኩሩ ትምህርቶችን ማካተት • ፅንሰ ሃሳቦችን ከአጠቃላይ ትምህርት ዩኒቶች ላይ በመውሰድና አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ርዕሶች ላይ ጥልቀት ያለው ትምህርት በመስጠት እንደየፍላጎታቸው እንዲመርጡ ማበረታታት፣ • ደረጃቸው ከፍ ያለ የሚነበቡ ነገሮችን መስጠት፣ • ሥርዓተ ትምህርቱን በፍጥነት እንዲማሩ ማድረግ (በት/ቤት ቀድሞ መመዝገብ፣ ማዘለል፣ኮሌጅ ቀድመው እንዲመዘገቡ ማድረግ) • ሥርዓተ ትምህርቱን ማሳጠር/መጭመቅ • ተጨማሪ የሌሎች ባለሙያዎችን እገዛ ሊያገኙ የሚችልበትን መርሃግብርመጠቀም • ተጨማሪ የማበልፀጊያ)ተግባራትን መስጠት
የአካል ጉዳተኞች (የእጅ ፣የእግርና የወገብ እንቅስቃሴዎች ችግር)	• እራስን ችሎ መኖርን የሚያበረታቱ ክሂሎት • በክፍል ውስጥ በት/ቤት በቤት፣ በሥራ ቦታና በማህበረሰቡ ውስጥ መንቀሳቀስ (መጓዝ) • የግል ጤናንና እራስን ከአደጋ መጠበቅ፣ • ለራስ ተሟጋች መሆን፣	• አግባብነት ያለው የሰውነት አቅጣጫና የአቀማመጥ መርሆዎችን መተግበር • የክፍል ውስጥ ቁሳቁሶችንና የሥራ ቦታን ተደራሽ ማድረግ • የተማሪውን ፍላጎት ለማርካት የክፍል ውስጥ ሁኔታውን (ከፍታ፣አግድመት ....) በማሻሻል ምቹ ማድረግ • ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ ቁሳቁሶችን ማቅረብ፣ • ቴክኖሎጂንና ተስማሚ መሣሪያዎችን (የእንቅስቃሴ መሣሪያዎች፣የወገብና ክንድ መደገፊያዎች፣ ገጽ የሚገለብጥ መሣሪያ፣ተስማሚ ሠሌዳ ስካነር የድምፅ መለያ መርሃግብር፣ ከአፍጋር የሚገጠሙ መሣሪያዎች)
ኦቲዝም	• የጥሞና ክሂሎት፣ • የትውስታ ክሂሎት፣ • ተግባራዊ ትምህርት፣ (የሥራ ማመልከቻ መሙላት፣መሰረታዊ የመግባቢያ ቃላትን መማር፣ የገንዘብ አጠቃቀምን፣ ማወቅ፣በንግግር ሃሳብ	• እራስን ችሎ ህይወትን ለመምራት የሚያስችሉ ክሂሎትን ማለትም የእለት ተዕለት ተግባራትን በቤት በት/ቤት፣ በሥራ ቦታ ወይም በማህበረሰብ አካባቢ ለመስራት የሚያስችሉ እድሎችን ይፈጥራል ።(ጫማ ማሰር፣ ቢስኪሌት መንዳት፣ ከአንድ ክፍል ወደ ሌላ ክፍል መዘዋወር፣ለሰዎች በተገቢው መንገድ ሰላምታ መስጠት)የመሳሰሉትን ለመተግበር የሚያስችል ነው። • ተጨባጭ፣ እድሜን ያማከለ፣ በእውነተኛ ህይወት ላይ የተመሠረተ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን መጠቀም • አዳዲስ ነገሮችን በቅደም ተከተል ማሳየት፣ መረዳታቸውን ማረጋገጥ • ድጋፍ ሰጪ ቴክኖሎጂ ተጠቀም

	መለዋወጥ፣) • የተግባቦት ክሂሎት፣ • የማህበራዊ መስተጋብር ክሂሎት፣ • የትምህርት ቆስሞሽ ስትራቴጂዎች፣ • ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣ • አንድን ነገር የማደራጀት ክሂሎት፣ • ሃሳብን የማጠቃለል ክሂሎት፣ • ተግባቦትን ማመቻቸት፣ • ለራስ ተሟጋች መሆን ፣	• የእይታ (አመልካች፣ ግራፎችና ስዕሎች፣ ቀለም) ፍንጭ ሰጪዎችን ወይም የመስማት " ለ-- ዝግጁ ሁን" " ቁም" " ወደኔ ተመልከት" " አዳምጥ" የመሳሰሉትን ፍንጭ ሰጪዎች በመጠቀም ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ወይም የራሳቸው የትምህርት ቅስሞሽ እንዲመሩ እገዛ ያደርጋል፣ • መረጃ ማስተላለፊያ ቋንቋዎችንና መመሪያዎችን በቀላሉ መንገድ ማቅረብ • ረቂቅ መረጃዎችን ከተማሪዎቹ ህይወት ጋር ከሚገናኙ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ መተርጎም • የተለያዩ የተግባቦት ክሂሎትን መጠቀም (የፊት ገፅታ፣የእጅ የእግርና የራስ እንቅስቃሴ፣ ንግግር፣ ቋንቋ አልባ መግባባት፣ የምልክት ቋንቋ፣ ድጋፍ ሰጪ ቴክኖሎጂ) • ተግባራትን ፈጥነው እንዲያከናውኑ በንግግር ምልክት መስጠት • ሥርዓት ያለው (ሥልታዊ) የማስተማር ዘዴን መጠቀም • ተፈጥራዊ የሆኑ ፍንጭ ሰጪ ነገሮችን መጠቀም • ምቹና ተስማሚ መሣሪያዎችን መጠቀም
መስማት-ማየት መሳን	• ስለራስ እይታ • የንፅፅር ፅንሰ ሃሳቦች • የመጓጓዣ መንገድን ምልክት የመምረጥ ቴክኒኮች • በአይናማ መሪ የመሄድ ቴክኒኮች • የቀረውን እይታ መጠቀም • ብሬል • የትውውቅና እንቅስቃሴ ክሂሎት • በተረፈው የማዳመጥ ችሎታ መጠቀም፣ • የተግባቦት ክሂሎት • የምልክት ቋንቋ • የጣት ፊደላትን መጠቀም • የማዳመጥ ሥልጠና • የተግባር ትምህርቶች (የሥራ ማመልከቻ መሙላት፣ የመግባቢያ ቃላትን መማር ገንዘብን መጠቀም በንግግር መግባባት) • ለራስ ተሟጋች መሆን	• ተግባቦት ክሂሎትን ለማዳበር የተለያዩ ሞዴሎችን መጠቀም (የአካል እንቅስቃሴ፣ ንግግር ቋንቋ አልባ የምልክት ቋንቋ ድጋፍ ሰጪ ቴክኖሎጂዎች) • የንግግር፣ የእይታ ወይም የመነካካት ፍንጭን በመስጠት መጠቀም • ሥርዓተ ያለው (ሥልታዊ) የማስተማር ዘዴን መጠቀም • ምቹና ተስማሚ መሣሪያዎችን መጠቀም • የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎችን መጠቀም • ጎላ ያሉ ፊደላት ወይም የብሬል ቁሳቁሶችን መስጠት • በድምፅ የተቀረፁ ቁሳቁሶችን መስጠት • በቴክኖሎጂ የሚታገዙ መሣሪያዎችን መጠቀም (የብሬል መፃፊያ መሣሪያ፣ አጉሊ መነፅር፣ በማተም ችሎታን ለማወቅየሚያስችሉየሚናገሩ ኮምፒውተሮች የንባብ መሣሪያ) ስካን የሚያደርጉና ጮክ ብሎ የሚያነብ ለጥቁር ማርከር መጠቀሚያ የሚሆን ነጭ ሠሌዳ የሚናገር ካልኩሌተር • ተማሪዎቹን ሊያነቃቁ የሚችሉ የሚነካኩ ነገሮች መስጠት • ዝቅተኛ ደረጃና ተቃራኒ ቀለም ያላቸውን ወረቀቶች መጠቀም • እየመረጡ በሚመቻቸው ቦታ እንዲቀመጡ ማድረግ

በጭንቀት የሚከሰት የአእምሮ ቁስለት	• የሙከራ አወሳሰድ ስትራቴጂዎች • የማስታወሻ አወሳሰድ ስትራቴጂዎች • ፍሬ ሃሳቡን የማስቀመጥ ክሂሎት • ለማስታወስ የሚረዱ ቁልፍ ቃላት አጠቃቀም ስትራቴጂዎች • መረጃዎችን ለማግኘት፣ለመረዳትና ለማስታወስ የሚያግዝ የትምህርት ቅስሞሽ ስትራቴጂዎች • እራስን መምራት ክሂሎት • የትውስታ ስትራቴጂዎች • የግንዛቤ ክሂሎት • የችግር ፊቺ ክሂሎት • በራስ ተሟጋች መሆን	• የተለያዩ የግንዛቤ ክሂሎትን ኢላማ በማድረግ ለማዳበር ኮምፒዩተሮችን መጠቀም • ትምህርት የሚሰጥበትን ጊዜ ማሳጠር • በውን ያሉ ተጨባጭ የሆኑ የእድሜ ተመጣጣኝ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን መጠቀም • አዳዲስ አሰራሮችን ቅደም ተከተል ባለው መንገድ ማሳየት፣ በእያንዳንዱ ደረጃም መረዳታቸውን ማረጋገጥ • መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የመለያ ጥያቄዎችን መጠቀም፣ • እንደተግባቦት መሣሪያዎች ያሉ አጋዥ ቴክኖሎጂ መጠቀም፣ • የእይታ (አመልካች፣ ግራፎችና ስዕሎች፣ ቀለም) ፍንጭ ሰጪዎችን ወይም የመስማት “ ለ-- ዝግጁ ሁን“ “ ቁም“ “ ወደኔ ተመልከት“ “ አዳምጥ“ የመሳሰሉትን ፍንጭ ሰጪዎች በመጠቀም ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ ወይም የራሳቸው የትምህርት ቅስሞሽ እንዲመሩ እገዛ ያደርጋል፣ • መረጃ ማስተላለፊያ ቋንቋዎችንና መመሪያዎችን በቀላሉ መንገድ ማቅረብ • ረቂቅ መረጃዎችን ከተማሪዎቹ ህይወት ጋር ከሚገናኙ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ መተርጎም • መረጃዎችን ሊጠቅሙ በሚችሉ መንገድ በማደራጀት መጠቀም፣ • አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የእረፍት ጊዜውን ብዙ ማድረግ።